አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3550 | ቅዳሜ ህዳር 27 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር




# “ብዙ ያልፈጠረ ጥራትን ማረጋገጥ አይችልም”

## ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)



ፎቶ- ከፋይል

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

- **የሀገርን ከፍታ ለማረጋገጥ መፍጠን፣ መፍጠር፣ ማብዛት እና ያንንም በጥራት አሳድጎ መስራት እንደሚገባም ተመላክቷል**

**በመለሰ ተሰጋ**

የኢትዮጵያን የታሪክ ምዕራፎች በትዝታ አክናፍ በእውነት መዳፍ ከፊት ወደ ኋላ ገለጥ ገለጥ ብናደርግ ከአክሱም ሀውልት እስከ ላል ይበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት፣ ከሶፍ ኡመር ዋሻ እስከ ጀጎል ግንብ፣ ከጥያ ትክል ድንጋይ እስከ ሀላላ ኬላ ...፣ ከዘርያዕቆብ የፍልስፍና ምጥቀት እስከ አባ ጅፋር የቴክኖሎጂ ዕውቀት... ከፍ ከፍ ያሉ አያሌ የሀገር አብነቶችን መጥቀስ እንችላለን።

ይሁን እንጂ የአክሱም ሀውልትን ከወጥ ድንጋይ ያነፀው፣ ቤትን ከጣሪያ ጀምሮ በመሰራት መጨረስ እንደሚቻል ላል ይበላን ሰርቶ የዓለምን የህንፃ አሰራር ጥበብ ፉርሽ ያደረገው ያ! ትውልድ መፍጠኑን አቁሞ፣ መፍጠሩን ትቶ፣ ማብዛቱን እና ማጥራቱንም ዘንግቶ እንዴት ባለበት ቆመ!

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

“የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ቀንን ስናከብር ትኩረታችን የወል ትርክትን ማስረጽ መሆን አለበት”



8

ፎቶ- ከገፀ ድር

የሕገ-መንግስት እና ፌዴራሊዝም አስተምህሮ ማዕከል ዋና ዳይሬክተር ኃይለየሱስ ታዬ (ዶ/ር)

በብዝሃነት የጎለበተ አንድነት



4

ፎቶ- ከገፀ ድር

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ያለ ልዩነት ከሁሉም አቅጣጫ መጥተው የተሳተፉበትና መስዋዕትነት ከፍለው ያገኟቸው ድሎች በርካታ ናቸው

ተስፋ ያጫረው የስፖርቱ ስኬትና ምስጢሩ



20

ፎቶ- ከገፀ ድር

የኢትዮጵያ ከ17 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድን ከ22 ዓመታት በኋላ ሞሮኮ በምታዘጋጀው የ 2026ቱ የአፍሪካ ዋንጫ ላይ ይሳተፋል

# ለቤት አቅርቦቱ የቴክኖሎጂ መላ

“በዚህ ዓመት ከያዝናቸው ዋነኛ እቅዶች መካከል ቀዳሚው ለከተማችን ነዋሪዎች የቤት አቅርቦትን ተደራሽ ማድረግ ነው”

## የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ



ፎቶ- ከገፀ ድር

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ለሀገራችን የመጀመሪያ በሆነው የግንባታ ቴክኖሎጂ 26 ሺህ ቤቶችን ስራ አስጀምረዋል

- **በፍጥነቱ፣ በጥራቱ እና በጥንካሬው ተመራጭ የሆነውን ኮልድ ፎርምድ እስቲል (ሲ.ኤ.ኤስ) ቴክኖሎጂን በመጠቀም የ26 ሺህ ቤቶች ግንባታ ተጀምሯል**

**በመለሰ ተሰጋ**

አዲስ አበባ ውበት እንደጅረት የሚጎርፍባት ግሩም ከተማ ናት። ለመኖሪያ፣ ለንግድ፣ ለኢንቨስትመንት እና ለመዝናኛ ምቹ በመሆኗ በርካቶች ይመርጧታል፡፡ እናም፣ ከተማዋን በስራ መግቢያና መውጪያ ላስተዋላት ወዲያ ወዲህ የሚተራመሰው የአዳም ዘር መብዛቱን

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

# የፌዴራሊዝም ስርዓቱ መንገድ ሲቃኝ

- **ሀገራዊ እና ብሔረሰባዊ ማንነቶችን ሚዛናዊ አድርጎ ለመሄድ የተጀመሩ ስራዎችን አጠናክሮ ማስቀጠል እንደሚገባ ተጠቁሟል**

**በስንታየሁ ምትኩ**

ኢትዮጵያ የብዝሃነት አምባ ናት፡፡ ብዝሃነት ውበትና ድምቀቷ ነው፡፡ እነዚህ ብዝሃ-ማንነቶች የሰፆት አገር ብትሆንም፤ ብዝሃነቱ ተገቢውን እውቅና አግኝቶ፣ በእኩልነት፣ በዴሞክራሲና በሰላም መኖር የሚያስችል የፖለቲካ ስርዓት አልነበረም።

ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ማንነታቸው ታውቆ፣ ራስን በራስ የማስተዳደር መብታቸው

ወደ ገጽ 6 ዞሯል




አድራሻ +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

# ርዕሰ አንቀፅ



## ብዝሃነትን ማክበርና ጠንካራ አንድነትን መገንባት ለእድገታችን ወሳኝ ነው!

ኢትዮጵያ የበርካታ ማንነቶች ባለቤት የሆኑ ህዝቦች በአንድነት ጠላትን እየመከቱ እስከዛሬ ያቆዩዋት ሀገር ነች። አያቶቻችን በርካታ ገድሎችን ተባብረው በአንድነት ፈፅዋል፡፡ የዓድዋ ድል አንዱ የዚህ እውነት ማሳያ ነው፡፡ ከመላው ኢትዮጵያ ተውጣጥተው ወደ ዓድዋ ተራሮች የተመሙት እኒህ ጀግኖች አያቶቻችን ዘመናዊ የጦር መሳሪያ በያዘው ወራሪ ኃይል ፊት በድፍረት የቆሙት ያለ የዘር፣ የኃይማኖት፣ የብሔር እና ሌሎች ማንነቶች ልዩነት ነው፡፡

የበርካታ ማንነቶች ባለቤት የሆኑ ኢትዮጵያውያን በአንድነት ሆነው ከወራሪው ጣሊያን ጋር ገጥመው ድል የነሱት በጠንካራ የአንድነት መንፈስ ነው፡፡ ይህ በብዝሃነት ውስጥ ያለ የአንድነት መንፈስ እንደ ካራማራ፣ ዶጋሊ፣ ጉንደት እና ጉራዕ ባሉት ድሎች የጦርነት አውዶችም ተደግሟል፤ ምክንያቱም ኢትዮጵያውያኑ ሊወርሯቸው የመጡ የተለያዩ ሀገራት ኃይሎችን ያለ ልዩነት በጋራ ሆነው ድል ነስተዋል፡፡

የዚህ ሚስጥሩም ምንም እንኳ ልዩነቶች ቢኖሩም ኢትዮጵያውያን ከጊዜያዊ ግጭት ባለፈ የሀገርን ሉዓላዊነት አደጋ ላይ የሚጥል ነገር ሲያጋጥም ቅድሚያ ለሀገር አንድነት ዘብ የሚቆሙ በመሆናቸው ነው፡፡

ይህን ብዝሃነትን እንደ ውበት የቆጠረና ለሀገራዊ አንድነት ዋጋ የሰጠው መንገድ በልማቱም ጭምር ስኬት እንዲገኝበት ስለማድረጉ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ አብነት ነው፡፡ የግድቡ ግንባታ ከተበሰረበት መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ኢትዮጵያውያን ከጫፍ እስከ ጫፍ በመንፈስ ተሳስረዋል፤ ለጋራ ጉዳይ በጋራ ቆመዋል፤ ትንሽ ትልቁ፣ ድሃና ሀብታሙ፣ ነጋዴና ገበሬው ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዘር፣ ኃይማኖት፣ ብሔር ሳይለየው በጋራ የተሰለፈበት የጋራ የድል አድራጊነት ታሪክ ነው፡፡

ኢትዮጵያውያን ለበርካታ በረከቶች ያበቃቸውን ይህን በአንድነት የተሸመነ ብዝሃነታቸውን በአንድነት ሆነው ያከብሩታል፤ ብዝሃነቱ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ልብ ውስጥ የታተመ ቢሆንም በአደባባይም ወጥተው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀንን በጋራ ያከብሩታል፡፡

ዘንድሮ 20ኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በዓል በፌዴሬሽን ምክር ቤት አስተባባሪነት “ዴሞክራሲያዊ መግባባት ለኅብረ ብሔራዊ አንድነት” በሚል መሪ ቃል በተለያዩ መርሃ ግብሮች በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳድሮች ከህዳር 1 ቀን ጀምሮ በድምቀት እየተከበረ የሚገኝ ሲሆን፣ ሀገራዊ ማጠቃለያ መርሃ ግብር በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በሆሳዕና ከተማ ህዳር 29 ቀን 2018 ዓ.ም ይከበራል።

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ቀን በዓል ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝቦች ማንነታቸው እንዲከበር፣ ለፍትህ፣ ነፃነትና ለዴሞክራሲ ስርዓት መከበር፣ በጋራ በወንድማማችነት ላይ የተመሰረተ ሕብረ ብሔራዊ አንድነት የበለጠ እንዲጠናከር ታስቦ የሚከበር ነው፡፡

ኢትዮጵያውያን በአንድነት ተባብረው ያገኟቸው ድሎች ሳይደበዝዙ የበለጠ ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል። በቀጣይም ወቅቱ የሚጠይቀው የሀገረ መንግስት ግንባታ እንዲጎለብት ልዩነትን በአከበረ መልኩ አንድነትን በማጠናከር መጓዝ ይገባል፡፡

# የእኔ እይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

## ሊዘምን የሚገባው የተቋማት የአቅጣጫ ጠቋሚ ስርዓት

**በሰናይ ምግባሩ**

መረጃ ሀብት ነው፤ ጊዜ ደግሞ ወርቅ፡፡ በተለይ አሁን ያለንበት የዲጂታል ዘመን የእነዚህን ሁለት ነገሮች ዋጋ ከፍ ያደርገዋል፡፡ የአደጉት ሀገራት በዚህ ረገድ የተሻለ ተሞክሮ አላቸው ብሎ መናገር ይቻላል፡፡ መዲናችን አዲስ አበባ ደግሞ የኢትዮጵያውያን ብቻም ሳይሆን የአፍሪካ መዲና፣ ሶስተኛዋ የዲፕሎማቲክ ማህበረሰቡ መቀመጫ፣ የተለያዩ ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ስብሰባዎች የሚካሄድባት እንደመሆኑ በመንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ያለው አገልግሎት አሰጣጥ የተሳለጠ እና ወቅቱን የሚመጥን ማድረግ ላይ በትኩረት መስራት ይጠበቅባታል፡፡ የመንግስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ ረገድ እየተሰሩ ያሉ ስራዎች ይበል የሚያሰኝ ነው። ከዚህ ጎን ለጎን ተገልጋዮች ወደ ተቋማት ሲመጡ የሚፈልጉት አገልግሎት ያለበትን ክፍል በቀላሉ ማግኘት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል ብዬ አምናለሁ፡፡

ለዚህ መነሻ የሆነኝ በትናንትናው ዕለት ለስራ ጉዳይ ከጓደኞቼ ጋር ወደ አንድ መንግስታዊ ተቋም ሄድን። ከመስሪያ ቤቱ ስፋት አንጻር እኛ የምንፈልገው አገልግሎት ያለበትን ክፍል በቀላሉ ለማግኘት ተቸገርን። ይህም ቀላል የማይባል ጊዜ እንድናባክን፣ ሰዎችንም ደጋግመን እንድንጠይቅ ግድ አድርጎብናል። መግቢያው በር ላይ ወዴት መሄድ እንደምንፈልግ ጠይቆ መረጃ የሚያጋራን አካል ቢኖር አልያም ደግሞ ክፍሎቹ የሚገኙበት ጠቋሚ ነገር በግልጽ ሊታይ በሚችል ሁኔታ ቢቀመጥ ይህን ሁሉ ድካም መቀነስ ይቻል ነበር፡፡

ይህን መነሻ አደረግኩ እንጂ እኔን ጨምሮ አብዛኛው ሰው ወደ ተቋማት ለአገልግሎት ስንሄድ የምንፈልገውን ክፍል በቀላሉ ለማግኘት እንቸገራለን። ምን አልባትም ቦታው ወረፋ ካለ በዚህ አይነቱ መደናገር ብዙ ሰዎች ሊቀድሙን፣ አንዳንዴም ‘ሰዓት ደርሷል ነገ ና/ነይ’ እስከማስባል ሊያደርሰን እንደሚችል ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ይህ ደግሞ በአንድም በሌላም መልኩ የመልካም አስተዳደር ችግር ሆኖ ተገልጋዮችን ሊያማርር ስለሚችል ለጉዳዩ ተገቢውን ትኩረት መስጠት ይገባል ባይ ነኝ፡፡ ይህን ስል ለዚህ በሚመጥን መልኩ የተደራጀ የመረጃ ዴስክ ያላቸው ተቋማት የሉም እያልኩ እንዳልሆነ ይታወቅልኝ፡፡

ከዚህ አይነት ልምምድ ውጭ የሆኑ ተቋማት ግን ባላቸው የሰው ኃይልና የቴክኖሎጂ አቅም ይኼን ተግባራዊ ቢያደርጉ፣ የሚያደርጉትም ምን ያህል የተጠናከረ እንደሆነ ቢፈትሹ ጥሩ ነው፡፡ ቢያንስ ቢያንስ በትልቅ ባነር ላይ ክፍሎችን እና የህንጻና ቢሮ ቁጥራቸውን ጽፎ መግቢያ በር ላይ መስቀል ቢቻል ሊፈጠር የሚችለውን እንግልት በተወሰነ መልኩም ቢሆን ይቀንሰዋል ብዬ አስባለሁ።

“ደንበኛ ንጉስ ነው፣ የተገልጋይን እርካታ ለመጨመር እንሰራለን፣ የሚመጣው ሰው ግብር ከፋይ በመሆኑ ተገቢ የሆነ አገልግሎት የማግኘት መብት አለው...” ብሎ ለሚሰራ ተቋም ለእንደነዚህ ቀላል ለሚመስሉ ነገር ግን ወሳኝ ስራዎችም ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይጠበቅበታል፡፡ ነጭ ነገር ላይ ያለች ትንሽዬ ጥቁር ነጥብ ጎላ ብላ እንደምትታየው፤ ሁሉ ብዙ ጥንካሬ ባለው ተቋም ጭምር በእንደነዚህ አይነት ክፍተቶች ስሙ እንዳይጠለሽ መጠንቀቅ መቻል አለበት፡፡

የተቋማትን አገልግሎት የሚከታተለው፣ የሚደግፈውና የሚቆጣጠረው አካል ደግሞ በዚህ ላይ ተገቢውን ግብረ መልስ መስጠት፣ የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ማድረግ ይጠበቅበታል ብዬ አስባለሁ፤ እናንተስ ምን ትላላችሁ?

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እየተዘጋጀች

ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን
የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ

ግንቦት 1985 ዓ.ም
ተመሰረተች

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት
በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜልባ ፐሪንቲንግ ፐብሊሺንግ ኤንድ ፓኬጂንግ ሼር ካምፓኒ

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ለይላ መሀመድ
ይግለጡ ጓዴ
ሄለን ጥላሁን
ፋንታነሽ ተፈራ

**ዋና አዘጋጅ**
ምህረቱ ፈቃደ
Mehretu@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 34/55

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# “ብዙ ... ከገጽ 1 የዞረ

ስልጣኔን ቀድሞ ጀምሮ ለምን ጭራ ሆነ! የሚለውን ስናስብ ነገሩ ውስብስብነት ባያጣውም እጅጉን የሚያስቆጭ መሆኑ ግን አያጠያይቅም፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ይህንኑ እውነት ከነ መፍትሔው ጭምር በመደመር መፅሐፋቸው መግቢያ አስፍረውታል፡፡

ከሰሞኑም ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ “በመደመር መንግሥት ዕይታ፣ የዘርፎች እመርታ!” በሚል መሪ ቃል ለከፍተኛ አመራሮች ስልጠና መስጠታቸው ይታወሳል፡፡

በዚሁ ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስለመፍጠር ሲያብራሩ፣ ብዙ ያልፈጠረ ጥራትን ማረጋገጥ አይችልም ብለዋል፡፡ እናም ከብዙ ፈጠራ ውስጥ ጥራት ያላቸው ጉዳዮች እንደሚወጡ አንስተዋል።

ብዙ ለመፍጠርም ፍጥነት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን በመግለጽ፣ ያልፈጠነ ጊዜው እንደማይጠብቀው አጽንኦት ሰጥተዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ብዛት፣ እድል እና ጥራት ግን ውጤት መሆኑን በማንሳት በብዙ ፈጠራ ውስጥ አዳዲስ እና ጥራት ያላቸው ነገሮችን ከብዙው ውስጥ መዝዞ ማውጣት እንደሚቻልም ተናግረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) አክለውም፣ በብዙ ፈጠራ ውስጥ ዘላቂ ውጤትን ማስቀጠል እንደሚቻል የገለጹ ሲሆን፣ በብዙ መፍጠር ውስጥ በመፍጠን ጥራትን ማረጋገጥ እንደሚቻልም ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያን ለማሻገር በመደመር መንግስት እሳቤዎች በመታገዝ፣ በመፍጠን መርህ፣ በመፍጠር እሳቤ፣ ፈጠራንም በማብዛት እና ያንንም በጥራት አልቆ በመስራት ሊሆን ይገባል ብለዋል።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያና አማካሪ አቶ በረከተአብ ተስፋዬ እንደሚሉት እንደ ሀገር ኢኮኖሚያዊ አቅማችንንም ሆነ ሌሎች ዘርፎችን የበለጠ ለማላቅ ከኢትዮጵያ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ሀብቶች፣ ታሪካዊ ዕውነታዎች እና ያለፈው ትውልድ የከወናቸው የዕድገትና የአብሮነት እርሾዎችን ከግምት በማስገባት ከዓለም ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ አቅጣጫን መከተል ይገባል፡፡

በመሆኑም መንግስት ያስቀመጣቸው “መፍጠር፣ መፍጠን፣ ማብዛት እና ማጥራት” የሚሉ አራት የማይነጣጠሉና የሚደጋገፉ እሳቤዎች ሀገርን ከታሪካዊ መቀዛቀዝ አውጥቶ ወደ ብልጽግና ለማሸጋገር የሚያግዙ የዕድገት ቀመሮች ናቸው ብለዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) አራቱን ምሶሶዎች አስመልክቶ በሰጡት ማብራሪያም መፍጠር፣ አዳዲስ ሐሳቦችንና መፍትሔዎችን በማመንጨት የሥራ እና የልማት መስኮችን ማስፋት ነው። የልማት ሥራዎችንና የለውጥ እርምጃዎችን በከፍተኛ ፍጥነትና ቅልጥፍና መፈጸምም ነው።

ማብዛት ደግሞ የተገኙ መልካም ልምዶችንና ስኬቶችን በስፋትና በተደራጀ መልኩ ማስፋፋት ሲሆን፣ ይህም የሥራ አፈጻጸምን፣ ስርዓቶችን እና ውጤቶችን


ፎቶ- ከፋይል
የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

ያለማቋረጥ በማሻሻል ጥራትን ማረጋገጥ እንደሆነም አብራርተዋል፡፡

እንደ ምጣኔ ሀብት ባለሙያው በረከተአብ ምልከታ ይህ ፍልስፍና የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን (ዶ/ር) ጠንካራ አመራር እና ኢትዮጵያን የመለወጥ ራዕይ የሚያንጸባርቅ ሲሆን፣ የሀገሪቱን ታሪካዊ ኃይልና የህዝቧን ተስፋ ወደ ተግባራዊ ውጤት ለመቀየር የሚያስችል የዕድገት ሞዴል መሆኑን ከለውጡ ወዲህ በግብርናው፣ በኢንደስትሪው፣ በቱሪዝም እና መሰል ዘርፎች እየታዩ ያሉ ውጤቶችን በአስረጂነት መጥቀስ እንደሚቻልም ገልፀዋል፡፡

የኢኮኖሚ ዕድገት የሚጀምረው እሴት በመፍጠር ነው የሚሉት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ በረከተአብ፣ አዳዲስ ድርጅቶች፣ አዳዲስ የምርት መስመሮች፣ አዳዲስ አገልግሎቶች እና ቴክኖሎጂዎች በፍጥነት፣ በጥራት፣ በማብዛት እና በመፍጠር መስራት ሲቻል ነው፡፡

ለአብነትም ፈጠራ የኢኮኖሚውን ምርታማ ድንበር ይጨምራል፤ የሥራ ዕድልን ያሰፋል፤ የዜጎችን የነፍስ ወከፍ ገቢ በመጨመር ምቹ ኑሮን እንዲያጣጥሙ ያደርጋል፤ ከዚህ ባሻገርም ከራስ ተርፎ ምርቶቻችንን በስፋት ለዓለም ገበያ አቅርበን የበለጠ ተጠቃሚ እንድንሆን ያደርጋልም ብለዋል፡፡

ፍጥነት ለሀገር የኢኮኖሚ ከፍታ አስፈላጊ ነው ስንል መንግሥት እና የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው ላይ የሚታዩ እንቅፋቶችን በመቅረፍ ምርትና ምርታማነትን ከፍ በማድረግ ፈጠራ ብቻውን እንዳይቆም ይልቅም እንዲበዛ ያደርጋል ሲሉም አክለዋል፡፡

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው እንደሚሉት መፍጠር፣ መፍጠን፣ ማብዛትና ማጥራትን በመጠቀም ሲንጋፖርን የመሳሰሉ ሀገራት በአጭር ጊዜ ውስጥ ዕድገታቸውን ማላቅና በዓለም ኢኮኖሚ ሚዛንም ከፍ ብለው መገኘት ችለዋል፡፡

የደቡብ ኮሪያ ተአምራዊ ዕድገትም በድንገት የተመዘገበ ሳይሆን እንደ ሀገር ያላቸውን ሁለንተናዊ አቅም በመፈተሽ፣ በተለይም የኢንደስትሪዎቿን ችግር በመቅረፍ አቅማቸውን በማላቅ እና የተትረፈረፈ ምርት እንዲያመርቱ በማበረታታት ነው፡፡ በመሆኑም ደቡብ ኮሪያ ያደገችው ብሔራዊ የኢንዱስትሪ አቅምን በማፋጠን፣ ፈጠራን በማብዛት፣ ምርትና ምርታማነትን በስፋት እና ጥራትን መሰረት አድርጎ በመስራት እንደሆነም የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ተናግረዋል፡፡

አፍሪካዊቷ ሀገር ሩዋንዳም፣ ከችግር በኋላ መፍጠን፣ መፍጠር፣ ማብዛትና ማጥራት በመቻሏ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከችግሮቿ ተላቅቃ የለውጥ ተምሳሌት መሆን እንደቻለችም ጠቅሰዋል፡፡

በመሆኑም ኢትዮጵያ በፈጠራ የታገዙ አዳዲስ የእድገት ሞተሮች ያስፈልጓታል፡፡ ምክንያቱም ካለው አቅም አንፃር ሲመዘን ዝቅተኛ ምርታማነት ያለው ግብርና፣ ውስን ማኑፋክቸሪንግ፣ ከውጭ በሚገቡ እቃዎች ላይ ጥገኛ መሆን፣ ከፍተኛ የወጣቶች ስራ አጥነት ስላለባት ይህንን ችግር በሚገባ ለመቅረፍ ግድ መፍጠር ይጠበቅብናል ብለዋል፡፡

በመሆኑም አዳዲስ ኢንዱስትሪዎች (ማኑፋክቸሪንግ፣ ዲጂታል ቴክኖሎጂ፣ የግብርና ማቀነባበሪያ)፣ አዳዲስ የኤክስፖርት ምርቶች፣ በገጠር እና በከተማ አካባቢዎች አዳዲስ ስራዎች፣ አዳዲስ የፈጠራ ማዕከላት እና የምርምር እና ልማት ማዕከላት፣ አዳዲስ ዘርፎችን መፍጠር፣ ማብዛት፣ ማጥራት እና መፍጠን እንዳለባትም ጠቁመዋል፡፡

ፍጥነት ለሀገር ኢኮኖሚ ከፍታ ያስፈልጋል ስንል ብዙ ተጨባች ምክንያቶች ስላሉን ነው የሚሉት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው፣ ለአብነትም ዓለም በከፍተኛ ፍጥነት በሚመራ የዕድገት መስመር ላይ በመሆኑ ተወዳዳሪ ለመሆን የግድ መፍጠን ይኖርብናል፡፡ በሌላ በኩል ከለውጡ ወዲህ የመጡና እየታዩ ያሉ ስኬቶች እንደተጠበቁ ሆኖ የዘገየ የፕሮጀክት ትግበራ፣ የቢሮክራሲያዊ እንቅፋቶች፣ የፋይናንስ ተደራሽነት ችግር፣ የኃይል እጥረት እና መሰል ችግሮች ይስተዋላሉ፤ በመሆኑም እነዚህን ችግሮች ለማስወገድ ፍጥነት የግድ ይለናል ብለዋል፡፡

“ኢኮኖሚያዊ አቅማችንንም ሆነ ሌሎች ዘርፎችን የበለጠ ለማላቅ ከኢትዮጵያ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ሀብቶች፣ ታሪካዊ ዕውነታዎች እና ያለፈው ትውልድ የከወናቸው የዕድገትና የአብሮነት እርሾዎችን ከግምት በማስገባት ከዓለም ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ አቅጣጫን መከተል ይገባል”

በሌላ በኩል ፍጥነት የልማት ፕሮጀክቶችን ወጪ ይቀንሳል፣ መንግስት በፍጥነት እርምጃ ሲወስድ ባለሀብቶች በራስ መተማመን ያገኛሉ፤ ፈጣን የመሠረተ ልማት ዕድገት ምርታማነትን ይጨምራል፤ ሰፋፊ የስራ ዕድልን መፍጠር እንደሚያስችልም ተናግረዋል፡፡

እንደ ሩዋንዳ፣ ቬትናም እና ደቡብ ኮሪያ ያሉ በፍጥነት የተንቀሳቀሱ ሀገራት ድህነትን በአጭር ጊዜ እያሸነፉ መምጣታቸውን የጠቀሱት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ በረከተአብ፣ ኢትዮጵያም የኢኮኖሚ ከፍታዋን በሚገባ ታረጋግጥ ዘንድ መፍጠን፣ መፍጠር፣ ፈጠራንም ማብዛት እና ያንንም በጥራት አልቆ መስራት ይኖርባታል ብለዋል፡፡

# በብዝሃነት የጎለበተ አንድነት

- **ኢትዮጵያውያን ከዓድዋ እስከ ሕዳሴው ግድብ ያሉ ድሎችን በአብሮነት እንዳሳኩት ሁሉ ለቀጣይ ሀገራዊ ድሎችም መተባበር እንዳለባቸው ተመላክቷል**

**በመለሰ ተሰጋ**

ዓድዋ ጥበብ ነው፤ የማይረሳ ታሪክ በሀገር ልጆች ጀግንነትና ጥበብ የተገለጠበት፣ ዓድዋ እውነት ነው፤ ውሸት በአደባባይ የተረታችበት፡፡ ዓድዋ አብሮነት ነው፤ ሁሉም ለሀገር ክብር በአንድነት የቆመበት፡፡ ዓድዋ ቅኔ ነው፤ ሰው ሞቶ ሰው ሊያድን ልክ እንደ ሰርገኛ ሆ! ብሎ የዘመተበት፡፡

የበርካታ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች መኖሪያ፣ የብዝሃ ቋንቋ፣ ባህልና መልክዓ ምድር ባለቤት የሆነችው ኢትዮጵያ ይህ ብዝሃነት ትልቅ ሀብት ሆኗት ዜጎቿ በመሰባሰብ የዓድዋን ድል ተጎናፅፈዋል፡፡ ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብም በጋራ ገንብተዋል። ወደፊትም እነዚህን አሰባሳቢና የወል ትርክት በማጉላት አንድነትን ማጠናከር ላይ አተኩሮ መስራት ይገባል፤ ይላሉ በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር ሳሙኤል ሺበሺ፡፡

በዓለማችን ይህን መሰል ብዝሃነት ያለባቸው ሀገራት ልዩነታቸውን በአንድነት አስተሳስረው በመያዛቸው ሁለንተናዊ ለውጥ ማስመዝገብ መቻላቸውን አውስተው፣ ለአብነትም ህንድን ምሳሌ በማድረግ ጠቅሰዋል።

“ህንድ በርካታ ብሔረሰቦችን፣ ቋንቋዎችና ባህሎችን የታደለች ሀገር ናት፡፡ ከፍተኛ የህዝብ ቁጥርም አላት፡፡ አልፎ አልፎ የእርስ በርስ አለመግባባቶች ቢኖሩም ከልዩነት ባሻገር አንድ የሚያደርጉ የወልና አሰባሳቢ ትርክትን በመገንባት ሀገራዊ አንድነቷን አጠናክራ መቀጠል ችላለች” ብለዋል፡፡

አክለውም፣ በህንድ ለሁሉም ብሔሮች፣ ዕምነቶች፣ ቋንቋዎች እና ባህሎች ክብርና እውቅና በመሰጠቱ በህንዳውያን ዘንድ ተከባብሮና አብሮ መኖር አንዱ እሴት ሆኖ እንዲቀጥል ማድረጓን ገልፀዋል፡፡

እንደ መምህር ሳሙኤል ገለፃ፣ አንዱ የሌላውን ባህልና ማንነት ማወቅና ማክበር፣ ከልዩነት ይልቅ ለአንድነት ከፍ ያለውን ዋጋ መስጠት እና በጋራ ትርክት ላይ ማተኮር አንዱ የህዝቦች ማሰባሰቢያና የጋራ ሀገርን መገንቢያ መንገድ ስለመሆኑም ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያም ሰፊ የተፈጥሮና ማህበራዊ ካፒታል የሆነ ድንቅ ብዝሃነት ያላት ሀገር ናት፡፡ ምንም እንኳን በየዘመናቱ የተወሰኑ መንሸራተቶች ቢኖርም እነዚህን የተፈጥሮ፣ ባህላዊ እና ኃይማኖታዊ ልዩነቶች አቻችሎ የመኖር ልምድ አለ። ለአብነትም እንግዳን ተቀብሎ መኝታን ሳይቀር ለቅቆ ማሳደር፣ ማብላትና ማጠጣት፣ ደስታና ሀዘንን እኩል ተጋርቶ ማሳለፍ የመሳሰሉ ባህሎች አሉ፡፡

ሊያስተሳስሩ የሚችሉ ነገሮችን እንደ ዕድል አለመጠቀም እንደ ሀገር አንዱ ማነቆ እንደሆነ የተናገሩት መምህር ሳሙኤል፣ አሁንም ቢሆን ኢትዮጵያውያንን በብርቱ ሊያስተሳስሩ የሚችሉ የወልና አሰባሳቢ ትርክት ገንብቶ እንደ ዓድዋ ለዓለም የሚበቃ፣ እንደ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብም ሀገርና አህጉርን የሚያነቃ፣ ብዙ ድሎችን በአብሮነት የምናስመዘግብባቸው ዕድሎች አሉ ብለዋል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ያለ ልዩነት ከሁሉም አቅጣጫ መጥተው የተሳተፉበትና መስዋዕትነት ከፍለው ያገኟቸው ድሎች በርካታ ናቸው

ከዘመናዊው ባሻገር በየአካባቢው ያሉ ባህላዊ የግጭት ማጥፊያ ጥበቦችን፣ የስራ ባህሎችን፣ የማህበራዊ መስተጋብርን፣ መረዳዳትን እና መጠያየቅን የሚያጎለብቱ እሴቶችን ለህብረ ብሔራዊነት መጎልበት፣ ለሀገራዊ ድልና ስኬቶች የበለጠ መጠቀም እንደሚገባም ገልፀዋል፡፡

መምህር ሳሙኤል፣ ልዩነትን ለመራራቂያ ሳይሆን ለውበት መጠቀም ላይ በሚገባ መስራት እንደሚገባ ገልፀው፣ ይህንንም ከቤተሰብ፣ ከአካባቢና ከትምህርት ቤት ጀምሮ ትውልዱ ላይ ወጥነትና ተከታታይነት ያላቸውን ተግባራት መከወን ያስፈልጋል። ከተናጠልና ከሀሰት ትርክት በመውጣት አስተሳሳሪ በሆኑት ላይ መስራት ይገባልም ብለዋል፡፡

እንደ ሀገር ከለውጡ ወዲህ የወልና አሰባሳቢ ትርክትን ለመገንባት እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት ተስፋ ሰጪ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ለአብነትም የዓድዋ ድል መታሰቢያ መገንባትን ማሳያ አድርገዋል። መታሰቢያው የወልና አሰባሳቢ ትርክትን ለመገንባት የሚደረገውን ጥረት የሚያግዝ ስለመሆኑም አንስተዋል፡፡

የወል ትርክት ለወል ሀገር አስፈላጊ መሆኑን የገለፁት መምህር ሳሙኤል፣ በሚያለያዩ ትርክቶች ላይ ከመጠመድ ይልቅ በሚያቀራርቡ ጉዳዮችና ሀገራዊ ተስፋዎች ላይ ማተኮር ለጋራ ሀገራዊ ዕጣ ፈንታችን ብሩህነት መሠረት ነው።

የወል እሳቤን ማደርጀት፣ ለወል ሀገር ግንባታ መሠረት በመሆኑ እንደ ዓድዋ ድል መታሰቢያ አይነት የእሴት ግንባታ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባውም ተናግረዋል፡፡

የወልና አሰባሳቢ ትርክትን ለመገንባት ከሚደረገው ጥረት ባልተናነሰ መልኩ አስተሳሳሪ እና ሁሉንም ማዕከል ያደረጉ ልማቶችም መገንባት እንዳለባቸው የገለፁት መምህሩ፣ እንደ ህዳሴው ግድብ የመሳሰሉ አስተሳሳሪ ልማቶችን አቅም በፈቀደ መልኩ መተግበር ሀገራዊ አንድነትን በፅኑ መሰረት ላይ ለመገንባት ትልቅ መሰረት የሚጥል ስለመሆኑም ጠቁመዋል፡፡

በሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ የታሪክና ቅርስ አስተዳደር ትምህርት ክፍል መምህር ተማም ሐጅአደም (ዶ/ር) ለአዲስ ልሳን ጋዜጣ እንደገለፁት ኢትዮጵያ ብዙ አሰባሳቢ ትርክት አሏት፡፡ ለአብነትም የዓድዋ ድል አንዱ ነው። በዚህ ዘመን ደግሞ እንደ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ አይነት ታላላቅ ፕሮጀክቶችን መጥቀስ እንችላለን ብለዋል፡፡

በተለይም የዓድዋ ድል የኢትዮጵያውያን አብሮነት ጎልቶ ከሚወሳባቸው የታሪክ ምዕራፎች መካከል አንዱ ነው ይላሉ ተማም ሐጅአደም (ዶ/ር) ምክንያቱን ሲያስረዱም፣ “የዓድዋ ድል ሁሉም የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች በእምነት፣ በባህል እና በቋንቋ ሳይለያዩ ከሁሉም አቅጣጫ መጥተው የተሳተፉበትና ታላቅ መስዋዕትነት ከፍለው ያገኙት ድል ነው። ድሉ ኢትዮጵያውያን ለጋራ ዓላማ የተነሱበትና ነፃነታቸውን ያስጠበቁበት ነው፡፡ የህዳሴው ግድብም የኢትዮጵያውያን ህብረት በተግባር የተገለፀበት ታላቅ ድል እንደሆነም አንስተዋል፡፡

የዓድዋ ድልም ሆነ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ህብረ ብሔራዊነት መገለጫችን፣ አብሮነታችን ያለውን ታላቅነት የሚያመላክቱ ናቸው። በተለይም የዓድዋ ድል ኢትዮጵያ በሁሉም ዜጎቿ ተጋድሎ የፀናች ሀገር መሆኗን መስካሪ ነው፡፡ የተማረው፣ ያልተማረው፣ ገበሬው፣ ወንድና ሴቱ.... ሁሉም የተሳተፉበት ነው፡፡ ይህም አንዱ ያለ ሌላው መኖር እንደማይችል የሚያሳይ ነው፡፡ ደስታና ድልን፣ ሀዘንና ችግርን በጋራ ተካፍሎ መቆምን የሚያሳይ ነው ብለዋል ተማም (ዶ/ር)፡፡

ዋና መስሪያ ቤቱን በአሜሪካ ያደረገውና በመላው ዓለም የተለያዩ የጥናት ውጤቶችን በማሳተም የሚታወቀው ካሪ ጆርናል “ለጋራ ድሎች ተገቢውን ዋጋ መስጠት ሀገራዊ አንድነትን ለማጠናከር ያለው ፋይዳ” በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ መጋቢት 27 ቀን 2023 ይፋ ባደረገው ጥናት መሰረት፣ ጥቂት የማይባሉ የዓለማችን ሀገራት ለጋራ ድሎቻቸው ቦታ በመስጠታቸው ጠንካራ ሀገር መገንባት ችለዋል፤ ንቁ ማህበረሰብ በመፍጠርም ኢኮኖሚያቸውን አሳድገዋል፡፡

እንደ ጥናቱ ከሆነ የጋራ ታሪክ ሀገራዊ አንድነትን ያሳድጋል፤ የጋራ ታሪካዊ ትውስታን በዜጎች ልቦና ውስጥ ያስቀምጣል፤ በህብረተሰብ መካከል ሰላማዊ ግንኙነትን በመፍጠር የሀገር ግንባታ ሂደትን ከፍ የሚያደርጉ ዜጎችን በማፍራት ረገድም ወሳኝ ሚና ይጫወታል።

ታሪክ በህብረተሰብ ዕድገት እና ውህደት መካከል አዎንታዊ ግንኙነት አለው። ይህንንም እውን ለማድረግ ያለፈው ትውልድ የገነባቸውን መልካም ታሪካዊ እሴቶች እና ቅርሶችን ማስተዋወቅ እንደሚገባ የታሪክ ምሁራን ይናገራሉ፡፡

በጥናቱ መሠረት፣ ወደፊት ለመራመድ ምርጡ መንገድ ታሪክን ወደ ኋላ መመልከት ነው። ታሪክ ህብረተሰቡ ከየት እንደመጣ፣ ያጋጠሙት ተግዳሮቶች ምን ምን እንደሆኑ፤ እነዚህንም ለመፍታት ምን አይነት ብልሃትን እንደተጠቀመ፣ የቱ እንደተሳካለት፣ የትኛው ለምን እንደከበደው በተጨባጭ የሚያስተምር ነው፡፡

ለጋራ ታሪክ የሚገባውን ክብር መስጠት በአንድ ሀገር የዜጎችን ንቃተ ህሊና ማዳበር፣ የሀገር ፍቅርን ከፍ ማድረግ፣ በጥቃቅን ጉዳዮች ሀገራዊ ዋልታዎችን የማይንድ ትውልድን መገንባት እንደሚቻል ከላይ በጠቀስነው ጥናታዊ ሰነድ ተመላክቷል፡፡ በዓለማችን ገናና ታሪክ ካላቸው ሀገራት መካከል ኢትዮጵያ ከቀዳሚዎቹ ተርታ እንደምትሰለፍ የታሪክ ድርሳናት ይመሰክራሉ።

ከቅርብ ጊዜ ታሪካችን አንድ እውነት ብንመዝዝ እንኳ ታላቁን የዓድዋ ድል እናገኛለን። የህዳሴውን ግድብ የመሳሰሉም በጋራ ቆመን ገድል ያስመዘገብንባቸው እና የህብረ ብሔራዊነታችን መገለጫ እና የአንድነታችን ፅኑ ማረጋገጫ የሆኑ መሰል ድሎች አሉን፡፡

ከዚህ ባሻገርም ሀዘንና ደስታችን በጋራ የምንካፈልባቸው ባህላዊ ክንዋኔዎች እና መሰል እሴቶች አሰባሳቢ ትርክትን ለመፍጠር እንደሚያግዙም ምሁራኑ ይናገራሉ፡፡

በርግጥም ኢትዮጵያ ድንቅ ነች፡፡ እንደ ዳሎል በፍፁም ትህትና ዝቅ ብላ ሁሉንም የምታከብር ደግሞም እንደ ዳሽን ተራራ ከፍ ብላ በኩራት የጀግንነቷን እና የነፃነት ተሟጋችነቷን የሚመሰክሩ ታሪኮቿን የምትናገር ቅኔ የሆነች ሀገር ናት፡፡

ደጋ፣ ወይና ደጋ፣ ቆላና በርሃ ልዩ ልዩ የአየር ንብረት ያለባት አይነግቡ ምድር፤ ጠይም፣ የቀይ ዳማው፣ ጥቁርና ቀዩ ሁሉም በየመልኩ የሚኖርባት ግሩም ሀገር መሆኗን ብዙዎች በየዘመናቱ ቢመሰክሩላትም ይህንን ሀብቷን በወጉ ገልጣ፣ አልምታና አስተዋውቃ በተገቢው አለመጠቀሟን እየጠቀሱም ብዙዎች ቁጭታቸውን ይሰነዝራሉ፡፡

የታሪክ ምሁራኑ ዓድዋ ሦስት አበይት ነገሮችን ያስተምረናል ይላሉ፡፡ ይሄውም ውስጣዊ አንድነትን ማጠናከር፣ ዘመኑ የሚፈልገውን ዕውቀትና ቴክኖሎጂ መታጠቅ እና ጠንካራ የዲፕሎማሲ ስራ መስራት እንደሆነም ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ የታሪክ ጉዞ እንደሚነግረን በዚህ ሀገር ታሪክ ከፍታ ውስጥ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በህብር የሚችለውን ጡብ ማስቀመጡን ያወሱት የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር ሳሙኤል ሺበሺ (ዶ/ር) ሁሌም የጋራ ለሆነው ድል በጋራ መቆም እና ለሀገር የሚጠቅሙና ዘመኑን የዋጁ ተጨማሪ ድሎችን ማስመዝገብ ያሻል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

# ለቤት ... ከገጽ 1 የዞረ

ይገነዘባል፡፡ ከተማዋ ለዚህ ሁሉ ወፌ ሰማይ ምቹ ብትሆንም የቤት ችግር ግን የነዋሪዎቿ ራስ ምታት ሆኖ ቀጥሏል፡፡

ከሰሞኑ በህዝብ አውቶቡስ ላይ ያስተዋልኩትን አንድ እውነት ላጫውታችሁ፡፡ ሁለት በዕድሜ ጠና ያሉ ሰዎች ስለ ቤት ችግር እያወጉ ነው፡፡ አንደኛው አዛውንት "እንዴት ሰው እግር የማታዘረጋ ቤት አስር ሺህ ብር ያከራያል! መውደቂያ ያጣው 'ልክፈል' ቢል እንኳ ህሊና እንዴት ችሎ ዝም ይላል" አሉ፤ ንዴትና ቁጭት ውስጣቸውን እንደናጠው ፊታቸው እያሳበቀባቸው፡፡ ሌላኛው ቀጠል አደረጉና "ለመረዳዳት፣ ለመተሳሰብ ችግራችንን በጋራ ለመካፈል የምንቆምበት የህሊና ምርኩዛችን ከተሰበረ ቆየ" ሲሉ ከኋላቸው የነበሩ ሌላኛው "ጎልማሳ ኧረ እንደቤተሰብ የሚያስቡ አከራዮችም አሉ!" በማለት ጨዋታውን ተቀላቀሉ፡፡ እኔ ግን የቤት ኪራይ ያማረራቸው አዛውንት የችግሩን ክብደት "የህሊና ምርኩዛችን ተሰበረ" በማለት የገለፁበትን መንገድ እያብሰለሰልኩ ወረድኩ፡፡

በእርግጥም የቤት ችግር ተከራዩን እጅጉን ያማረረ ጉዳይ ነው፡፡ መንግስት ችግሩን ለመቅረፍ በተለያዩ መርሃ ግብሮች ሰፊ ጥረት እያደረገ ቢሆንም የችግሩ ስፋት በሚጠይቀው ፍጥነትና ብዛት መጓዝ ባለመቻሉ የቤት እጥረት የከተማዋ ነዋሪዎች ቋሚና አንገብጋቢ ችግር ሆኖ ስለመቀጠሉ ምስክር አያሻውም፡፡

በእርግጥ የቤት ችግር የአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን ዓለም በእጅጉ እየተፈተነባቸው ካሉ ጉዳዮች አንዱ ስለመሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ለአብነትም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እ.ኤ.አ ጥቅምት 20 ቀን 2023 በኒው ዮርክ ከተማ ባደረገው ጠቅላላ ጉባኤ የቤት ችግር ማቃለል በሚቻልባቸው ዘዴዎችና አቅጣጫዎች ላይ ያተኮረ ሰፋ ያለ ጥናት በዘርፉ ባለሙያዎች ቀርቦ ነበር፡፡ በዚህ ጥናታዊ ሪፖርት መሰረትም በዓለማችን ቤት መስራት አሊያም መግዛት የማይችሉ ሰዎች ቁጥር እያሻቀበ ነው፡፡

ይህንንም ተከትሎ በዓለማችን በየቀኑ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች የመኖሪያ ቤት ወጪያቸውን መክፈል ባለመቻላቸው ብቻ ከቤት ንብረታቸው እንደሚፈናቀሉ፣ ይህም ለቤት እጦት መባባስ አስተዋጽኦ ስለማድረጉም በሪፖርቱ ተመላክቷል፡፡

በመሆኑም በዓለም ዙሪያ 1 ነጥብ 6 ቢሊዮን ህዝብ በቂ የመኖሪያ ቤት እና መሰረታዊ አገልግሎቶች እንደሌለው የጠቆመው ሪፖርቱ ይህም በ2030 ወደ 3 ቢሊዮን ሊደርስ እንደሚችል ተጠቁሟል፡፡

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ በቀረበው የባለሙያዎች ጥናታዊ ሪፖርት መሠረት፣ አስተዳደሮች፣ መንግሥታዊ ድርጅቶች እና ተቋማት የመኖሪያ ቤት እጥረትን ለመፍታት የበለጠ የተቀናጀ ጥረት ማድረግ አለባቸው፡፡

አዲስ አበባ ከተማም የተለያዩ የቤት



ፎቶ- ከገፀ ድር

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ለሀገራችን የመጀመሪያ በሆነው የግንባታ ቴክኖሎጂ 26 ሺህ ቤቶችን ስራ አስጀምረዋል

አማራጮችን ለነዋሪዎቿ በማመቻቸት የቤት ባለቤት እንዲሆኑ በማድረግ ላይ ናት፡፡ ይህንንም ተግባር የበለጠ በሚደግፍና ጥራትና ፍጥነት የታከለበትን የዘመኑን ቴክኖሎጂ በመጠቀም እንደ ሀገር አዲስ የሆነውን እና ዓለም በስፋት እየተጠቀመበት ያለውን ቴክኖሎጂ ይፋ አድርጋለች፡፡

ባሳለፍነው ሐሙስም (ህዳር 25 ቀን 2018 ዓ.ም) የ26 ሺህ ቤቶች ግንባታ ለሀገራችን የመጀመሪያ በሆነ የግንባታ ቴክኖሎጂ በላፍቶ ሳይት ስራ መጀመሩን የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ አብስረዋል፡፡

ከንቲባዋ ባስተላለፉት መልዕክት፣ በዚህ ዓመት ከያዝናቸው ዋነኛ እቅዶች መካከል ቀዳሚው ለከተማችን ነዋሪዎች የቤት አቅርቦትን ተደራሽ ማድረግ ነው ብለዋል።

በዚህ ዓመት ከ100 ሺህ በላይ ቤቶችን ለመገንባት አቅደን በርካታ ተግባራትን እያከናወንን ሲሆን፣ እቅዳችንን በጥራትና በፍጥነት እውን ለማድረግ ለሀገራችን የመጀመሪያ የሆነውን ኮልድ ፎርምድ እስቲል (ሲ.ኤ.ኤስ) የግንባታ ቴክኖሎጂን መጠቀም አንድ አማራጭ አድርገናል ብለዋል ከንቲባዋ፡፡

ይህ ቴክኖሎጂ በሌላው ዓለም የተለመደ ሲሆን፣ ህንፃዎችን በፋብሪካ ውስጥ የሚገጣጠሙ ብረቶችን በመጠቀም ወለልን፣ ግድግዳና ጣሪያን ጨምሮ ሁሉንም ክፍል በፍጥነትና በጥራት ማምረት የሚያስችል አሰራር ነው።

የቴክኖሎጂ ፋብሪካው በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ መተከሉን ገልፀው፣ በፈጠራና ፍጥነት መርህ ግንባታን ከሳይት ወደ ፋብሪካ በመቀየር የግንባታ ፍጥነትን በማሳደግ፣ ወጪን በመቀነስና ጥራትን ከማሻሻል አንጻር ተመራጭ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

አስተዳደሩ የነዋሪውን ጥያቄ ለመመለስ እና ተጠቃሚነቱን ለማረጋገጥ በጠንካራ የፕሮጀክት ማኔጅመንት፣ ዲስፕሊን እና በ24/7 የስራ መርሃ ግብር ፕሮጀክቱ በጥራትና በፍጥነት ተጠናቅቆ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል ያደርጋልም ብለዋል።

ዓለም የቤት ችግርን በፍጥነትና በጥራት ለመቅረፍ እየተጠቀመበት ያለውና አዲስ አበባ ለሀገራችን ያስተዋወቀችው ኮልድ ፎርምድ እስቲል (ሲ.ኤ.ኤስ) በፍጥነት በሚለዋወጠው የግንባታ ኢንዱስትሪ ውስጥ በቤት ገንቢዎች ዘንድ ተመራጭ እየሆነ መጥቷል።

ኮልድ ፎርምድ እስቲል (ሲ.ኤ.ኤስ) የላቀ ጥምረትና ጥንካሬ፣ ዘላቂነት ያለው፣ እሳትን በተሻለ መልኩ መቋቋም የሚችል፣ የመሬት መንቀጥቀጥ ክስተቶችን እና በአውሎ ንፋስ ምክንያት ሊመጣ የሚችልን ችግር መቋቋም የሚችል እና ቆሻሻን በእጅጉ የመቀነስ አቅም አለው ይላል የሳይቤሪያ ስቴት የኢንዱስትሪ ዩኒቨርሲቲ እ.ኤ.አ ሐምሌ 22 ቀን 2024 የኮልድ ፎርምድ እስቲል (ሲ.ኤ.ኤስ) ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች በሚል ርዕስ ይፋ ያደረገው መረጃ፡፡

ቴክኖሎጂው የስራ ጫናን ያቃልላል፣ ወጭን እና ብክነትን ይቀንሳል። ከህንፃ መረጃ ሞዴሊንግ እና ከኮምፒዩተር ዲዛይን ሶፍትዌር ጋር ያለምንም እንከን ይዋሃዳል፤ ይህም ውስብስብ የስነ ህንፃ መዋቅሮችን በትክክል ለማምረት ያስችላል።

ቴክኖሎጂው ሀብትን፣ ጊዜን እና ቦታን በአግባቡ መጠቀም ስለሚያስችል የሀገርን ኢኮኖሚ የመደገፍ አቅም አለው። ለአብነትም አስቀድሞ በፋብሪካ የተሰሩ የኮልድ ፎርምድ እስቲል (ሲ.ኤ.ኤስ) ክፍሎችን በግንባታ ቦታው ላይ ለመገጣጠም ዝግጁ ሆነው ይደርሳሉ፤ ይህም የሰው ኃይል ወጪን እና የቁሳቁስ ብክነትን ይቀንሳል።

ከእንጨት በተለየ መልኩ ኮልድ ፎርምድ እስቲል (ሲ.ኤ.ኤስ) ለማድረቅ ጊዜ አይፈልግም፤ በመበላሸት ወይም በተባይ ጉዳት ምክንያት ምንም ብክነት አያስከትልም፡፡ በሌላ በኩልም ለረጅም ጊዜ መቆየት ከመቻሉም በላይ ከፍተኛ ብክነትን ከሚያስከትሉት ኮንክሪት እና እንጨት በተቃራኒ ኮልድ ፎርምድ እስቲል (ሲ.ኤ.ኤስ) በጥቂት ጥገና ብቻ መቶ በመቶ እንደገና ጥቅም ላይ መዋል የሚችል ነው፡፡

ከእንጨት በተለየ መልኩ፣ ኮልድ ፎርምድ እስቲል (ሲ.ኤ.ኤስ) አይቃጠልም፣ አይበላሽም፣ አይበሰብስም፣ ምስጦችን አይስብም ይላል የሳይቤሪያ ስቴት የኢንዱስትሪ ዩኒቨርሲቲ የኮልድ ፎርምድ እስቲል (ሲ.ኤ.ኤስ) ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች በሚል ርዕስ ያሳተመው ፅሑፍ፡፡

በፅሑፉ በግልፅ እንደሰፈረው በዘመናዊ የግንባታ ሂደት ውስጥ፣ ዘላቂ፣ ሁለገብ እና ወጪ ቆጣቢ የሆኑ ቁሳቁሶች በጣም አስፈላጊ ናቸው፡፡ በዚህም ኮልድ ፎርምድ እስቲል (ሲ.ኤ.ኤስ) በዓለማችን ግንባታ አንዱስትሪ ውስጥ እጅጉን ተመራጭ እየሆነ መጥቷል፡፡

ከኮልድ ፎርምድ እስቲል (ሲ.ኤ.ኤስ) ዋና ዋና ጥቅሞች አንዱ አስደናቂ የጥንካሬ እና የክብደት ጥምርታው ነው። ቀላል ክብደት ያለው ቢሆንም በልዩ መዋቅር የተሰራ በመሆኑ ጥንካሬው አስተማማኝ ነው፡፡ በቀላል ክብደቱ ምክንያትም ለመያዝ እና ለማጓጓዝ አያስቸግርም፤ ይህም የማጓጓዣ ወጭን እና የቦታ አስተዳደርን ቀላል ያደርገዋል። በጥገና ምክንያት የሚባክን ጊዜና ገንዘብንም ይቀንሳል ይላል የዩኒቨርሲቲው ጥናታዊ ፅሑፍ።

የኮንስትራክሽን ኢንጅነዬር በሱፈቃድ አየለ እንደሚሉት ዓለም አቀፉ የግንባታ ዘርፍ ለከፍተኛ የኃይል ፍጆታ እና ከኃይል ጋር ለተያያዘ የካርቦን ዳይኦክሳይድ ልቀቶች ተጠያቂነትም፣ ኃላፊነትም አለበት፡፡ ይሁን እንጂ እንደ ኮልድ ፎርምድ እስቲል (ሲ.ኤ.ኤስ) ያሉ ከተፈጥሮ የሚስማሙ፣ ፈጣን፣ ወጭ ቆጣቢ እና አስተማማኝ ቴክኖሎጂዎችን ከመጠቀም አንፃር ክፍተት በመኖሩ በዘርፉ ችግሮች እንደሚስተዋሉ ጠቁመዋል፡፡

ዓለም በስፋት በተለይም ያደጉት ሀገራት እየተጠቀመበት ያለውን ኮልድ ፎርምድ እስቲል (ሲ.ኤ.ኤስ) ቴክኖሎጂን አዲስ አበባ መጠቀም መቻሏ ፋይዳው ብዙ ነው፡፡ ለአብነትም በከተማዋ የሚስተዋለውን የቤት አቅርቦት ችግር በፍጥነት፣ በጥራትና ሁለንተናዊ አስተማማኝነትን ባረጋገጠ መልኩ ችግሮቹን በሂደት መፍታት ያስችላል፡፡

ለሀገራችን የመጀመሪያ የሆነው ይህ ቴክኖሎጅ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ዓለም ከደረሰበት የቴክኖሎጅ ምጥቀት ጋር በማስታረቅ፣ የጊዜን እና የገንዘብን ብክነትን በመቀነስ ይባክኑ የነበሩ ሀብቶቻችንን በሌሎች ልማቶች ላይ በማዋል የሀገርን ከፍታ ማፋጠን ያስችላል፡፡

በተለይም ኢትዮጵያ በስፋት እየሰራችበት ካለው እና ዓለም አቀፍ ዕውቅናን ካስገኘላት የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ወይም በከተማ እና በገጠር መልክዓ ምድሮች ላይ ችግኞችን በመትከል ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ደህንነትን እና ሥነ-ምህዳርን በማሻሻል የኢትዮጵያን ዘላቂ ልማት ማሳደግን መሰረት ካደረገው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ጋር የሚጣጣም በመሆኑ ኮልድ ፎርምድ እስቲል (ሲ.ኤ.ኤስ) ፋይዳው ከቤት አቅርቦትም በላይ መሆኑን የኮንስትራክሽን ኢንጅነዬሩ ገልፀዋል፡፡

## የፌዴራሊዝም ... ከገጽ 1 የዞረ

ተከብሮ እና የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸው ተረጋግጦ መኖር የሚችሉበት ስርዓት ይፈጠር ዘንድ በተለያዩ ጊዜያት ትግል ሲካሄድ እንደነበር በፌዴራሊዝምና በመንግስታት ግንኙነት ዙሪያ የተለያዩ ጥናትና ምርምሮችን ያደረጉትና በአሁኑ ወቅት የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ምክትል ኃላፊ ሆነው በማገልገል ላይ የሚገኙት አቶ በላይ ወዲሻ ይናገራሉ፡፡

በኢትዮጵያ ከ1960ዎቹ የተማሪዎች ንቅናቄ ጀምሮ ሲነሱ የነበሩ ጥያቄዎች በዋናነት ሶስት ናቸው፤ የብሔር፣ የመሬት እና የዴሞክራሲ፡፡ የንጉሱን ስርዓት በተካው የደርግ መንግስት የመሬት ላራሹ ጥያቄ ምላሽ ቢያገኝም የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ራስን በራስ የማስተዳደር እና የዴሞክራሲ ጥያቄዎች ሳይመለሱ ነበር የቀጠሉት፡፡ በዚህ ምክንያት ለአስራ ሰባት ዓመታት ሀገሪቱ በዕርስ በዕርስ ጦርነትና ውድመት እንድትቆይ አድርጓል፡፡ በ1983 ዓ.ም የመጣውን የመንግስት ለውጥ ተከትሎ ብዝሃነትን ለማስተናገድ፣ ፍትሀዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመፍጠር ኢትዮጵያ የፌዴራል ስርዓትን መከተል እንደጀመረች አቶ በላይ ይገልፃሉ፡፡

"ከ1983 ዓ.ም በፊት የነበረው አስተዳደር ማዕከላዊና ብዝሃ ማንነትን የማያስተናግድ በመሆኑ ምክንያት ግጭትና ጦርነት ፈጥሮ፣ የሀገር አንድነትና ቀጣይነት ስጋት ውስጥ ወድቆ ነበር" የሚሉት በሃረማያ ዩኒቨርሲቲ የህግ ኮሌጅ የፌዴራሊዝምና ህገ መንግስት መምህር ሱልጣን ቃሲም፤ የፌዴራል ስርዓትን ሀገራት እንደየራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ ተግባራዊ ያደርጉታል፡፡ በኢትዮጵያ መተግበር ያስፈለገበት ምክንያትም ብዝሃነትን በአግባቡ ለማስተናገድና ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በመንግስት አስተዳደር ስርዓት ውስጥ ፍትሀዊ ውክልና ማግኘት እንዲችሉ ታስቦ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ የፌዴራሊዝም ስርዓትን መከተል ከጀመረች ከሶስት አስርት ዓመታት በላይ ጊዜያት ተቆጥረዋል፡፡ በእነዚህ ዓመታት በስርዓቱ መተግበር ምን ትሩፋት ተገኘ? ክፍተቶችስ ምንድን ነበሩ? ጠንካራ ህብረ ብሔራዊ አንድነት ያለው ሀገር ለመፍጠር ምን መሰራት አለበት? የሚለውን እንደሚከተለው ዳስሰነዋል፡፡

### የፌዴራሊዝም ስርዓቱ ትሩፋት

ኢትዮጵያ የፌዴራሊዝም ስርዓትን መከተል ከጀመረች በኋላ በተለያየ መልኩ የሚገለፁ መልካም ውጤቶች መገኘታቸውን የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ። የፌዴራሊዝም ምሁሩ ሱልጣን እንደሚሉት፣ "ይህ ስርዓት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ማንነታቸው እንዲታወቅና እንዲከበር ያደረገ፣ ቋንቋቸውን፣ ባህላቸውን፣ ታሪካቸውን... የሚያዳብሩበትን ምቹ ሁኔታ የፈጠረ በመሆኑ፣ ሀገሪቱን ሊበታትን የሚችል ግጭትና ጦርነት ጋብ እንዲል አድርጓል።"

ለረጅም ጊዜ 'መብታችን አልተከበረም፤ ማንነታችን እውቅና አላገኘም' በሚል የጠመንጃ ትግል በማድረግ እስከ መገንጠል ጥያቄ የሚያነሱ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች እንደነበሩ



ፎቶ በገነት ወንድሙ

የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ምክትል ኃላፊ አቶ በላይ ወዲሻ

**ኢትዮጵያ የፌዴራል ስርዓትን መከተል ከጀመረች በኋላ በተለያየ መልኩ የሚገለፁ መልካም ውጤቶች ተገኝተዋል**

የሚያነሱት የፌዴራሊዝም ምሁሩ ሱልጣን፣ በፌዴራሊዝም ስርዓቱ ምክንያት እነዚህ ህዝቦች በኢትዮጵያ ማዕቀፍ ውስጥ መኖር እንደሚችሉ ማመን የቻሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ "የፌዴራሊዝም ስርዓቱ ሀገርን ሊበትን ይችል ለነበረ የፖለቲካ ጥያቄ መልስ በመስጠት ለሀገር አንድነትና ቀጣይነት አስተዋፅኦ አድርጓል" ይላሉ፡፡

የፌዴሬሽን ምክር ቤት ምክትል ጽህፈት ቤት ኃላፊው አቶ በላይ፣ በፌዴራሊዝም ስርዓቱ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ራስን በራስ የማስተዳደር፣ ቋንቋ፣ ባህልና ታሪካቸውን የመጠቀም፣ የማሳወቅና የማሳደግ መብት አግኝተዋል፡፡ በፌዴሬሽን ምክር ቤት እውቅና ያገኙ 76 ብሔሮችና ብሔረሰቦች በኢትዮጵያ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ህዝቦች ከዓመታት በፊት እርስ በርሳቸው አይተዋወቁም ነበር፡፡ በ"ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን" እና በተለያዩ መድረኮች አንድ ላይ ተሰባስበው ባህል፣ ታሪክና ወጋቸውን የሚያሳዩበት፣ እርስ በርስ የሚተዋወቁበት፣ ባህላቸውን የሚለዋወጡበት፤ በመካከላቸው መከባበር፣ ትስስርና አንድነት የሚጠናከርበት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል። በአካል ብቻ ሳይሆን በመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት ባህላቸውን፣ ታሪካቸውን፣ እሴቶቻቸውን የሚያሳዩበትና የሚሸጡበት ዕድል ማግኘት ችለዋል።

ይህም ኢትዮጵያውያን፣ 'ኢትዮጵያ ብዝሃነት ያለባት ሀገር' መሆኗን እንዲያውቁ፣ መከባበርና አንድነት እንዲጠናከር ዕድል መፍጠሩ የፌዴራሊዝም ስርዓቱ ሌላኛው ትሩፋት ተደርጎ የሚወሰድ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ሌላኛው ያስገኘው ትሩፋት ከኢኮኖሚ ጋር እንደሚያያዝ የፌዴራሊዝም ምሁሩ ሱልጣን ያነሳሉ፡፡ "ስርዓቱ በተበታተነ ትናንሽ ሀገር ከመኖር ይልቅ በአንድ ትልቅ ሀገር የጋራ የኢኮኖሚ ማህበረሰብን መገንባት ዓላማ አድርጎ የተነሳ በመሆኑ ትልቅ ገበያ መፍጠር አስችሏል፡፡ ክልሎች ከክልሎች፣ እንደሀገር ከጎረቤት ሀገራት ጋር ሰፊ የሆነ ገበያ ማካሄድ የሚቻልበትን መሰረት ጥሏል፡፡" ሰፊ ገበያና ሰፊ ሀገርን ማስቀጠል መቻሉ ደግሞ ጠንካራ ኢኮኖሚ ለመፍጠር እንደሚያግዝ ያብራራሉ፡፡

የፌዴሬሽን ምክር ቤት ምክትል ጽህፈት ቤት ኃላፊው አቶ በላይ እንዲሁ የፌዴራሊዝም ስርዓቱ ልማትን በማፋጠን አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ስርዓት ለመፍጠር የሚደረገውን ጥረት እያገዘ እንደሚገኝ ያነሳሉ፡፡ ለምሳሌ ብዙዎቹ በክልል የሚገኙ ስታዲየሞች፣ አዳራሾች፣ ሆቴሎች፣ የመንገድ፣ ውሃ፣ መብራትና ሌሎች የከተማ ልማቶች የተሰሩት የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን ምክንያት በማድረግ ነው።

ለምሳሌ፦ ዘንድሮ በሀገር አቀፍ ደረጃ በዓሉ በሚከበርባት ሆሳዕና ከተማ፣ ሁለት ወር ባልሞላ ጊዜ አንድ ስታዲዮም ገንብቶ መጨረስ የተቻለበት ሁኔታ መፈጠሩን በማሳያነት ጠቅሰዋል፡፡

### ያጋጠሙ ክፍተቶች፣ ማስተካከያዎችና ቀጣይ መፍትሔዎች

ከፌዴራሊዝም ስርዓቱ አተገባበር ጋር በተያያዘ ባለፉት ዓመታት የተለያዩ ክፍተቶች እንዳሉ ሲነገር ይደመጣል፡፡ አንዳንዶች ስርዓቱን ከአወቃቀሩ ጀምሮ 'ብሔርና ቋንቋ ማዕከል ያደረገ ነው' የሚል ትችት ያቀርባሉ፡፡ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ምክትል ኃላፊ አቶ በላይ ይህንን ሀሳብ አይቀበሉትም፡፡ "የፌዴራሊዝም ስርዓቱ ህብረ ብሔራዊ አወቃቀርን የተከተለ ነው፡፡ አንዳንዶች 'የጎሳ፣ የብሔር ነው' ይላሉ፡፡ ነገር ግን ብሔርን ብቻ መሰረት አድርጎ የተዋቀረ አይደለም፤ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 39፣ 46 እና 47 ላይ ብናይ ክልሎች የሚዋቀሩት ምክንያት ተመሳሳይ የሆነ ሥነ- ልቦና፣ መልክአምድራዊ አቀማመጥ፣ ኩታገጠምነት፣ ቋንቋና ባህል፣ በአንድ ክልል የመደራጀት ፈቃደኝነት ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ነው፡፡" በማለት ያብራራሉ፡፡

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

**ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ የሚቀርብ**

# የአስተዳደራዊ ውሳኔዎች

## ክፍል አንድ

ጌታነህ በላይ (ዐቃቤ ህግ)

የኢትዮጵያ የአስተዳደር ህግ ባለፉት ዓመታት በአስተዳደር አካላት የሚወሰኑ ውሳኔዎችን ለመቆጣጠር በሚያስችሉ የሥነ ሥርዓት ህጎች ረገድ ከፍተኛ ክፍተት ነበረበት። ይህ ክፍተት የተቋማት አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን ያለአግባብ እንዲጠቀሙበት ዕድል በመስጠት ለአስተዳደራዊ ፍትሕ መጓደል ምክንያት ሆኗል። የፌዴራል አስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 ይህንን ችግር ለመቅረፍ ወጥቷል፡፡ ይህ ህግ በአስተዳደራዊ እርምጃዎች ውስጥ የሥነ ሥርዓት ህጋዊነትን፣ ግልጽነትን እና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ወሳኝ ምዕራፍ ከፍቷል። ይህ አዋጅ ዜጎች መብቶቻቸውን በሚነኩ የአስተዳደር ውሳኔዎች ላይ ሕጋዊ ምላሽና ጥበቃ የሚያገኙበትን መደበኛ መንገድ ይዘረጋል።

### የአስተዳደር ውሳኔ ምንነት እና የተፈጻሚነት ወሰን

"የአስተዳደር ውሳኔ" ማለት የአስተዳደር ተቋም በዕለት ተዕለት ሥራው ውስጥ በሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ የሚሰጠው ውሳኔ ሲሆን፣ መመሪያ ማውጣትን ግን አይጨምርም። "የአስተዳደር ተቋም" ማለት በሕግ የተቋቋመ የፌዴራል ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ አስፈጻሚ አካል ሲሆን፤ ለፌዴራል መንግሥት ተጠሪ የሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደርን ያጠቃልላል።

አዋጁ በሁሉም የፌዴራል አስተዳደር ተቋማት ላይ ተፈፃሚነት ያለው ሲሆን፣ ጥቂት የማይካተቱ ጉዳዮች አሉ። ከነዚህም መካከል ዐቃቤ ሕግና ፖሊስ በወንጀል ሥነ ሥርዓት ህጉ የሚመሩ ተግባራትን ሲያከናውኑ፣ እንዲሁም የመከላከያና የደህንነት ተቋማት ዋና ኃላፊነታቸውን ሲያከናውኑ አይተገበርም። ሆኖም፣ እነዚህ የተገለሉ ተቋማት ከዋና ኃላፊነታቸው ጎን ለጎን አገልግሎት ሲሰጡ ወይም የቁጥጥር ሥራዎችን ሲሰሩ አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን ሲወስኑ፣ በዚሁ አዋጅ ሥር ተገዢ ይሆናሉ።

### 1. አስተዳደራዊ ውሳኔ አጀማመር፤ ጥያቄ ማቅረብና የአስተዳደር ግዴታዎች

#### 1.1. የአስተዳደራዊ ውሳኔ አጀማመር ሁኔታና ጥያቄ የማቅረብ መብት

የአስተዳደር ውሳኔ የሚጀመረው በሁለት ዋና ዋና መንገዶች ነው። አንደኛው፣ ውሳኔው በሚመለከተው የአስተዳደር ተቋም በራሱ አነሳሽነት ሊጀመር የሚችል ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በሚመለከተው ሰው ወይም በወኪሉ ሊቀርብ የሚችል ነው፡፡

#### 1.2. የአስተዳደር አካል የሚቀርብለትን ጥያቄውን የመቀበልና ማስረጃ መስጠት



የአስተዳደር ውሳኔ ጥያቄ በጽሑፍ መቅረብ አለበት። የጽሑፍ ማመልከቻው በአካል፣ በምዝገባ ፖስታ አድራሻ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መንገዶች ሊቀርብ ይችላል። ይህ የኤሌክትሮኒክስ አማራጭ መካተቱ መደበኛ የሆነውን የጽሑፍ ሰነድ አስፈላጊነት ከመጠበቅ ጎን ለጎን ተደራሽነትና ቅልጥፍና ያሳድገዋል።

ማመልከቻው በዝርዝር መረጃዎችን ማካተት ይኖርበታል። ይህም ቀን፣ የጠያቂው ወይም ወኪሉ ስም፣ ፊርማና አድራሻ፣ አቤቱታው የቀረበለት የአስተዳደር ተቋም ስም፣ አስተዳደራዊ አካሉ ሊፈጽመው የሚገባውን ተግባር፣ እና ለውሳኔው አስፈላጊ የሆኑትን ማብራሪያና ማስረጃዎች ማካተት አለበት። ተቋማት ይህን ሂደት ለማቅለል የቅጽ ማመልከቻዎችን ሊያዘጋጁ ይችላሉ። ዜጋው እውነታዎችን እና ማስረጃዎችን እንዲያቀርብ መጠየቁ በአስተዳደር ሂደት ላይ ትልቅ ኃላፊነት ከመጣል ባሻገር፣ ሂደቱ በዘፈቀደ ሳይሆን በሰነድና በእውነታ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ያስገድዳል። ይህም ወደፊት የፍርድ ቤት ክለሳ ቢፈለግ እንኳን የአስተዳደር ሰነዱ ቀድሞ እንዲደራጅ ይረዳል።

### 2. የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት፣ መርሆዎችና የሚፈጽመው አካል

#### 2.1. የአስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ መርሆዎችና ግዴታዎች

የአዋጁ ዋና ዓላማ አስተዳደራዊ ፍትህ ማስፈን ሲሆን፤ ለዚህም የሚያግዙ የአስተዳደር አካላት የውሳኔ አሰጣጥን የሚመሩት ዋና ዋና መርሆዎች ፍትሐዊነትን፣ ግልጸኝነት እና ገለልተኝነትን ያጠቃልላሉ።

የመጀመሪያውና ዋነኛው መርህ የመስማት መብት ነው፡፡ ይህም ውሳኔው መብቱን ወይም ጥቅሙን ሊነካው የሚችለውን ማንኛውንም ሰው ሃሳቡን የመግለጽ ዕድል የመስጠት ግዴታን ያካትታል፡፡

ሁለተኛው መርህ ግልጽነትና ተጠያቂነት ሲሆን፣ ውሳኔዎች በግልጽ እና በሚገባ በተረጋገጡ ምክንያቶች ላይ መመሥረታቸውን ያረጋግጣል። በተጨማሪም ፍትሐዊነትና እኩልነት ተመሳሳይ የሆኑ ጉዳዮች ወጥ የሆነ አያያዝ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

ሶስተኛው መርህ ደግሞ የአግባብነት መርህ ሲሆን፣ የግልና የህዝብ ጥቅም ማመዛዘን፣ ተቋሙ የሚወስደው እርምጃ የተፈለገውን ሕጋዊ ዓላማ ለማሳካት ወይም በህግ ከተሰጠው ስልጣን በላይ መሆን እንደሌለበት ይደነግጋል፡፡

#### 2.2. የአስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ግዴታዎች እና ልዩ ሁኔታዎች

የአስተዳደር ውሳኔ ሰጪው ሰው በተገቢው ጊዜ ውስጥ ውሳኔውን ያለመዘግየት የመስጠት ግዴታ አለበት። ይህም በውሳኔው የተጎዳው ጥቅሙ በመዘግየቱ ምክንያት አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳይደርስበት ያረጋግጣል ።

ከዚህ በተጨማሪ ተቋሙ ተገቢ በሆነ ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት ካልቻለ ይህ ጥያቄው ውድቅ እንደሆነ በመቁጠር የአስተዳደር አካል ዝምታን ወደ ፍርድ ቤት እንዲሄድ በማድረግ የዜጎችን ፍትሕ የማግኘት መብት ያጠናክራል።

**"የአስተዳደር ውሳኔ" ማለት የአስተዳደር ተቋም በዕለት ተዕለት ሥራው ውስጥ በሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ የሚሰጠው ውሳኔ ነው**

#### 2.3. የአስተዳደር ውሳኔ የሚፈፅመው ሰው እና ውሳኔ ከመስጠት የሚነሳበት ሁኔታ

በህጉ አስተዳደራዊ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን የተሰጠው አካል የአስተዳደር ተቋሙ ኃላፊ፣ የስራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ነው።

ውሳኔ አሰጣጡ ፍትሐዊ እንዲሆን ውሳኔ ሰጪው አካል ገለልተኛ መሆን አለበት። በመሆኑም ማንኛውም ውሳኔ ሰጪ አካል በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ከመስጠት እንዲነሳ የሚያደርጉ ምክንያቶች በህጉ ላይ በዝርዝር የተቀመጡ ናቸው፡፡

እነዚህም በጉዳዩ ላይ ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅም ያለው ከሆነ፤ ጉዳዩ ከውሳኔ ሰጪው ጋር የዝምድና ወይም የጋብቻ ግንኙነት ያለውን ወይም የቅርብ ወዳጁን የሚመለከት ከሆነ፤ ወይም ጠበቃ ወይም በሌላ ሙያዊ አቅም ውሳኔ ለሚሰጥበት ሰው ውክልና ሰጥቶ ከነበረ፤ ወይም በጉዳዩ ላይ በሌላ ሥልጣን ቀደም ብሎ ውሳኔ ሰጥቶ ከሆነ ከሂደቱ መገለል አለበት።

ይህን ጥያቄ በሰራተኛ አነሳሽነት ወይም ጉዳዩ በሚመለከተው ሰው አመልካችነት ውሳኔ ከመስጠት እንዲነሳ ሊያመለክት የሚችል ሲሆን፤ ሠራተኛውም የተቋሙ ኃላፊ የመጨረሻ ውሳኔ በ5 ቀን ውስጥ እስከሚሰጥ ድረስ ውሳኔ ከመስጠት ሂደቱ ታግዶ ይቆያል፡፡

ይህ መርህ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ከአድልዎ የጸዱና በሥርዓት የተጠበቁ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

#### 2.4. ውሳኔውን ለተገልጋይ ስለማሳወቅ

የአስተዳደር ተቋሙ ውሳኔውን ለሚመለከተው ሰው ወዲያውኑ በጽሑፍ የማሳወቅ መሠረታዊ ግዴታ አለበት። ለተገልጋዩ በሚሰጠው ጽሑፍ ላይም የውሳኔውን ምክንያቶች በግልጽ ማካተት አለበት። ለተጠያቂነት ሲባል የውሳኔው ዝርዝር ይዘት የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡- የውሳኔው ቀንና ቁጥር፣ የስልጣን አካሉ ስም፣ የጉዳዩ ተከራካሪ ወገኖችና አድራሻዎቻቸው፣ የይገባኛል ጥያቄው ማስረጃዎች የታዩበት ሁኔታ፣ የፍሬ ነገር እና የህግ ጉዳዮችን እንዲሁም የተሰጠው የመጨረሻ ውሳኔን ያካተተ መሆን አለበት።

አንባቢዎቻችን ክፍል ሁለትን በሚቀጥለው ሳምንት ይዘን እንቀርባለን።

# “የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ቀንን ስናከብር ትኩረታችን የወል ትርክትን ማስረጽ መሆን አለበት”

**የሕገ-መንግስት እና ፌዴራሊዝም አስተምህሮ ማዕከል ዋና ዳይሬክተር ኃይለየሱስ ታዬ (ዶ/ር)**



ፎቶ ከገፀ ድር

የሕገ-መንግስት እና ፌዴራሊዝም አስተምህሮ ማዕከል ዋና ዳይሬክተር ኃይለየሱስ ታዬ (ዶ/ር)

**በሄለን ጥላሁን**

የኢትዮጵያውያንን አብሮነት በተጠናከረ መልኩ ለማስቀጠል መሰራት ካለባቸው የቤት ስራዎች መካከል የወል ትርክት ግንባታ አንዱ ነው:: ይህን ማድረግ የሚያስችሉ መልካም አጋጣሚዎችን በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል:: የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን ዘንድሮ ለ20ኛ ግዜ ይከበራል:: ቀኑን ለወል ትርክት ግንባታ አጋዥ በሆነ መልኩ ለማክበር መስራት ያስፈልጋል::

## የመጣንበት መንገድና ውስንነቶቹ

የሕገ-መንግስት እና ፌዴራሊዝም አስተምህሮ ማዕከል ዋና ዳይሬክተር ኃይለየሱስ ታዬ (ዶ/ር) ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት ማብራሪያ፣ ከዚህ ቀደም የነበረው ስርዓት ነጠላ ትርክት ላይ መሰረቱን የጣለ አካሄድ ይከተል ነበር:: በነበረው ሂደት የተፈጠረው ትልቁ ችግር ብዝሃነትን በአግባቡ ማስኬድ አለመቻሉ ነበር:: ብዝሃነት በውስጡ የብሔር፣ የቋንቋ፣ የኃይማኖትና መሰል ጥብቅ ጉዳዮቻችንን የሚይዝ ነው:: ይህንን በአግባቡ አስተናግደናል ብሎ ለማለት አያስደፍርም::

ብዝሃነትን ለማስተናገድ የግድ መሬት ላይ ወርዶ ተፈፃሚነትን ያተረፈ የአሰራር ስርዓት መከተል ያስፈልጋል:: በኢትዮጵያ ከለውጡ በፊት ይስተዋል የነበረውን ነጠላ ትርክትን በማረቅ የወል ትርክትን ለማስረጽ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ቀን መከበር ጉልህ ፋይዳ እንዳለው አስታውቀዋል::

እንደ ኃይለየሱስ (ዶ/ር) ገለፃ፤ ብዝሃነታችን የህብረ ብሔራዊነታችን መገለጫ ሆኖ ሳለ ያስተናገድንበት መንገድ ግን ነጠላ ትርክትን በሚያሰርፅ አግባብ ነበር:: ወደራስ ያተኮረ የብሔር ማንነት ላይ ብቻ ትኩረቱን በማድረግ ነጣጣይ ትርክት ላይ ያተኩር ነበር:: ከጊዜ ቆይታ በኋላም በጋራ አብሮነታችን ላይ ጫና በመፍጠሩ ምክንያት ዋጋ የከፈልንባቸው ነገሮች አሉ::

“ነጠላ ትርክት ሀገር በሁለት እግሯ እንዳትቆም ያደርጋል” የሚሉት ኃይለየሱስ (ዶ/ር)፣ “የፌዴራል ስርዓቱ ተመሰረተ፣ ህገ መንግስቱ ወጣ፣ ክልሎች ተደራጁ” ይባል እንጂ ከዚያ ያለፈ አተገባበሩ ላይ የተጨነቀ አልነበረም:: የፌዴራል ስርዓት ፍልስፍናው አብሮነት ስለመሆኑ ተገቢውን መረዳት ማህበረሰቡ ዘንድ እንዳልነበረ አስረድተዋል::

ቀደም ሲል በነበረው ስርዓት በየጊዜው ለሚነሱ ጥያቄዎችና ችግሮች ከስር ከስር መፍትሔ ከማበጀት ይልቅ አድበስብሶ እና ትኩረት በመንፈግ ሂደቶችን እንደ አስፈላጊነታቸው ያስቀጥል ነበር:: የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦችን ህብረ ብሔራዊነት ለማስጠበቅ የተዘጋጁ ማስፈፀሚያ መመሪያና ህጎችን በአግባቡ ተፈፃሚ ለማድረግ የተሰራ ስራ አለመኖሩን ጭምር ኃይለየሱስ (ዶ/ር) ገልፀዋል:: በተለይም የፌዴራል ስርዓቱ

> **“ህብረ ብሔራዊነት ብሎም አንድነት ላይ መሰረቱን የጣለ የፌዴራሊዝም ስርዓት በአግባቡ መሬት ላይ እንዲተገበር የሚቀረጹ መልዕክቶች ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል”**

በራሱ የተገነባበት ትርክት አስቸጋሪ የነበረ ሲሆን እርስ በእርስ የሚያጋጭ፣ የሚበታትን ሴራን መሰረት ያደረገ እና ሀገርን ከማቅናት ህዝቦችን ከማወዳጀት ይልቅ ትኩረቱን ነጠላ ትርክት ላይ ያጠነጠነ ነበር:: የብሔሮች ፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ቀን በሚል የተለያዩ መልዕክቶች ተቀርፀው ይከበራሉ:: መልዕክቶቹ በትክክል ዓላማቸው ምን እንደሆኑና ለምን እንደሚከበሩ በግልፅነት የተቀመጠ ነገር አልነበራቸውም ሲሉም አክለዋል::

## ማህበረሰቡ በዓሉን የተረዳበት መንገድ

የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ቀን ከዚህ ቀደም ይከበር የነበረበት አግባብ ብሔርተኛነትን በማጉላት አንደኛውን ብሔር ከሌላኛው ጋር የሚያራርቅ ነበር የሚሉት በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሶስት ነዋሪ አቶ ሃይሉ ጉተማ ናቸው። የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ቀን ተብሎ ይከበር እንጂ እርስ በእርስ ያለንን ህብረ ብሔራዊነት ከማንጸባረቅ ይልቅ ግለኝነትን በሚያዳብር ተግባራት የታጀበ እንደነበር አስታውሰዋል:: ሀገራዊ ለውጡ ህብረ ብሔራዊነትን ያስከበረ፣ የብሔረሰቦችን ማንነት ከፍ ያደረገ እና አንዱን ከአንዱ እኩል ለማስተናገድ የሚያስችል የፌደራሊዝም ስርዓት ማስፈን ያስቻለ ብሎም የጋራ ትርክታችን ላይ ትኩረት እንድናደርግ መንገዱን ያሳየ ነው ሲሉ ሃሳባቸውን አጋርተዋል::

ወይዘሮ ትነበብ ንጉሴ ይባላሉ። ነዋሪነታቸው በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 ነው:: ከለውጡ በፊት በነበረው ስርዓት በህገ መንግስት ደረጃ የጸደቁ መመሪያዎች እና ደንቦች በርካታ ቢሆኑም ከተፈፃሚነታቸውና በአግባቡ መሬት ላይ ወርደው ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር ከፍተኛ ክፍተት እንደነበር አስታውሰዋል:: ላለፉት በርካታ ዓመታት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በአይነ ቁራኛ እንዲተያዩ፣ አንዱ የአንዱ ጠላት እንደሆነ እንዲያስብ ተደርጎ ነበር:: በዚህም ምክንያት የጋራ ትርክት ላይ መሰረቱን የጣለ ስራ እንዳይሰራ እንቅፋት ሆኖ መቆየቱን አስረድተዋል::

እንደ ወይዘሮ ትነበብ ገለፃ፤ ከለውጡ ማግስት የተናጥል ትርክትን ወደ ወል ትርክት ለማምጣት የሚያስችሉ በርካታ ስራዎች እየተሰሩ ነው:: በዚህም እኛ ኢትዮጵያውያን በህብረ ብሔራዊነታችን ውስጥ ያለውን የደመቀ ማንነታችንን ለወል ትርክት ማጠናከሪያነት መጠቀም ይኖርብናል ሲሉ ሃሳባቸውን አጋርተውናል::

በፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ምክትል ኃላፊ አቶ በላይ ወዲሾ ህዳር 29 የሚከበረውን 20ኛው የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ቀንን አስመልክቶ ከአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ጋር ቆይታ ባደረጉበት ወቅት፣ በኢትዮጵያ ከለውጡ በፊት ይስተዋል የነበረውን የነጠላ ትርክትን በማረቅ የወል ትርክትን ለማስረጽ የቀኑ መከበር ጉልህ ፋይዳ እንዳለው አስታውቀዋል:: ኢትዮጵያ የፌዴራል ሥርዓትን መከተል ከጀመረች ከሰላሳ ዓመት በላይ ያስቆጠረች ቢሆንም በብሔር ማንነት፣ በባህልና በቋንቋ ላይ ትኩረት ያደረገና ነጠላ ትርክትን የሚያጎላ እንደነበር አስታውሰዋል።

እንደ አቶ በላይ ገለፃ፤ በዓሉ በሕዝቦች መካከል ሀገራዊ መግባባት እንዲፈጠር፣ ዲሞክራሲያዊ አንድነት እንዲጠናከር እና ህብረ ብሔራዊ አንድነት እንዲጎለብት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል:: 20ኛው የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ቀን በዓል በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሆሳዕና ከተማ ህዳር 29 ቀን 2018 ዓ.ም “ዴሞክራሲያዊ መግባባት ለህብረ ብሔራዊ አንድነት” በሚል መሪ ሀሳብ ይከበራል::

## ለወል ትርክት ግንባታ ምን መንገድ እንከተል?

የጋራ ጉዳያችን በፌዴራል ስርዓት እሳቤ ሲመነዘር የወል የሚያደርጉን ጉዳዮች ጎልተው እንዲወጡ ማስቻል እንደሆነ የሚናገሩት ኃይለየሱስ (ዶ/ር)፣ የህብረ ብሔራዊነታችን መገለጫዎች በርካታ ናቸው:: በህብረት ስንሆን እንዋባለን፤ ጠላት የማይደፍረን ብርቱ የታሪክ ባለቤቶች እንድንሆን ያደርገናል:: የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ቀን በሚከበርበት ወቅት አንዱ የአንዱን የአኗኗር ዘይቤ በመረዳት ብሎም በማክበር የሚያጋምደንን ፍቅር በማጎልበት የወል ትርክት ባለቤቶች እንድንሆን ያደርገናል ሲሉ ተናግረዋል::

እንደ ኃይለየሱስ (ዶ/ር) ገለፃ፤ ሀገራችን በተፈጥሮ ሃብት እጅግ የታደለች፣ በርካታ ቁጥር ያለው የሰው ሃይል ያላት አቅሟን በበርካታ መንገድ ስንፈትሸው የያዘቸው መንገድ አዋጭ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል:: እነዚህ አቅሞች የወል ትርክታችን እንዲሆኑ ማድረግ ድህነትን የማሸነፍ ሙሉ አቅም ለመፍጠር ያስችለናል::

ህብረ ብሔራዊነት ብሎም አንድነት ላይ መሰረቱን የጣለ የፌዴራሊዝም ስርዓት በአግባቡ መሬት ላይ እንዲተገበር የሚቀረጹ መልዕክቶች ላይ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ኃይለየሱስ (ዶ/ር) አስታውቀዋል:: ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ቀንን ስናከብር የመርሃ ግብሮች ማጠንጠኛ የወል ትርክት ማስረጽ መሆን አለበት:: በተጨማሪም መልዕክቱን ተደራሽ ለምናደርገው አካል ተገቢውን የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች መስራት ያስፈልጋል:: በዚህ መሰረት በህገ መንግስትና በፌዴራሊዝም ስርዓት ዙሪያ ግንዛቤ የመፍጠሪያ መድረኮች ተዘጋጅተው ቀደም ብሎ እውቀቱን እንዲገኝ የማድረግ ስራ እየተሰራ ይገኛል። የአመለካከት ችግር ከመቅረፍ አንፃርም ሰፊ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛል::

እንደ ኃይለየሱስ (ዶ/ር) ገለፃ፣ ከአንድ ወር በፊት በህገ መንግስትና በፌዴራሊዝም ስርዓት ዙሪያ የአሰልጣኞች ስልጠናዎችን እየሰጠን እንገኛለን:: ከዚህ በተጨማሪም ብሔር ብሔረሰቦች ሲገናኙ ስለራሳቸው ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ስለ ጋራ ጉዳያቸው ጭምር እንዲወያዩ ማስቻል ላይ በትኩረት እየተሰራ ይገኛል:: ስያሜ የተሰጣቸው አምስቱ ቀናትን በተመለከተ ከህዳር 25 እስከ 29 ድረስ የወንድማማቾች ቀን፣ የአብሮነት ቀን፣ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ቀን፣ የምክክር ቀን፣ የኢትዮጵያውያን ቀን በሚል በድምቀት እየተከበሩ መሆኑን አስታውቀዋል::

# የአንድ ጀምበር ፍሬዎች

**“የአንድ ጀምበር የስራ ዕድል ፈጠራው የነዋሪዎችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በቁርጠኝነት እየሰራን እንደሆነ ትልቅ ማሳያ ነው”**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ**

- **ከጥገኝነት ለመላቀቅና ለሌሎች ወገኖች የስራ ዕድል ለመፍጠር እንደሚያግዛቸው የስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ወጣቶችና ሴቶች ገልጸዋል**

**በስንታየሁ ምትኩ**

ወጣት እስማኤል ሀሺም በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 2 ነዋሪ ነው፡፡ ኑሮውን ለመምራት በታክሲ ረዳትነት፣ በሹፍርና እና ሌሎች የስራ መስኮች ሲሰራ እንደነበር ያነሳል። ነገር ግን ስራው ቀጣይነት የሌለው መሆኑና በራሱ ለመስራት በመፈለጉ ከጓደኞቹ ጋር በመሆን በወተት ከብት እርባታ ተደራጅተውና ስልጠና ወስደው የመስሪያ ቦታ እንዲሰጣቸው ሲጠባበቁ መቆየታቸውን ይናገራል፡፡

በአንድ ጀምበር የስራ ዕድል ፈጠራ ንቅናቄም፣ ወጣት እስማኤል እሱን ጨምሮ አምስት ሆነው ተደራጅተው ወደ ስራ ለመግባት የሚያስፈልጋቸውን 60 ካሬ ሜትር ስፋት ያለው የመስሪያ ቦታ ተሰጥቷቸዋል፡፡ የ“እስማኤል፣ ሱለምና ጓደኞቻቸው የወተት ከብት እርባታ ህብረት ሽርክና ማህበር” ስራ አስኪያጅ የሆነው ወጣት እስማኤል፤ ስራ የሚጀምሩበት ሁኔታ ስለተፈጠረላቸው በጣም ደስተኛ መሆኑን ተናግሯል፡፡

“ስንጠብቀው የነበረ ዕድል ነው። የተደረገልን የመስሪያ ቦታ ድጋፍ ለስራችን ትልቅ ዋጋ ያለው ነው። በዚህ ዘርፍ የመስሪያ ቦታ ከሌለ ምንም መስራት አይቻልም፡፡” ሲልም ወደ ስራ እንዲገቡ ከተማ አስተዳደሩ ላደረገው ድጋፍ ምስጋናውን አቅርቧል። እስማኤል በማብራሪያው፣ “በቀጣይም የሚያስፈልጋቸውን የብድር፣ የሙያና ሌሎች ድጋፎች እንደሚደረጉላቸው ቃል ተገብቶልናል፡፡ ወደፊትም በወተት ከብት እርባታ እና በወተት ማቀነባበር ላይ በሰፊው በመስራት ለበርካታ ወገኖች የስራ ዕድል የመፍጠር ህልም አለን” ብሏል፡፡

ሌላኛዋ የስራ ዕድል የተፈጠረላት ወጣት ትዕግስት ይመር ትባላለች። በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ነዋሪ ናት፡፡ ትምህርቷን እስከ አስረኛ ክፍል ድረስ ተከታትላለች፡፡ በትምህርት ለመቀጠል ፍላጎት ቢኖራትም ውጤት ሊመጣላት ባለመቻሉ፤ ከቤተሰቦቿ ጋር ሆና መስተንግዶና ፅዳትን ጨምሮ የተገኘውን እየሰራች ነበር የምትኖረው፡፡ ከዚህ ባሻገር የስራ ዕድል እንዲፈጠርላት በምትኖርበት አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 አስተዳደር በስራ ፈላጊነት ተመዝግባ መቆየቷን ትናገራለች፡፡

በአንድ ጀምበር የስራ ዕድል ፈጠራ ከሶስት ጓደኞቿ ጋር በመሆን በሻይና ቡና ንግድ ወይም “ቡና ጠጡ” በመደራጀት ስራ መጀመራቸውን አክላለች፡፡ የስራ ዕድል ስለተፈጠረላት ደስተኛ መሆኗን በመናገርም፣ ወደፊት ስራውን በማስፋት ለሌሎች ወገኖችም የስራ ዕድል የመፍጠር ህልም እንዳላቸው አክላለች፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በከተማዋ ለስራ ፈላጊ ወጣቶችና ሴቶች የስራ ዕድል ለመፍጠር ልዩ ትኩረት በመስጠት እየሰራ ይገኛል፡፡ ሐምሌ 24 ቀን 2018 ዓ.ም በአንድ ጀምበር ለ30 ሺህ



ፎቶ- ከገፀ ድር

የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ከተማ አስተዳደሩ በአንድ ጀምበር የስራ እድል የፈጠረላቸውን ወጣቶችና ሴቶች ስራ ሲያስጀምሩ

የከተማዋ ወጣቶችና ሴቶች የስራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡ የስራ ዕድል የተፈጠረባቸው ዘርፎችም በአገልግሎት 13 ሺህ 637፣ በኮንስትራክሽን 7 ሺህ 781፣ በከተማ ግብርና 5 ሺህ 256፣ በማኑፋክቸሪንግ 2 ሺህ 359 እንዲሁም በንግድ 967 ዜጎች ናቸው፡፡

በአንድ ጀምበር የስራ ዕድል ፈጠራ መድረክ ላይ የተገኙት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ እንደተናገሩት፣ የስራ ዕድል የተፈጠረላቸውና ወደ ስራ የገቡት ቀደም ሲል የከተማ አስተዳደሩ ከነዋሪዎች ጋር ባካሄዳቸው የተለያዩ መድረኮች “የስራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው” ጥያቄ ሲያነሱ የነበሩ ወጣቶችና ሴቶች ናቸው። አስተዳደሩ በክህሎትና በእውቀት የበለፀገ፣ ጠንካራ ሞራልና ስነ ምግባር ያለው እንዲሁም ችግር ፈቺ የሆነ ትውልድ ለመፍጠር እየሰራ ይገኛል፡፡ በገበያው በሰለጠነ የሰው ሀይል ፍላጎትና አቅርቦት መካከል ያለውን ክፍተት ለመሙላትም በርካታ ወጣቶች አጫጭር ስልጠና እንዲወስዱ፣ የክህሎትና ሙያ ባለቤት እና በኢኮኖሚው ውስጥ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

“ትናንትና ስራ በመምረጥና ያለንን እምቅ አቅም በተሟላ ሁኔታ ባለመጠቀማችን የምንፈልገው የእድገት ደረጃ ላይ ሳንደርስ ቆይተናል፡፡” ያሉት ከንቲባ አዳነች አቤቤ፣ ነገ የተሻለ ይሆን ዘንድ የስራ ባህልን በማሳደግ፣ በፍጥነት እና በጥራት መስራትን መርህ በማድረግ እየተሰራ እንደሚገኝ ጠቁመዋል፡፡

“ለ30 ሺህ ዜጎች በአንድ ጀምበር የስራ እድል መፍጠርና ስምሪት ማድረግ የነዋሪዎችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በቁርጠኝነት እየሰራን እንደሆነ ትልቅ ማሳያ ነው” ያሉት ከንቲባ አዳነች፤ በዕለቱ በከተማ ግብርና፣ ማኑፋክቸሪንግ፣ ኮንስትራክሽን፣ ንግድና አገልግሎት የስራ ዘርፎች ለስራ ፈላጊዎች የስራ ዕድል መፈጠሩን ተናግረዋል፡፡

“ወደ ስራ የገቡ ወጣቶችና ሴቶች ከፊታቸው የሚያጋጥማቸውን ፈተና ለማለፍ በርትተው መስራት ይገባቸዋል፤ የከተማ አስተዳደሩ ከጎናቸው በመሆን ድጋፍ ያደርጋል፡፡ በስፋት እየተተገበረ ያለው የአንድ ጀምበር የስራ ዕድል ፈጠራ ንቅናቄም በቀጣይነት በልዩ ትኩረት ተጠናክሮ ይቀጥላል” ሲሉም ከንቲባ አዳነች አክለዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የስራና ክህሎት ቢሮ ኃላፊ አቶ ሚሊዮን ማቴዎስ በበኩላቸው፣ በመዲናዋ በ2018 በጀት ዓመት ለ350 ሺህ ዜጎች በቋሚነት የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ እየተሰራ የሚገኝ ሲሆን በአራት ወራት ጊዜ ውስጥ ለ158 ሺህ 138 ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡ ይህም በእቅድ ከተያዘው አኳያ 97 በመቶ ድርሻ እንዳለው ተናግረዋል፡፡

ለዜጎቹ የስራ ዕድል የሚፈጠረው በተለያዩ አማራጮች ነው፡፡ ከቅጥር ባለፈ በተለያዩ ዘርፎች ስራ ፈላጊዎች እንዲደራጁ በማድረግ በአራት ወራት ውስጥ 40 ሺህ 71 አንቀሳቃሾች ያላቸው 7 ሺህ 591 ኢንተርፕራይዞችን በማደራጀት ወደ ስራ ማስገባት ተችሏል፡፡ ለኢንተርፕራይዞቹም የብድር፣ የመስሪያና መሸጫ ቦታ፣ የማሽን አቅርቦትና የገበያ ትስስር ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡ በአንድ ጀምበር የስራ ዕድል የተፈጠረላቸው 30 ሺህ ዜጎችም ውጤታማ እንዲሆኑ አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚደረግላቸው አቶ ሚሊዮን ተናግረዋል፡፡

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ኪሩቤል ሰለሞን ለዝግጅት ክፍላችን እንደተናገሩት፣ በአዲስ አበባ በአንድ ጀምበር ሰፊ የስራ እድል መፈጠሩ የከተማ አስተዳደሩና ከንቲባዋ ለወጣቶችና ሴቶች የሰጡትን ትኩረት ያሳያል፡፡ የወጣቶችን የስራ አጥነት ችግር ለመቅረፍ ከተማ አስተዳደሩ የጀመራቸው የአንድ ጀምበር የስራ ዕድል ፈጠራ ተነሳሽነት ይበል የሚያሰኝና ቀጣይነት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡

እንደ ባለሙያው ገለጻ፣ የስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ወጣቶችና ሴቶች በስራቸው ውጤታማ እንዲሆኑ፣ ወደ ቀጣይ የእድገት ደረጃ እንዲሸጋገሩ፣ ወደ ባለሀብትነት አድገው ከራሳቸው ባለፈ ለሌሎችም ወገኖች የስራ እድል መፍጠር እንዲችሉ ተከታታይነት ያለው ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ስራቸውን ሲያከናወኑ የሚገጥሟቸውን ችግሮች ማለፍ እንዲችሉ የቅርብ ድጋፍና ክትትል ማድረግ ይጠበቃል፡፡

አዲስ ወደ ስራ የሚገቡ ስራ ፈጣሪዎች (ኢንተርፕርነሮች) ወደ ስራው ዓለም ሲገቡ የቢዝነስ አመራር ችግር፣ የፋይናንስ እጥረት፣ በቁርጠኝነት አለመስራት፣ የገበያ ትስስርና መሰል ፈተናዎች ሊያጋጥሟቸው እንደሚችሉና እነዚህን ችግሮች ለማለፍ ከመንግስትና ከራሳቸው ከኢንተርፕርነሮች ብዙ ስራ እንደሚጠበቅ አቶ ኪሩቤል አንስተዋል፡፡

ኢንተርፕራይዞች የማምረቻ ዋጋ በመቀነስ፣ ብዙ ምርት በጥራት በማቅረብ በገበያው ተወዳዳሪ ለመሆን መስራት ይጠበቅባቸዋል። መንግስት ኢንተርፕራይዞች ውጤታማ እንዲሆኑ በቅርብ ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግላቸው ይገባል። በተሰማሩበት ዘርፍ ውጤታማ ለሆኑ ኢንተርፕራይዞች እውቅና እና ማበረታቻ መስጠት፣ በየእድገት ደረጃቸው ሊያገኙት የሚገባውን ድጋፍ ማቅረብና ሌሎች ደግሞ ከእነዚህ ተሞክሮ እንዲወስዱ በማድረግ መስራት እንደሚገባ አያይዘው ያነሳሉ፡፡

ከገበያ ትስስር ጋር በተያያዘ ኢንተርፕራይዞች በጥራት ማምረት ከቻሉ ገበያው ውስጥ መግባት ያን ያህል ሊያሳስባቸው እንደማይገባ የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ተናግረዋል። ለምሳሌ፡- የኮንስትራክሽን ዘርፍ ላይ የተደራጁ ኢንተርፕራይዞች በከተማዋ ካለው ሰፊና ፈጣን የግንባታ እንቅስቃሴ አኳያ ገበያ ማግኘት አይቸግራቸውም። በከተማ ግብርና ዘርፍም በዶሮ እርባታ፣ ወተት፣ የጓሮ አትክልት ልማትና ሌሎችም ስራዎች የሚሰማሩት በደንብ ማምረት ከቻሉ ገበያው ውስጥ መግባት ይችላሉ። በዋናነት በአነስተኛ የማምረቻ ዋጋ በማምረት ቀድሞው ገበያው ውስጥ ካሉት ጋር ተወዳዳሪ ለመሆን መትጋትና በርትተው መስራት ይኖርባቸዋል፡፡

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ኪሩቤል እንደገለፁት፣ በከተማዋ የስራ ዕድል ፈጠራውን ለማሳደግ በርካታ የስራ ዕድል መፍጠር የሚችሉ የኢንዱስትሪ ዘርፎችን በመለየት ድጋፍና ማበረታቻ ማድረግ ይገባል፡፡ አዲስ አበባ ትልቅና ፈጣን እድገት እያስመዘገበች ያለች ከተማ ናት። የከተማ አስተዳደሩ በርካታ ተቋማት አሉት፤ ሰፊ መንግስታዊ አገልግሎትም ይሰጣል፡፡ ከዚህ አኳያ በከተማዋ ያለውን የስራ አጥነት ችግር ለመቅረፍ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በመተንተንና ጥናቶችን በማካሄድ መፍትሔዎችን ማመላከት ይቻላል፡፡ ብዙ መቅጠር የሚችሉ ተቋማት ወይም ድርጅቶች እነማን ናቸው? ምን ድጋፍ ቢደረግላቸው አቅማቸውን ማሳደግ ይቻላል የሚለውን በመለየት መስራት ይገባል፡፡

# የኪነ ጥበብ ጥቁምታ

**በጊዜው አማረ**

በመዲናችን አዲስ አበባ ባሳለፍነው ሳምንት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች እና አዳዲስ ጥበባዊ ስራዎች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል፡፡ ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናት የተለያዩ ጥበባዊ መሰናዶዎች ይደረጋሉ፡፡ ከተሰናዱ ዋና ዋና ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች መካከል የንባብ አውደ ርዕይ፣የህጻናት ፌስቲቫል፣ የሥዕል አውደ ርዕይ፣ የቴአትር መርሃ ግብር እና ሌሎች መሰናዶዎች ይገኙበታል፡፡ ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡




ፎቶ- ከገፀ ድር

በመዲናዋ ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

### የንባብ ፌስቲቫል

በአዲስ አበባ የተለያዩ ቦታዎች “አዲስ ሊትሬቸር ፌስቲቫል” የተሰኘ የኪነ ጥበብ ዝግጅት እየተካሄደ ነው፡፡ አዲስ ሊትሬቸር ፌስቲቫል ባሳለፍነው ማክሰኞ ተጀምሯል፡፡ በመርሃ ግብሩ ላይ የኪነ ጥበብ ፣ የውይይት እና የመጽሐፍ አውደ ርዕይ እና ሌሎች ፕሮግራሞች እየተካሄዱ ነው፡፡ በዛሬው እለትም በአዲስ አበባ የባህል ማዕከል ዝክረ ሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድህንን ጨምሮ ሌሎችም ዝግጅቶች ከ3፡00 ጀምሮ ይካሄዳሉ፡፡ በነገው እለትም የንባብ ውይይት፣ የመጽሐፍ ሽያጭ፣ ከደራሲዎች ጋር የመገናኘትና መጽሐፍ የማስፈረም ዝግጅት እንደሚኖር ተገልጿል፡፡

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን 75ኛ ዓመት በዓል ምክንያት በማድረግ “Ignite Your Love For Words!” በሚል መሪ ቃል ያዘጋጀው አዲስ ሊትሬቸር ፌስቲቫል ከህዳር 23 ቀን 2018 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ ስፍራዎች እየተሰናዳ ሲሆን እስከ ታህሣሥ 5 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ ይቆያል፡፡

### የህጻናት ዝግጅት

በዛሬው እለት ህጻናትን እያዝናና የሚያስተምር መርሃ ግብር ይካሄዳል። መርሃ ግብሩ የተዘጋጀው ዓለም አቀፍ የሕፃናት ቀን መነሻ በማድረግ ሲሆን፤ በወመዘክር አዳራሽ ይካሄዳል፡፡ በመርሃ ግብሩ ላይ የአዋቂዎች ምክር፣ የህጻናት የባህል ባንድ፣የመጽሐፍ ስጦታ፣ የህጻናት ግጥምና መዝሙርን ጨምሮ ሌሎችም እያዝናኑ ቁምነገር የሚያስጨብጡ መርሃ ግብሮች ይከናወናሉ ተብሏል፡፡ ዝግጅቱ ከ3፡00 ጀምሮ እንደሚካሄድም አዘጋጆቹ አሳውቀዋል፡፡

### ሥዕል

‘አብሮነት’ የሥዕል አውደርዕይ በመጪው ሰኞ ይጠናቀቃል፡፡ ሰዓሊያን በጋራ ሆነው ያሰናዱት የሥዕል አውደርዕይ አብሮነትና ህብረትን የሚያሳዩ የሥዕል ስራዎች የቀረቡበት ነው፡፡ የስዕል አውደርዕዩ በመጪው ሰኞ ይጠናቀቃል፡፡ በአውደርዕዩ ላይ የሥዕል ሥራዎቻቸውን ካቀረቡ ሰዓሊያን መካከል ብሩ ወርቁ፣ ያሬድ ወንድወሰንና ዘውዱ ገብረሚካኤል ይገኙበታል፡፡ የስዕል አውደርዕዩ መስቀል አደባባይ አጠገብ በሚገኘው በሃያት ሬጀንሲ ሆቴል ውስጥ ባለው በፈንደቃ የባህል ማዕከል ውስጥ እየታየ ይገኛል፡፡

### ፊልም

“ፀሐይ” የተሰኘው ፊልም በትናንትናው እለት ተመረቀ፡፡ የአምሃ ድጉማ አዲስ ፊልም ትናንት ሕዳር 26 ቀን 2018 ዓ.ም በአዲሱ የሕፃናትና ወጣቶች ቴአትር አዳራሽ ተመርቋል፡፡ በቀይ ምንጣፍ ስሥነ ስርዓት ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች፣ የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች እና የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች በተገኙበት ተመርቋል፡፡ ፀሐይ ፊልም ዛሬ እና ነገም በተመረጡ ሲኒማ ቤቶች በታላቅ ድምቀት ይመረቃል ተብሏል።

### ሙዚቃ

“አመል ነው” የተሰኘው የማኪ ኬቢ ሙዚቃ ለአድማጭ ተመልካች ይፋ ሆነ፡፡ ከዚህ ቀደሞ (ደነገጠ፣ በሕልሜ ነው፣ አሜሪካ፣ ከረሜላ፣ እዩልኝ እና አልወድም) በተሠኙ ስራዎች የምትታወቀው ሙዚቀኛ ማኪ ኬቢ አሁንም “አመል ነው” ቆንጆ ሙዚቃ ሰርታለች፡፡ ሙዚቃው በትናንትናው እለት በሆፕ ኢንተርቴይንመንት አማካኝነት ለአድማጭ ተመልካች ይፋ ሆኗል፡፡ የሙዚቃው የዜማ ደራሲ ብስራት ሱራፌል ሲሆን ገጣሚው ፍሬዘር አበበወርቅ ነው፡፡

### የቴአትር መርሃ ግብር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሑድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ። በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ቅዳሜ ሁለት ቴአትሮች ለእይታ ይበቃሉ። ቀን 8፡30 ሰዓት ላይ 12ቱ እንግዶች እንዲሁም፣ 11፡30 ሰዓት ባሎችና ሚስቶች ለእይታ ይበቃል፡፡ እሁድ በ8፡30 ሰዓት ንጉሥ አርማህ ቴአትር፣ እንዲሁም እምዩ ብረቷ የተሰኘው ቴአትር ደግሞ በ11፡30 ሰዓት ላይ ይታያሉ፡፡ በዚሁ በብሔራዊ ቴአትር በሌሎች ቀናት ማክሰኞ 11፡30 ሰዓት ሶስቱ አይጦች፣ ረቡዕ በ11፡30 ሰዓት የቅርብ ሩቅ፣ ሐሙስ በ11፡30 ሰዓት ሸምጋይ እንዲሁም አርብ በተመሳሳይ ሰዓት ዴጊያ የተሰኙ ቴአትሮች ለእይታ ይቀርባሉ፡፡

## የቁጥር ጨዋታ

### የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ የመጀመሪያው ክብ 3x21= 63 ይሆናል፡፡ የ63 ግልባጭ 36 ይሆናል። እንዲሁም 9x7= 63 ሲሆን፤ ግልባጩ 36 ነው፡፡ በዚህ አመክንዮ (ሎጂክ) መሰረት የሶስተኛው ክብ ሂሳባዊ አሰራር 8x12= 96 ግልባጩ 69 እንዲሁም 3x32= 96 ግልባጩ 69 ይሆናል፡፡ ስለዚህ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛ ቁጥር **69** ነው፡፡




### የዚህ ሳምንት የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት እትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



ኢኮኖሚ

# ለቱሪዝሙ መልካም እድል የፈጠረው በዓል

- የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች መከበር የቱሪዝም ፀጋዎች እንዲተዋወቁ ዕድል እንደሚሰጥ ተገልጿል



ፎቶ- ከፋይል
የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የቱሪዝም ጸጋዎች በጥቂቱ

በሄለን ጥላሁን

ከአዲስ አበባ በ2 መቶ 30 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ ወይን አደጋ የአየር ንብረት አላት፡፡ የመሬት አቀማመጧ ሜዳማና ተዳፋታማ ነው፡፡ ይህች ከተማ ሆሳዕና ናት፡፡ 20ኛውን የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን በዓል በድምቀት ለማክበርና እንግዶቿን ተቀብላ ለማስተናገድ ሽር ጉድ በማለት ላይ ትገኛለች፡፡ የዝግጅት ክፍላችንም ይህን መነሻ በማድረግ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በዓል መከበር የቱሪስት መስህቦችን በአግባቡ እንዲተዋወቁ በማድረግ ረገድ ያለው አበርክቶ ምን እንደሚመስል ለመቃኘት ወድዷል፡፡

## እየተደረገ ያለው ዝግጅት

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ምክትል ኃላፊ እና የኮሙኒኬሽንና የሚድያ ግንኙነት ዘርፍ ኃላፊ አቶ አብድልባር ኡስማን በጉዳዩ ዙሪያ ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት ማብራሪያ፣ የለውጡ ትሩፋት በሆነው በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ውስጥ ያሉ የቱሪዝም ፀጋዎች በርካታ ናቸው፡፡ እንደነዚህ ያሉ በዓላት መከበራቸው ለክልሉ የበለጠ መነቃቃትን እንደሚፈጥር ተናግረዋል፡፡ ቱሪዝም አንዱ የኢኮኖሚ ሴክተር መሆኑን ተከትሎ ለክልላችን ከሚያስገኘው ገቢ ባሻገር በጥቅል ሀገራዊ ኢኮኖሚው ላይ ትልቅ አሻራ ያኖራል ሲሉም አክለዋል፡፡

እንደ አቶ አብድልባር ገለፃ፤ በተፈጥሮ ሃብቶቿ የማትታማው የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በወንዞቿ፣ በተራሮቿ፣ በፏፏቴዎቿ እንዲሁም ሰው ሰራሽ መስህቦቿ የበርካቶችን ቀልብ መሳብ ከጀመረች ቆይታለች፡፡ 20ኛውን የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን በዓል ለማክበር የሚታደሙ እንግዶችን ለማስተናገድ በጉጉት እየጠበቀች እንደሆነም ምክትል ቢሮ ኃላፊው ገልፀዋል፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ ተጨማሪ ሃሳባቸውን ያጋሩን ከፍተኛ የቱሪዝም ተመራማሪ እና መምህር አያሌው ሲሳይ (ዶ/ር) ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት አስተያየት፣ 20ኛውን የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን በሆሳዕና ከተማ እንዲካሄድ መደረጉ በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ፀጋዎች ጎልተው እንዲወጡ ብሎም እንዲታወቁ በር ይከፍታል ብለዋል፡፡

እንደ አያሌው (ዶ/ር) ገለጻ፣ በክልሉ የሚገኙ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ቅርሶችን ለመጎብኘት የሚመጡ እንግዶች በተቻለ መጠን የመሰረተ ልማት ጥያቄ ሊኖርባቸው አይገባም፡፡ በተለይ አስጎብኚዎች የተለያዩ መርሃ ግብሮችን በማዘጋጀት ክልሉ ላይ የሚገኙ ፀጋዎችን አንድ ሁለት ብለው ማስጎብኘት ይጠበቅባቸዋል። ሆቴሎችም ቢሆኑ ጥራት ያለው አገልግሎት ከሙሉ መስተንግዶ ጋር ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

አቶ አብድልባርም በበኩላቸው፤ 20ኛውን የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀንን ለማክበር ቁጥራቸው እስከ 50 ሺህ የሚጠጉ እንግዶች ከውጭ እንዲሁም ከሀገር ውስጥ ይመጣሉ ተብሎ ይጠበቃል። ለሁሉም እንግዶች በቂ ማረፊያዎች ስለመዘጋጀቱ እንዲሁም በቂ የሆነ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ባሶች ከሆቴሎች ወደ ፕሮግራሙ የሚካሄድባቸው ስፍራዎች እንግዶችን ለማመላለስ ተዘጋጅተዋል፡፡ ከተሞቻችን የብልፅግና ተምሳሌት እንዲሆኑ የልማት ስራዎችን በተፋጠነ መንገድ በመስራት የአመራር ትኩረትና ክትትልን ከአዲስ የስራ ባህል ጋር አወዳጅቶ እየተሰራ ይገኛል ብለዋል፡፡

በዓሉን በድምቀት ለማክበር ዝግጅት ከተጀመረ አንድ ዓመት እንደሆነው የሚናገሩት ኃላፊው፣ ክልላቸው 20ኛውን የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀንን የማክበር እድል እንዳገኘ ከታወቀበት ሰዓት ጀምሮ ተገቢው ስራ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ የመሰረተ ልማት ስራዎችን የማስፋፋት በተለይም ከተሞችን በማስዋብ ፅዱ ማድረግ ተችሏል፡፡ በተለይም የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በሀገሪቱ የመጀመሪያ የሆነው የገጠር ኮሪደርንም በክልሉ በአራት ዞኖች (ሀዲያ፣ ስልጤ፣ ሀላባና ከምባታ ዞኖች) አስጀምረው በተሳካ ሁኔታ ተጠናቆ ለነዋሪዎች እንዲተላለፉ ተደርጓል፡፡ ኢንቬቲቩን በማስፋፋት የክልሉ መንግስት ከጠቅላይ ሚኒስትሩ የተሰጠውን አደራ በከፍተኛ ቁርጠኝነት እየተወጣ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

## በክልሉ ያሉ ፀጋዎች

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ስር የሚገኙ ከተሞች ለኑሮ ምቹ፣ የክልሉ ሰላም የተጠበቀ እንዲሁም እንግዶችን ቀና በሆነ ስነ ምግባር ለማስተናገድ የተዘጋጀ ማህበረሰብ ስለመኖሩ የሚናገሩት አቶ አብድልባር፣ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በ7 ዞኖች፣ በ3 ልዩ ወረዳዎች፣ በ50 ወረዳዎች እና በ29 የከተማ አስተዳደሮች የተዋቀረ አደረጃጀት ነው፡፡ ሆሳዕና የአስተዳደርና ፖለቲካ መቀመጫ መሆኗን አብራርተዋል፡፡

በክልሉ ያሉ የቱሪዝም ፀጋዎች ብሔራዊ ፓርክና ጥብቅ ደኖች፤ ተራራዎች፣ ሸለቆዎች፣ ፏፏቴዎች፣ ሃይቆች፣ ፍል ውሃዎች እና ትክል ድንጋዮች መሆናቸው ተለይቷል። አቶ አብድልባር በአስተያየታቸው፣ "የሚዳሰሱ ብሎም የማይዳሰሱ ቅርሶች ባለቤት እንደመሆናችን መጠን የውጭ እና የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች የቆይታ ጊዜያቸውን እንዲያራዝሙ ብሎም ደግመው እንዲመጡ አስቻይ ሁኔታዎች በርካታ ናቸው፡፡ የሚጎበኙ ፀጋዎችን በተመለከተ በጉራጌ ዞን የጀፎረ-የጉራጌ ባህላዊ የምህንድስና ጥበብ፣ ጊቤ ሸለቆ ብሔራዊ ፓርክ፤ ቆጠር ገድራ ጥብቅ ደን)፤ በሀዲያ ዞን (ቦዮና ቡደ መዳ ሀይቆች፤ ኣሊዳ ዋሻ፤ አገሜና ሆጄ ፏፏቴ)፣ በምስራቅ ጉራጌ ዞን (የጢያ ዓለም አቀፍ መካነ ቅርስ፣ ጥንታዊ ምድረ ከብድ አቦ ገዳም)፤ በስልጤ ዞን (ሀረ ሼጣንና አባያ ቱፋ ሀይቆች)፣ በከምባታ ዞን (የሀምባርቾ 777 ተራራ፣ የሶድቾ ዋሻ)፣ በሀላባ ዞን (አርቶ ፍል ውሃና ፉማ ፏፏቴ)፣ የም ዞን ("ሳሞ ኤታ" ዓመታዊው የየም የባህላዊ መድኃኒት ለቀማ ስነ ስርዓት፣ ጥንታዊ አንጋሪ ቤተ መንግስት)፤ በቀቤና ልዩ ወረዳ (ጥንታዊና ታሪካዊ ዘብሞላና ቃጥባሬ መስጅዶች)፤ በጠምባሮ ልዩ ወረዳ (የአሞ ሰው ሰራሽ ሀይቅ)፤ በማረቆ ልዩ ወረዳ (የፈቃ ከንፈልቻ ጥንታዊ ዋሻ) እንዲሁም የክልሉ ብሔረሰቦች የማንነታቸው መገለጫ የሆኑ የተለያዩ

> **የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን በዓል በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች መከበር መቻሉ ቱባውን ባህል ለማየት እድል ይፈጥራል**

ዓመታዊ በዓላት ያሏቸው ሲሆን መስቀል በጉራጌ፣ ያሆዴ በሀዲያ፣ መሳላ በከምባታ፣ መንገሳ በሀላባ፤ ሄቦ በየም፣ መሳላ (መሪሾ) በጠምባሮ እና ሌሎች ያልተጠቀሱ የክልሉ ጸጋዎች ናቸው" ብለዋል፡፡

20ኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን አከባበር በርካታ መርሃ ግብሮች የሚከናወኑበት ሆኖ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ብዝሃ ከተሞች አንዷ በሆነችው ወልቂጤ ከተማ በዓሉ በባዘር እና ኢግ ዚቢሽን ይከበራል። ዋናውና ማጠቃለያ ሁነት ሆሳዕና ከተማ ይከበራል፡፡ ከህዳር 25 እስከ 29 የወንድማማቾች ቀን፣ የአብሮነት ቀን፣ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ቀን፣ የምክክር ቀን እንዲሁም የኢትዮጵያውያን ቀን በሚል በድምቀት እየተከበሩ ይገኛል። መርሃ ግብሮችን በተመለከተ የተለያዩ ሲምፖዚየሞች ተዘጋጅተዋል፡፡ የፎቶ አውደ ርዕይ፣ ፓናል ውይይት በክልሉ የሚገኙ የቱሪዝም ሃብቶች የሚጎበኙበት አግባብ ጭምር ስለመዘጋጀቱ ተገልጿል፡፡

እንደ አያሌው (ዶ/ር) ገለፃ፤ በዓሉ በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች መከበር መቻሉ ቱባውን ባህል ምንም ሳይበረዝ ለማየት እድል ይፈጥራል፡፡ የክልሉ ማህበረሰብ የአመጋገብ፣ የአለባበስ፣ የአኗኗር ዘይቤ ምን ይመስላል? የሚለውን በቅርበት የማየቱን እድል ሰፊ ያደርገዋል። በክልል ከተሞች የሚገኙ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ መስህቦችን ለመጎብኘት እድሉን ያገኘ እንግዳ ቀጣይ ሌሎችን ሰዎች ጭምር ይዞ ለመምጣት ፍላጎት ያድርበታል፡፡ በሀገር ውስጥ ቱሪዝም ክልሎች በርካታ ጎብኚዎች እንዲኖራቸው የሚያደርግ ሲሆን ከገቢ አንፃርም ከፍተኛ አበርክቶ አለው፡፡

የበዓሉ መከበርን ፋይዳ አያሌው (ዶ/ር) ሲገልጹ፣ የቱሪዝም ፀጋዎች እንዲተዋወቁ ያደርጋል። ኢንቨስትመንትን ያበረታታል። ኢኮኖሚውን ያነቃቃል፤ የሥራ ባህል ያሻሽላል፡፡ የሥራ ዕድል ይፈጥራል፡፡ እንደሀገር የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች እርስ በርስ ባህላቸውን፤ ማንነታቸውን በማስተዋወቅ ማህበራዊ መስተጋብር ያጠናክራል፡፡ ወንድማማችነትና እህትማማችነትን በማጠናከር፤ ህብረ ብሔራዊ አንድነትን በማጎልበት ገዥ ትርክት እንዲሠርፅ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ አብራርተዋል።

# የቅጥር ማስታወቂያ

## የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከዚህ በታች በተገለፁት ክፍት የስራ መደቦች ላይ አመልካቾችን አወዳድሮ ለመቅጠር ይፈልጋል።

| ተ.ቁ | የሥራ መደብ መጠሪያ | ደረጃ | ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ | አግባብ ያለው የሥራ ልምድ | የሙያ ዓይነት | መደብ መታወቂያ ቁጥር | ብዛት | የቅጥር ሁኔት | ደመወዝ | የሥራ ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | **ለሬዲዮ ዘርፍ** | | | | | |
| 1 | የሬድዮ መዝናኛ ሪፖርተር | IX | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 3/1 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ እንዲሁም በጤና፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፣ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በስነ ትምህርት ዘርፎች ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.210 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አ/አ |
| 2 | የሬዲዮ ዜና ጀማሪ ሪፖርተር | VII | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 0 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ እንዲሁም በጤና፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፣ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በስነ ትምህርት ዘርፎች ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.237 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አ/አ |
| | | | | | **ለቋንቋዎች ዘርፍ** | | | | | |
| 3 | የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ መዝናኛ ጀማሪ ሪፖርተር | VII | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 0 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ እንዲሁም በጤና፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፣ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በስነ ትምህርት ዘርፎች ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.703 | 2 | በኮንትራት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አ/አ |
| 4 | የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ መዝናኛ ሪፖርተር | IX | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 3/1 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ እንዲሁም በጤና፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፣ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በስነ ትምህርት ዘርፎች ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.697 | 1 | በኮንትራት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አ/አ |
| 5 | የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ መዝናኛ ከፍተኛ ሪፖርተር | X | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 5/3 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ እንዲሁም በጤና፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፣ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በስነ ትምህርት ዘርፎች ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.694 | 1 | በኮንትራት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አ/አ |
| 6 | የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ትምህርታዊ ከፍተኛ ሪፖርተር | X | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 5/3 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ እንዲሁም በጤና፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፣ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በስነ ትምህርት ዘርፎች ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.675 | 1 | በኮንትራት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አ/አ |
| 7 | የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ዶክመንተሪ ረዳት አዘጋጅ | XI | ቢ.ኤ./ ኤም.ኤ ዲግሪ | 6/4 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ እንዲሁም በጤና፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፣ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በስነ ትምህርት ዘርፎች ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.681 | 1 | በኮንትራት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አ/አ |
| 8 | ትግርኛ ቋንቋ ጀማሪ ሪፖርተር | VII | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 0 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ እንዲሁም በጤና፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፣ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በስነ ትምህርት ዘርፎች ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.732 | 1 | በኮንትራት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አ/አ |
| 9 | ትግርኛ ቋንቋ ሪፖርተር | IX | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 3/1 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ እንዲሁም በጤና፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፣ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በስነ ትምህርት ዘርፎች ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.728 እና አ/18.729 | 2 | በኮንትራት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አ/አ |
| 10 | የእንግሊዘኛ ቋንቋ ከፍተኛ ሪፖርተር | X | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 5/3 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ እንዲሁም በጤና፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፣ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በስነ ትምህርት ዘርፎች ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.802 | 1 | በኮንትራት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አ/አ |
| 11 | የእንግሊዘኛ ቋንቋ ረዳት አዘጋጅ | XI | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 6/4 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ እንዲሁም በጤና፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፣ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በስነ ትምህርት ዘርፎች ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.798 | 1 | በኮንትራት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አ/አ |
| | | | | | **ለቴሌቪዥን ዘርፍ** | | | | | |
| 12 | ከፍተኛ የቴሌቪዥን የመዝናኛ ፕሮግራሞች አዘጋጅ | XIII | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 8/6 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ እንዲሁም በጤና፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፣ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በስነ ትምህርት ዘርፎች ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.171 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አ/አ |
| | | | | | **ለህትመትና ዲጂታል ሚዲያ ዘርፍ** | | | | | |
| 13 | የዲጂታል ይዘት ፕሮዳክሽን ም/ዋና አዘጋጅ | XIV | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 9/7 ዓመት ሲሆን ከዚህ ውስጥ 2ቱን በከፍተኛ አዘጋጅነት የሰራ/ች | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ እንዲሁም በጤና፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፣ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በስነ ትምህርት ዘርፎች ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.254 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አ/አ |

## ማሳሰቢያ፡-

1. አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10/አስር/ ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የትምህርት ማስረጃችሁን ዋናውንና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ በመያዝ በተቋሙ የሰው ኃብት ስራ አመራር እና ልማት ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 05 ድረስ በመምጣት እንድትመዘገቡ እናሳስባለን፡፡
2. ከግል ድርጅቶች የሚቀርብ የስራ ልምድ ማስረጃ የስራ ግብር የተከፈለበት ስለመሆኑ ከግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ማስረጃ ማምጣት ይኖርባቸዋል፡፡
3. የስራ ልምድ የሚጠይቀው ከወጣው ክፍት መደብ ጋር ቀጥተኛ መሆን አለበት፡፡
4. በቴክኒክና ሙያ/ሌቬል የሚወዳደሩ የብቃት ማረጋገጫ/COC ማቅረብ አለባቸው፡
5. ተመዝጋቢዎች ለምዝገባ ሲመጡ ፋይዳ መታወቂያ ኦርጂናል እና ኮፒ ማቅረብ አለባቸው፡፡
6. የምዝገባው ቀን ከህዳር 29/2018 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 10/ ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ
7. የፈተና ቀን በውስጥ ማስታወቂያ ይገለፃል፡፡
8. ለበለጠ መረጃ አድራሻ አምስት /5/ ኪሎ ቅድስተ ማርያም ፊት ለፊት ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጉን ስልክ 0111551848

# አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ

# ልጆች፤ በሽታን ለመከላከል ስለሚያግዙ ነገሮች ምን ያህል ታውቃላችሁ?

**በፋንታነሽ ተፈራ**



ሲዲሴ ፋሲል — ሮቤል ዘውዴ — እጅግነሽ ሙልዬ — ልዑል ከተማ

ፎቶ በገነት ወንድሙ

ልጆች፤ እንዴት ናችሁ? በየሳምንቱ በምንጽፋቸው ጉዳዮች ቁም ነገር እንደጨበጣችሁ ተስፋ እናደርጋለን:: በዛሬው ርዕሰ ጉዳያችን ደግሞ በሽታን አስቀድሞ መከላከል ላይ ሊከናወኑ ስለሚገባቸው ተግባራት የሌሎችን ልጆች ልምዶች አካትተን እንደሚከተለው አቅርበነዋል::

ሲዲሴ ፋሲል እባላለሁ። በፀሐይ ጮራ ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ7ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ:: በየቀኑ ከማከናውናቸው ተግባራት አንዱ ውሃ መጠጣት ነው:: ይህንንም የማደርገው ውሃ የመጠጣት ልምድ የሌላት እህት አለችኝ:: ይህን ባለማድረጓ ምክንያት የኩላሊት ታማሚ ሆናለች:: ተንቀሳቅሳ ለመስራትም ትቸገራለች:: እኔም ከዚህ በፊት በቀን ሁለት ጊዜ ብቻ ነበር የምጠጣው:: በአሁኑ ወቅት በቀን አራት ጊዜ በተቻለኝ አቅም እየጠጣሁ ነው::

ከዚህ በተጨማሪ ስፖርት እሰራለሁ:: ጤናማም ነኝ:: ትምህርቴንም በንቃት እንድከታተል አድርጎኛል:: ውሃ መጠጣቴም ሆነ ስፖርት መስራቴ ደስተኛ እንድሆን አግዞኛል::

ሮቤል ዘውዱ እባላለሁ:: 12 ዓመቴ ሲሆን ውሃ በቀን አራት ጊዜ እጠጣለሁ:: ትምህርት ቤት ስሄድም በኮዳዬ የምይዘውን ውሃ ጨርሼ ነው የምመለሰው:: በምማርበት ፀሐይ ጮራ ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በስፖርት ክፍለ ግዜ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ አደርጋለሁ:: የስፖርት ዝግጅቶች ሲኖሩም ከቤተሰቦቼ ጋር እሳተፋለሁ:: በወር አንድ ጊዜ እሁድ ቀን የመኪና እንቅስቃሴ ስለሚዘጋ የጎዳና ላይ ሩጫ እሮጣለሁ:: በዚህም 40 ኪሎ የነበረው ክብደቴ በ5 ኪሎ ቀንሷል:: ጤነኛ ሆኜ ትምህርቴን እንድማር አግዞኛል::

እጅግነሽ ሙልዬ እባላለሁ:: በፀሐይ ጮራ ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ነኝ:: የ5ኛ ክፍል ተማሪ ስሆን 13 ዓመቴ ነው:: ውሃ የመጠጣት ልምዴ አነስተኛ ነበር፤ አያቴን አሟት ህክምና ቦታ ሄዳ የሽንት ቧንቧ ኢንፌክሽን መሆኑ ተነግሯት ውሃ መጠጣት እንዳለባትም ምክር ተሰጥቷት በቀን 2 ሊትር ውሃ እየጠጣች ነው:: ውሃ መጠጣት ለጤና ጠቃሚ መሆኑን ከአያቴ ትምህርት ወስጃለሁ:: የማይጠጡ ልጆችም ካሉ እንዲጠጡ እላለሁ። ትምህርት ቤት በኮዳ የምወስደውን ውሃ ጨርሼ እጠጣለሁ:: ስፖርትም እሰራለሁ:: ስፖርት መስራቴም ደስታዬን ጨምሮልኛል:: ጤናማም አድርጎኛል። ከዚህ በተጨማሪ ትምህርት ቤት የተለያየ ስፖርት እሰራለሁ:: እሁድ እሁድ ከሰፈር ልጆች ጋር እሮጣለሁ:: በተጨማሪም እግር ኳስ እጫወታለሁ:: እንቅስቃሴ ማድረጌ የሰውነት ክፍሎቼ እንዲፍታቱ እና ቅልጥፍናዬ እንዲጨምር አድርጎልኛል::

ልዑል ከተማ እባላለሁ:: የ5 ክፍል ተማሪ ነኝ:: ጤናዬን ለመጠበቅ ውሃ ሲጠማኝ ብቻ ሳይሆን ሳይጠማኝም የመጠጣት ልምድ አለኝ:: ቤተሰቦቼም ውሃ እንድጠጣና ስፖርት እንድሰራ ያበረታቱኛል::

ስፖርት መስራት ያስደስተኛል:: የፀሐይ ጮራ ቅድመ አንደኛ፣ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሳምንት ሁለት ቀን እሰራለሁ:: በሳንምት ሶስት ቀን ደግሞ ከትምህርት ሰዓት ውጭ የእግር ኳስ ስልጠና እሰለጥናለሁ:: ስፖርት በመስራቴም እድሜዬና ክብደቴ እንዲመጣጠን አድርጎኛል:: ጤናማ ሰውነት እንዲኖረኝ ረድቶኛል:: ውሃ በመጠጣትና ስፖርት በመስራት ጥንቃቄ ስለማደርግ በህመም ምክንያት ከትምህርት ቤት ቀርቼ አላውቅም፤ በጣም ጤነኛ ነኝ::

ልጆች፤ እናንተም ውሃ መጠጣትና አካላዊ እንቅስቃሴ ማድረግን ጨምሮ በሽታን አስቀድሞ መከላከል የሚያስችሉ ተግባራትን በማከናወን ጤናችሁን መጠበቅ አለባችሁ እንላለን::

## 10 ልዩነቶችን ፈልጉ





## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**ጥቁር ላም ነጭ እንቦሳ አስከትላ**

**መልስ፡-** ሀ. ጀበናና ስኒ

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**የዚህ ሳምንት ጥያቄ ፡-**
**እግር የላትም ትሄዳለች፤ አፍ የላትም ትናገራለች።**

ሀ. መንገድ
ለ. ሬድዮ
ሐ. ሰዓት

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ::**

**ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ**

# መፍትሔ ጠቋሚው የመስክ ምልከታ

**በላዋይሽ ቢተው**

የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን የሚያስተዳድራቸው የመንገድ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ እንዲጠናቀቁ ለማድረግ ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል የፕሮጀክቶች የመስክ ምልከታ ተጠቃሽ ነው፡፡ በቅርቡ የባለሥልጣኑ ስትራቴጅክ ማኔጅመንት አባላትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች በስራ ተቋራጮች እና በራስ ኃይል እየተገነቡ የሚገኙ የመንገድ ፕሮጀክቶችን የግንባታ ሂደት ተዘዋውረው ጎብኝተዋል። የጉብኝቱ ዋና ዓለማ እየተገነቡ የሚገኙ የመንገድ ፕሮጀክቶች ወቅታዊ አፈፃፀም ለመቃኘትና የተጓተቱ የመንገድ ፕሮጀክቶች የግንባታ ሂደት እንዲፋጠን አቅጣጫ ለማስቀመጥ ያለመ ነው፡፡

የመስክ ጉብኝት ከተደረገባቸው የመንገድ ፕሮጀክቶች መካከል ከአየር ጤና - ወለቴ፣ ፋኑኤል፣ በረከት፣ ወታደር ሰፈር፣ ቦሌ ቡልቡላ 5፣ ጀሞ ጋራ፣ ኮዬ ፈጬ የጋራ መኖሪያ ቤቶች የውስጥ ለውስጥ የመንገድ ፕሮጀክቶች፣ አራብሳ- አይሲቲ ፓርክ፣ አቃቂ ድልድይ ይገኙበታል፡፡

ጉብኝት የተደረገባቸው የመንገድ ፕሮጀክቶች በተደጋጋሚ ከህዝብ ቅሬታ የሚቀርብባቸው እና በተያዘላቸው ጊዜ መጠናቀቅ ያልቻሉ መሆናቸው ፕሮጀክቶቹ ያሉበትን ሁኔታ በቦታው ተገኝቶ መገምገምን አስፈላጊ አድርጎታል።

የአየር ጤና አደባባይ- ወለቴ - አለምገና መንገድ የመስክ ምልከታ ከተከናወነባቸው ፕሮጀክቶች መካካል ይገኝበታል፡፡ የመውጫና መግቢያ ኮሪደር ሆኖ ለረጅም ዓመታት ሲያገለግል የቆየው ይኸው መንገድ ደረጃው ተሻሽሎ እየተገነባ ይገኛል፡፡ ቀደም ሲል በአንድ ጊዜ ሁለት ተሽከርካሪዎችን ብቻ የሚያስተናግድ ጠባብ መንገድ በመሆኑ፣ በአካባቢው እየጨመረ የመጣውን የትራፊክ ፍሰት ለማስተናገድ አስቸጋሪ ሆኖ ቆይቷል፡፡

በዚህም መነሻነት 30 ሜትር የጎን ስፋት እንዲኖረው ተደርጎ፣ ሰፊ የእግረኛ መንገድ እና ሌሎች ዘመናዊ የመንገድ መሰረተ ልማት አካላትን አካትቶ በመገንባት ላይ ነው፡፡ ፕሮጀክቱ 5 ነጥብ 7 ኪሎ ሜትር ርዝመት እና 40 ሜትር ስፋት ያለው የአስፓልት መንገድ ግንባታ ነው። የግንባታ ስራውን እያከናወነ የሚገኘው ደግሞ ይርጋለም ኮንስትራክሽን የተባለ ሀገር በቀል ሥራ ተቋራጭ ነው፡፡

ፕሮጀክቱ በ2018 በጀት ዓመት አድገት ያሳየ ቢሆንም የስራ ተቋራጩ ግንባታውን በፍጥነት እንዲያከናወን በመስክ ምልከታው ወቅት የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በአፅንኦት ተናግረዋል። የስራ ተቋራጩ ያለውን ሙሉ አቅም በመጠቀም እንዲሁም ቀን ከሌት በመስራት ፕሮጀክቱን ከዳር እንዲያደርስ መመሪያ ሰጥተዋል፡፡



ፎቶ ከፋይል

የተቋሙ አመራሮች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የመንገድ ፕሮጀክቶች ላይ የመስክ ምልከታ ባደረጉበት ጊዜ

ሌላኛው ቅኝት የተደረገበት የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት 6 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው የአራብሳ - አይሲቲ ፓርክ ነው። ፕሮጀክቱ ከተማዋን በምስራቅ በኩል ከቦሌ ጎሮ መንገድ እና ከሌሎች የኮሪደር መንገዶች ጋር የሚያገናኝ ነው። አለማየሁ ከተማ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ የመንገዱን ግንባታ ለማከናወን የተዋዋለ ቢሆንም የስራ ተቋራጩ በተፈለገው ፍጥነት ግንባታውን እያከናወነ ባለመሆኑ፤ በተቀላጠፈ ሁኔታ የግንባታ ሂደቱን እንዲቀጥል የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነዬር ሙህዲን ረሻድ በመስክ ምልከታው ወቅት ለፕሮጀክቱ መሪዎች ጥብቅ መመሪያ ሰጥተዋል፡፡

የመስክ ምልከታው ከዋና መንገዶች ባሻገር በጋራ መኖሪያ መንደሮች የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ፋኑኤል፣ በረከት፣ ወታደር ሰፈር የጋራ መኖሪያ መንደሮች ላይም የቀጠለ ሲሆን የውስጥ ለውስጥ የአስፓልት መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ላይ ምልከታ ተደርጓል፡፡ ፕሮጀክቱ 4 ነጥብ 1 ኪሎ ሜትር የአስፓልት እና 5 ነጥብ 6 ኪሎ ሜትር የኮብል መንገድ ርዝመት አለው፡፡ ድሪባ ደፈርሻ የስራ ተቋራጭ የአስፓልት መንገድ ግንባታውን እያከናወነው ሲሆን 514 ሜትር ሽፋን ያለውን መንገድ የመጀመሪያ ደረጃ አስፓልት በማድረግ የፓይፕ ቀበራ እና ቁፋሮ በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ ጥላሁን አበበ ጠቅላላ የስራ ተቋራጭ የኮብል መንገድ ግንባታ ስራውን በማከናወን 3 ኪ.ሜ ሰብ ቤዝ ደረጃ አድርሷል በተጨማሪም የከርቭ ስቶን፣ የዝናብ ውሀ ማፋሰሻ መስመር ዝርጋታ እና የቁፋሮ ስራዎችን በመስራት ላይ ነው፡፡

የባለስልጣኑ አመራሮች እና ባለድርሻ አካላት ፕሮጀክቶቹን ተዘዋውረው በተመለከቱበት ወቅት የግብአት እጥረት፣ የወሰን ማስከበር ችግር እና የአፈር መድፊያ ቦታ እጥረት የመንገዱን ግንባታ በታቀደው ልክ ለማከናወን ፈታኝ እንዳረገባቸው የፕሮጀክቱ ኃላፊዎች ቢገልፁም ተቀባይነት የሌለው አቤቱታ በመሆኑ ስራ ተቋራጮቹ የግንባታ ስራዎችን በፍጥነት እንዲያከናውኑ የባለስልጣኑ አመራሮች አቅጣጫ ሰጥተዋል፡፡ በቀጣይ አንድ ወር ለኮብል መንገድ የተለዩ መንገዶች ኮብል ንጣፍ ስራውን እንዲያከናውኑ እንዲሁም አስፓልት የሚሆኑትን መንገዶች የአስፓልት ደረጃ አድርሱ በማለት የባለስልጣኑ አመራሮች ለስራ ተቋራጩ ማሳሰቢያ ሰጥተዋል፡፡

የመስክ ምልከታው ሌላኛው መዳረሻ ቦሌ አራብሳ 5 ኮንዶሚኒየም የአስፓልት እና የኮብል መንገዶች ግንባታ ፕሮጀክት ሲሆን በባለስልጣኑ የራስ ኃይል መንገድ ግንባታ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ ፕሮጀክቱ በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን ግንባታ ሲከናወን ቆይቶ በታቀደው ፍጥነት መሰረት ሊከናወን ባለመቻሉ ባለስልጣኑ ግንባታውን ተረክቦ በራስ ሀይል እየገነባው ይገኛል፡፡

የመንገድ ፕሮጀክቱ 4 ነጥብ 4ኪሎ ሜትር የአስፓልት መንገድ ሲሆን ግንባታው 38 በመቶ ደርሷል እንዲሁም 5 ነጥብ 3 ኪሎ ሜትር ሽፋን ካለው የኮብል መንገድ ግንባታ 45 በመቶ መስራት እንደተቻለ በጉብኝቱ ወቅት ለተሳታፊዎቹ ገለፃ ተደርጓል፡፡ የግንባታ ስራው ከውሃ፣ ኤሌክትሪክ እና ቴሌኮም መሰረተ ልማት ዝርጋታ ጋር በቅንጅት በመከናወን ላይ እንደሆነም ተጠቁሟል፡፡ ፕሮጀክቱ በጥሩ እንቅስቃሴ ላይ መሆኑን በመስክ ምልከታ ወቅት የተናገሩት ዋና ዳይሬክተሩ ኢንጂኒዬር ሙህዲን ረሻድ፣ በቀጣይ የአስፓልት የማልበስ ስራ በፍጥነት እንዲጀመር መመሪያ ሰጥተዋል፡፡

የመጀመሪያው ዙር የመስክ ምልከታ የመጨረሻ መዳረሻ የነበረው የካ ጣፎ ኮንዶሚኒየም የአስፓልት እና ኮብል መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ባለስልጣኑ በራስ ሀይል የሚገነባው ነው፡፡ ይህ ፕሮጀክት 3 ነጥብ 8 ኪሎ ሜትር የአስፓልት መንገድ እና 7 ኪሎ ሜትር የኮብል መንገድ ሽፋን አለው፡፡

የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አካባቢው የልማት ተነሺዎች መኖሪያ እንደመሆኑ የልማት ጥያቄ እየቀረበበት ስለሚገኝ ግንባታው በፍጥነት ተጠናቆ ወደ አገልግሎት እንዲገባ ትዕዛዝ አስተላልፈዋል፡፡ የኮብል መንገዱን በተመለከተም ቀሪ ስራዎችን በማጠናቀቅ ለማህበራት እንዲያስረክቡም ነው ዋና ዳይሬክተሩ ግንባታውን እያከናወነ ለሚገኘው የባለስልጣኑ ፕሮጀክት ፅህፈት ቤት ያሳሰቡት፡፡

የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ኢንጂኒዬር ሙህዲን ረሻድ ከመስክ ምልከታው መጠናቀቅ በኋላ በሰጡት አስተያየት፣ "የመስክ ምልከታው የፕሮጀክቶቹን የግንባታ ደረጃ በመገምገም እና ያጋጠሙትን ችግሮች በመለየት የመፍትሔ አቅጣጫ ለማስቀመጥ አስችሎናል" ብለዋል፡፡

የመስክ ምልከታው፣ "ባለስልጣኑ በራስ ኃይልና በስራ ተቋራጮች እያስገነባቸው የሚገኙ የመንገድ ፕሮጀክቶች የወቅታዊ አፈፃፀም ለመቃኘትና የተጓተቱ የመንገድ ፕሮጀክቶችን የግንባታ ሂደት እንዲፋጠን አቅጣጫ ለመስጠት እድል ፈጥሯል" ያሉት የባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ የኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ኢንጂኒዬር ታከለ ሉሌና በበኩላቸው የመልካም አስተዳደር ጥያቄ የሚነሳባቸውን የመንገድ ፕሮጀክቶች አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት እንደሚያስችልም ተናግረዋል።

የባለሥልጣኑ ሬጉላቶሪ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ኢንጂኒዬር ፀጋዬ ቦርሴ የመስክ ምልከታው በፕሮጀክቱ ላይ "የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ፣ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የወሰን ማስከበርና ተያያዥ ችግሮችን ለመፍታት እንዲሁም የግንባታ ስራውን ለማፋጠን ትልቅ አቅም አለው" ብለዋል፡፡

ኢኮኖሚ

**ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ**

# “‘ከተማ ላይ ዓሳ ማርባት አይቻልም’ የሚለውን አስተሳሰብ በተግባር መቀየር ችያለሁ”

**በዓሳ እርባታ ስራ የተሰማራው ወጣት አይናለም ሙሉጌታ**

- **በከተማዋ 9 ሺህ 602 ኪሎ ግራም የዓሳ ምርት ለማግኘት እየተሰራ መሆኑ ተጠቁሟል**

**በይግለጡ ጓዴ**

የድምጻዊ አሰፋ አባተ ‘ዓሣ አበላሻለሁ ዓባይ ዳር ነው ቤቴ፤ ዶሮ መረቅማ ከወዴት አባቴ’ የሚለው ስንኝ በብዙ መልኩ ሊተረጎም የሚችል ቢሆንም ብዙዎችን የሚያግባባው ግን ዓባይ ዳር ለሚኖር ሰው ዓሳ እንደልብ የሚገኝ ስለመሆኑ ነው፤ በዚያ ዘመን ዓሣ እንደ ዶሮ ወጥ ሁሉ ከተወዳጅ ምግቦች ተርታ ቢመደብም በውሃ አካላት አቅራቢያ እንጂ እንደዚህኛው ዘመን በከተሞችም ጭምር የሚመረት ባለመሆኑ የስንኝ ማድመቂያ ይሆን ነበር፡፡

የሥነ ምግብ ባለሙያዎች ዓሣን መመገብ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ይመክራሉ፤ ነገር ግን ለብዙሃኑ ኢትዮጵያውያን ዓሣ ማግኘት ቀላል አልነበረም፡፡ ከገንዘብም በላይ አካባቢ የሚወስነው ጉዳይ ሆኖም ኖሯል። ዳሩ የዓሳ እርባታ ዛሬ በመላው ኢትዮጵያ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራበት ከሚገኘው የግብርና ዘርፍ ውስጥ አንዱ ሆኗል።

የግብርና ስራ ፍኖተ ካርታ፣ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ እና ፓኬጅ ተዘጋጅቶለት ከተሜው ጭምር እንዲጠቀምበት እየተደረገ ነው። በዚህም ለረጅም ጊዜ ከገበታ ርቆ የነበረውን ዓሣን በአዲስ አበባ ከተማ ጭምር በየጓሮው ልክ እንደ ጎመን የሚያገኙት እየሆነም መጥቷል፡፡ የድምጻዊ አሰፋ አባተን፣ ‘ዓሣ አበላሻለሁ ዓባይ ዳር ነው ቤቴ፤ ዶሮ መረቅማ ከወዴት አባቴ’ የሚለውን ስንኝ በመዋስ ‘ዓሣ አበላሻለሁ ቡልቡላ ነው ቤቴ፤ ዶሮ መረቅማ ከወዴት አባቴ’ ለማለት የወደድንበትን መረጃ በዚህ ፅሑፍ እናጋራችኋለን፡፡



ፎቶ ከፋይል

በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 በተለምዶ ቡልቡላ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ በዓሳ እርባታ ስራ የተሰማራው ወጣት አይናለም ሙሉጌታ

ወጣት አይናለም ሙሉጌታ በአዲስ አበባ ከተማ ዓሳ ማርባት ላይ ከተሰማሩ ወገኖች መካከል አንዱ ነው፤ በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 በተለምዶ ቡልቡላ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ ነዋሪ የሆነው ወጣቱ፣ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የተጀመረውን የሌማት ትሩፋት መርሃ ግብር ተቀላቅሎ በቅጡ እየተጠቀመበት መሆኑን ይናገራል፡፡

ከ6 ዓመት በፊት ከሰበታ የዓሳ ምርምር ማዕከል 1 ሺህ 500 የዓሳ ጫጩቶችን ገዝቶ በማምጣት ከቡልቡላ ፓርክ ጀርባ የካባ ድንጋይ ሲወጣበት የነበረውን ሰፊ ጉድጓድ ውሃ ሞልቶ ወደ ጥቅም ማስገባቱን የሚናገረው ወጣቱ፣ ላለፉት ሶስት ዓመታት ምርቶቹን ወደ ገበያ በማውጣት ሲሸጥ መቆየቱን ነግሮናል፤ በዚህም ገቢውን አሳድጓል፡፡

በዓሳ እርባታ ስራ ለዘጠኝ ወጣቶች የስራ እድል የፈጠረው ወጣት አይናለም፣ “ከተማ ላይ ዓሳ ማርባት አይቻልም” የሚለውን አስተሳሰብ በተግባር መቀየር ችሏል፡፡ “አዲስ አበባ ላይ የዓሳ እርባታ ስራ የሚተገበር አይመስልም ነበር፤ ከከተማ የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና

> **“በአዲስ አበባ 13 በግል እና 37 ደግሞ በማህበር የተደራጁ አካላት በዓሳ እርባታ ስራ ዘርፍ ተሰማርተዋል፤ በ2017 ዓ.ም 9 ሺህ 414 ኪሎ ግራም የዓሳ ምርት ተገኝቷል፤ በ2018 በጀት ዓመት ደግሞ 9 ሺህ 602 ኪሎ ግራም የዓሳ ምርት ለማግኘት እየተሰራ ነው”**

ባለሙያዎች ሙያዊ እገዛ በተጨማሪ የአጭር ጊዜ የዓሳ እርባታ ስልጠና በማግኘቴ ውጤታማ ሆኛለሁ” ብሏል ከዝግጅት ክፍላችን ጋር በነበረው ቆይታ።

ወጣት አይናለም የዓሳ እርባታ ስራውን ከተለያዩ ቦታዎች ለሚመጡ ግለሰቦችና ቡድኖች ተሞክሮውን እያጋራ ይገኛል። ከዓሳ እርባታ ጎን ለጎን በአካባቢው የዶሮ እና የፍየል እርባታ ስራም ይሰራል፤ በቀጣይም የተቀናጀ የከተማ ግብርና ስራ ተግባራዊ በማድረግ በበግ ማድለብ እና በወተት ላም የእርባታ ስራም ለመሳተፍ እቅድ አለው፡፡

በሳምንት ከ100 እስከ 150 ኪሎ ግራም የዓሳ ምርት እንደሚያገኝ የጠቆመው ወጣቱ፣ ወደ ቤታቸው ይዘው ለሚሄዱ ደንበኞቹ በኪሎ 600 ብር፣ በቦታው ላይ ተጠብሶ ለሚመገብ ደግሞ በኪሎ 800 ብር ይሸጣል፡፡ የገበያ ትስስር የተፈጠረለት ወጣቱ በግብርና ባለሙያዎች የሙያ ድጋፍ እና የመብራት እንዲሁም የውሃ አገልግሎት ተጠቃሚ በመሆኑ የበለጠ ውጤታማ እንዳደረገው ገልፆልናል፡፡

እንደ እንቁላል፣ ዶሮ፣ ዓሳ፣ ወተት እና የወተት ተዋጽኦ ያሉ የግብርና ምርቶች በከተማዋ ዙሪያ ከሚገኙ አካባቢዎች ሲገባ እንደነበር ወጣቱ በማስታወስ፣ የሌማት ትሩፋት መተግበር ከጀመረ ወዲህ ግን በአዲስ አበባ ከተማ ጥሩ ውጤት መጥቷል ባይ ነው፡፡

የከተማ ነዋሪዎች በውስን ቦታ ላይ ሰርተው ውጤት ማግኘት እንደሚችሉ እውቀት አልነበራቸውም የሚለው ወጣት አይናለም፣ የሌማት ትሩፋት ተግባራዊ መሆን ከጀመረ ወዲህ ነዋሪዎቹ ባላቸው ክፍት ቦታ እንዴት አድርገው መስራት እና ምርት ማግኘት እንደሚችሉ በደንብ እየተሰራበት ነው ብሏል፡፡

ወጣት አይናለም የሌማት ትሩፋት በተለይም ደግሞ በዓሳ እርባታ ውጤታማ እንዲሆን እንዳስቻለው ገልጾ፣ ስራው ሲጀምር በርታ፣ ጠንክር ከሚሉት ጓደኞቹ ጎን ለጎን እንዴት ከተማ ላይ ይሳካል? የሚሉ እንደነበሩ ያስታውሳል፤ ውጤቱን ሲመለከቱ ግን ግርምት ፈጥሮባቸዋል ሲል ነግሮናል፡፡

ዓሳ በትኩረት ከተሰራበት ከራስ ምግብነት ባለፈ ለገበያ በማቅረብ ገቢን ማሳደግ እንደሚያስችል ወጣቱ ያስረዳል። ከሽያጭ ከሚያገኘው ገቢ በስሩ የሚገኙ 9 ሰራተኞች እና ቤተሰቦችን ከማስተዳደር ባለፈ በአዋጭ የብድርና ቁጠባ ተቋም ገንዘብ መቆጠብ ችሏል፡፡

ወይዘሮ አሰለፈች መኩሪያ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የወረዳ 11 ነዋሪ ናቸው፡፡ በግቢአቸው ባለ ክፍት ቦታ ላይ ጉድጓድ ቆፍረው ዓሳ ማርባት ችለዋል። 635 የዓሳ ጫጩቶችን በመያዝ ወደ ስራ ከገቡ ሁለት ወር እንደሆናቸው በመጠቆም፣ ስራው ውጤታማ እንደሚያደርጋቸው ከወዲሁ እምነት ማሳደራቸውን ገልፀዋል፡፡

ከዚህ ቀደምም በጓሮ አትክልት ልማት እና በዶሮ እርባታ ተሰማርተው ውጤታማ መሆናቸውን የተቆሙት ወይዘሮ አሰለፈች፣ የዓሳ እርባታ ከሚያከናወኑ ከሌሎች ነዋሪዎች ባገኙት ተሞክሮ እና በክፍለ ከተማ ግብርና ባለሙያዎች በተደረገላቸው ሙያዊ ድጋፍ የዓሳ እርባታ ስራውን በጥሩ ሁኔታ እያከናወኑ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

የከተማ ግብርና የከተማ ነዋሪዎች ባላቸው ውስን ቦታ ሰርተው ውጤታማ እንዲሆኑ አስችሏል ባይ ናቸው፡፡ ወይዘሮ አሰለፈች በቀጣይ የዓሳ እርባታ ስራውን ይበልጥ አጠናክረው ለመቀጠል ከወዲሁ ተዘጋጅተዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ኮሚሽነር ባዩ ሽጉጤ የዓሳ እርባታ የሥራ ዕድል በመፍጠር እንዲሁም የምግብ ፍጆታን በማሟላት በኩል ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

በወጣት አይናለም እየተሰራ ያለው የዓሳ እርባታ የስራ እድል ከመፍጠር አልፎ ከፍተኛ የገቢ ምንጭ ማስገኘት መቻሉን ጠቁመው፣ ከዚህም በላይ በሰፊው ማልማት እንዲችል አስፈላጊው ድጋፍ እንደሚደረግለት ተናግረዋል፡፡

በአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን በእንስሳት ሀብት ልማት ዳይሬክቶሬት የእንስሳት ዕርባታ ባለሙያ አቶ ቢንያም አድማሱ በከተማዋ የዓሳ እርባታ ስራ በትኩረት እየተሰራበት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ በከተማዋ 13 በግል እና 37 ደግሞ በማህበር በአጠቃላይ 50 ተጠቃሚዎች በዓሳ እርባታ ዘርፍ ተሳታፊ እንደሆኑ ገልጸዋል፡፡

በከተማዋ 10 የዓሳ ኩሬ እንዲሁም 31 በፖንድ የሚሰራ በአጠቃላይ 41 የዓሳ የእርባታ ቦታ እንደሚገኝ አቶ ቢንያም ጠቁመዋል፡፡ በ2017 ዓ.ም 9 ሺህ 414 ኪሎ ግራም የዓሳ ምርት እንደተገኘ በመጠቆም፣ በ2018 በጀት ዓመት ደግሞ 9 ሺህ 602 ኪሎ ግራም የዓሳ ምርት ለማግኘት እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡

ለዓሳ እርባታ ስራ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ግብዓት እያቀረቡ ሲሆን፣ ከዚህም መካከል የዓሳ ጫጩት የማመቻቸት ስራ አንዱ መሆኑን የእርባታ ባለሙያው ገልጸዋል፡፡

ተጠቃሚዎች ወደዘርፉ እንዲገቡ አስፈላጊውን ሙያዊ ድጋፍ እያደረጉ እንደሚገኙ ገልጸው፣ በዘርፉ ምርትና ምርታማነት እና የተሳታፊዎችን ቁጥር ለመጨመር የድጋፍ እና ክትትል ስራ በማድረግ ላይ እንደሚገኙ አቶ ቢንያም ጠቁመዋል፡፡

አክለውም፣ በከተማዋ የሚገኙ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በዓሳ እርባታ ስራ እንዲሳተፉ እየተሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ኮሚሽነር ባዩ ሽጉጤ በበኩላቸው፣ ዘርፉን ለማሳደግ የወረዳ እና የክፍለ ከተማ የአስተዳደር የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ጽህፈት ቤት ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ድጋፋቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉም አሳስበዋል፡፡

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# መዲናዋ ከማዕድን ሀብቷ ምን ያህል እየተጠቀመች ነው?

- **130 የኮንስትራክሽን ማዕድን አልሚዎች ፈቃድ ወስደው እየሰሩ ይገኛሉ**

**በለይላ መሀመድ**



ፎቶ፡- ከፋይል

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የሚገኘው የጥቁር ድንጋይ ጠጠር ማምረቻ ቦታ

አዲስ አበባ ካሏት የተፈጥሮ ሀብቶች መካከል የኮንስትራክሽን ማዕድን ተጠቃሽ ነው፡፡ በከተማ አስተዳደሩ የኮንስትራክሽን ማዕድን ተብለው ከተለዩት መካከል ጥቁር ድንጋይ፣ ገረጋንቲ፣ ቀይ አሸዋ፣ ቀይ አፈር፣ ነጭ የግንብ ድንጋይ ወይንም ጥርብ ድንጋይና የወንዝ አሸዋ ወይም ጠጠር ይገኙበታል። ጥቁር ድንጋይ በድንጋይ መፍጫ ማሽን (ክሬቸር) ተፈጭቶ ለተለያዩ ግንባታ ግብዓት የሚውል ነው፡፡ ገረጋንቲ በመንገድ፣ በአርማታና ሌሎች ግንባታዎች ላይ ለሙሌት አገልግሎት የሚውል ጠንካራ ድንጋይ ነው፡፡ ቀይ አሸዋ ወይንም ቀይ አፈር ደግሞ ለመንገድ እና ለተለያዩ የግንባታ ስራዎች የሚያገለግል እንደሆነ በአዲስ አበባ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የማዕድን ፍቃድ አሰጣጥ ከፍተኛ ባለሙያ አቶ ደገመው ቱሉ ይገልጻሉ፡፡

ባለስልጣኑ በማቋቋሚያ አዋጁ 74/2014 በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት እና የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 መሰረት አድርጎ የኮንስትራክሽን ማዕድን ፍቃድ አሰጣጥ መመሪያ አዘጋጅቷል፡፡ አቶ ደገመው እንደሚያብራሩት፣ መመሪያው የወጣበት ዓላማ የኮንስትራክሽን ስራዎችና ልዩ ልዩ የኮንስትራክሽን ማዕድናትን በማጥናት የማዕድን ማምረት ፈቃድ መስጠትና ማስተዳደር፣ ከዘርፉ 3 በመቶ (ሮያሊቲ) እና ሌሎች ተዛማጅ ክፍያዎችን መሰብሰብ፣ ውስን የሆነውን የተፈጥሮ ሀብት በአግባቡ በመጠቀም የከተማዋን የኮንስትራክሽን ማዕድናት ፍላጎት እንዲሟላ እንዲሁም አካባቢን ያገናዘበና ከስነ ምህዳር ጋር የሚጣጣም ዘላቂነት ያለው የማዕድን ልማት ማረጋገጥ በማስፈለጉ ነው፡፡

እንደ ባለሙያው ገለጻ፣ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የኮንስትራክሽን ማዕድን ፍቃድን የሚሰጠው በክፍለ ከተማና በማዕከል ደረጃ ነው፡፡ ነጭ ድንጋይ ወይንም ጥርብ ድንጋይ ፍቃድ የሚሰጠው በክፍለ ከተማ ደረጃ ሲሆን ከ5 እስከ 10 ሺህ ካሬ ሜትር ስፋት ባላቸው ስፍራ የሚሰጥ ነው፡፡ በተመሳሳይ ቀይ አሸዋ የሚሰጠው በክፍለ ከተማ ደረጃ በሚገኙ የአካባቢ ጥበቃ ጽህፈት ቤቶች ነው። በማዕከል ወይም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ፍቃድ የሚሰጠው ጥቁር ድንጋይ እና ገረጋንቲ ነው፡፡ የቦታ ስፋቱም 80 ሺህ ካሬ ሜትር ስፋት ባለው መሬት ላይ ሊደርስ ይችላል፡፡ ጥቁር ድንጋይ ፍቃድ የሚወስዱ ማህበራት ወይንም ግለሰቦች የተለያየ መጠን ያላቸውን ጠጠሮች መፍጨት የሚችል የድንጋይ መፍጫ ማሽን (ክሬቸር) ሊኖራቸው ይገባል፡፡

እንዲሁም 'ማዕድን የማውጣት ፍቃድ ይሰጠኝ' የሚል አልሚ ወይንም ባለሀብት መጀመሪያ ማዕድን የሚወጣበትን ቦታ በዘርፉ የሚሰሩ አማካሪ ድርጅቶችን በማስጠናት ልማቱ ከአካባቢው ጋር የተስማማ መሆኑን ማወቅ ይኖርበታል። ሌላው ምን ያህል ትርፋማ እንደሚሆን በአማካሪው ድርጅት ማስጠናት ይኖርበታል፡፡ ጥናቱንም የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ቦታው ድረስ በመሄድ አዋጭነቱን ያረጋግጣል፡፡

ከፍተኛ ባለሙያው በማያያዝም፤ ማዕድን የሚወጣበት ስፍራ ማሟላት ያለበት መስፈርት ለመቃብርና ኃይማኖታዊ ጉዳዮች በተከለሉ ቦታዎች፣ የቅድመ ታሪክ ቅሪቶች ባሉባቸው ወይንም ብሔራዊ መታሰቢያዎች በቆሙባቸው ስፍራዎች፣ መሰረተ ልማት በተከለሉበት ቦታዎች፣ ከመኖሪያ መንደር 500 ሜትር፣ ከኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ ከመሰረተ ልማት አውታሮች 100 ሜትር፣ ከወንዝ ዳርቻዎች ከ30 እስከ 100 ሜትር፣ ከህዝብ መሰረተ ልማት ለምሳሌ ከመብራት ፖል 50 ሜትር፣ ከአስፋልት መንገድ ከ50 እስከ 100 ሜትር መራቅ ስላለበት በዚህ ደረጃ መቀመጡን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

ሌላው አልሚው ለመልሶ ማልማት አቅም ሊኖረው ይገባል፡፡ አሰራሩን በተከተለ መልኩ ለመልሶ ማልማት የሚሆን ገንዘብ በዝግ አካውንት ማስያዝ ይጠበቅበታል፡፡ ምክንያቱም ማዕድን ከወጣ በኋላ ስፍራው ለአደጋ የተጋለጠ ስለሚሆን አልሚው ማዕድን የማውጣት ስራውን እንዳጠናቀቀ ለአደጋ በማያጋልጥ መልኩ ማልማት አለበት፡፡ ሳያለማ የሚወጣ ከሆነ መንግስት አልሚው ያስያዘውን ገንዘብ በመጠቀም ያለማል፡፡ ይህንን ሁሉ መስፈርት አሟልተው ሲገኙ ባለስልጣኑ የአገልግሎት እንደ የካርታ፣ በደረሰኝ የሚከፈል የሮያሊቲ ክፍያ (3 በመቶ ከሚያመርቱት የማዕድን ምርት የሚከፍሉት) ለመሳሰሉ ክፍያ በመቀበል ወደ ፍቃድ መስጠት ይገባል፡፡

አንድ አምራች የሚጠበቅበትን መስፈርት አሟልቶ ፍቃድ ከወሰደበት ቀን ጀምሮ በ6 ወራት ጊዜ ውስጥ የኮንስትራክሽን ግብአቱን ማምረት ይጠበቅበታል፡፡ እያንዳንዱን የምርት መጠን ምን ያህል እንዳመረተ እና እንደሸጠ በየወሩ ሪፖርት እንዲያደርግ ይጠበቃል፡፡ በየ3 ወሩ ደግሞ አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴውን የሚያሳይ መደበኛ ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ፍቃድ ወስዶ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ስራ ካልጀመረ የመጀመሪያ ዙር ማስጠንቀቂያ ይሰጠውና በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ስራ ካልጀመረ ፍቃዱ ተነጥቆ እድሉ ለሌላ አልሚ እንዲዛወር ይደረጋል፡፡ አልሚውን እንዳይጀምር ያደረጉት ችግሮች አሳማኝ ከሆኑ ለምሳሌ ከይዞታና ፍርድ ቤት ጋር የተያያዘ ክርክር ያጋጠመው ከሆነ ችግሩ እንደሚታይለት ከፍተኛ ባለሙያው ገልጸዋል፡፡

በአዲስ አበባ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የማዕድን ፍቃድና አስተዳደር ዳይሬክተር አቶ ኃይሉ ጸጋዬ በበኩላቸው፤ ከደረሰኝ፣ ከገቢና ቅጣት ጋር በተያያዘ በሰጡት ሀሳብ፤ አንድ አልሚ ደረሰኝ ሳይቆርጥ ወይንም የአገልግሎት ክፍያ 3 በመቶ (ሮያሊቲ) ሳይከፍል ምርት ይዞ ቢወጣ እስከ 300 ሺህ ብር ይቀጣል፡፡ የ3 ወር ሪፖርት ካላቀረበ ደግሞ 30 ሺህ ብር ይቀጣል፡፡

አሁን ላይ በኮንስትራክሽን ማዕድን ማውጣት የተሰማሩ 130 አልሚዎች በስራ ላይ መሆናቸውንም አክለዋል፡፡

እነዚህ የኮንስትራክሽን አልሚዎች በተለያየ ጊዜ ክፍያ የሚፈጽሙ ቢሆንም አጠቃላይ በ2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት 15 ሚሊየን 172 ሺህ ብር ገቢ ተሰብስቧል፡፡ ቅጣትን በተመለከተ በህገ ወጥ መንገድና ያለፍቃድ የሚሰሩ አልሚዎችን ለመለየት መረጃ እየተሰበሰበ ነው፡፡ በህጋዊ መንገድ እየሰሩ መሆን አለመሆናቸውን እንዲሁም ከገቢም አንጻር የአንድ ወር እና የሶስት ወር ሪፖርት ማቅረብ ወሳኝ ከመሆኑ አንጻር በበጀት ዓመቱ ሩብ ዓመት ወቅቱን ጠብቀው ሪፖርት ያላቀረቡ 20 አልሚዎችን በገንዘብ ለመቅጣት በደብዳቤ የማሳወቅ ስራ መከናወኑንም አቶ ሀይሉ ገልጸዋል፡፡

## በዘርፉ እያጋጠመ ያለው ፈተና

ከኮንስትራክሽን ግብአት ጋር በተያያዘ እንደ ከተማ እያጋጠመ ያለው ችግር ግብአቱ እያለ ሳንጠቀምበት የማስፋፊያ ግንባታ ስራዎች ይሰሩበታል፡፡ ግብአቱ በብዛት ባለባቸው አካባቢዎች ለምሳሌ በጎሮ፣ በአቃቂ ቃሊቲና በለሚ ኩራ ክፍለ ከተሞች የቤት ግንባታዎች እየተስፋፉ መጥተዋል፡፡ ሌላው የኮንስትራክሽን ግብአት ባለባቸው አካባቢዎች የመሰረተ ልማቶች መስፋፋት ነው፡፡ ህገወጥ የቤት ግንባታ ለኮንስትራክሽን የሚውል የማዕድን ድንጋይ ባለበት ቦታ ላይ ይሰራል፡፡ እነዚህን ህገወጥ የቤት ግንባታዎች አፍርሶ ማዕድን ለማውጣት መሞከር ሌላው ዘርፉን ፈተና ላይ የጣለ ችግር ነው፤ እንደ አቶ ደገመው ገለጻ፡፡

አቶ መስፍን አልከቴ በኮንስትራክሽን ማዕድን ፍቃድ ወስደው ወደስራ የተሰማሩ ባለሀብት ወይንም አልሚ ናቸው፡፡ ስራቸውን በተመለከተ ሲያብራሩ፤ የማዕድን ማልማት ስራውን የሚያከናውኑት በራሳቸው ይዞታ ላይ ገረጋንቲ ማልማት ላይ ነው፡፡ ከአዲስ አበባ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ያገኙት ድጋፍም ወደ ስራ እንዲገቡ አግዞቸዋል። በተጨማሪም በየጊዜው በስራ ቦታቸው (ሳይት) በመገኘት ክትትልና ቁጥጥር ያደርጉላቸዋል፡፡ ክትትል በሚያደርጉበት ወቅትም ለባለሙያዎቹ ተገቢውን ሙያዊ የምክር አገልግሎት ይሰጧቸዋል። በዚህ አገልግሎት መርካታቸውን አብራርተዋል።

## የፌዴራሊዝም ... ከገጽ 6 የዞረ

አተገባበሩ ላይ ግን ክፍተቶች እንደነበሩት አቶ በላይ ያነሳሉ፡፡ ከሀገራዊ ለውጡ በፊት በአብዛኛው በነጠላ ትርክት ወይም አንድ ብሔር ላይ የታጠሩ ስራዎች ጎልተው ይሰሩ ነበር። በዚህ ምክንያት የብሔር አክራሪነትና ዋልታ ረገጥነት በመስፋፋቱ ግጭትና መጠራጠር ተፈጥሯል፡፡ በአንድ ክልል ውስጥ ‘አንተ የእኔ ነህ’፤ ‘አንተ/ቺ የእኔ አይደለህም/ሽም’ የሚል ስሜት፤ አንዱ ሌላውን የማግለል አዝማሚያ ታይቷል። ይህ ዓይነቱ አካሄድም ህገ መንግስታዊ መሰረት የሌለው በትግበራው ያጋጠመ ክፍተት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

ሌላው በህብረ ብሔራዊ የፌዴራሊዝም ስርዓት ሁሉም ክልሎች እኩል እንደሆኑ የተቀመጠ ቢሆንም፣ ግማሾቹ በሀገራዊ ጉዳይ ባለቤት በመሆን የመወሰን መብት ሲኖራቸው፣ ሌሎች (እንደ ቤኒሻንጉል ጉምዝ፣ ሶማሊ፣ ጋምቤላ፣ ሐረር...ያሉ ክልሎች) በድርጅት ስም ‘አጋር’ ተብለው የመወሰን ስልጣን አልነበራቸውም፡፡ ተግባሩ በፓርቲ አደረጃጀት ብቻ ሳይሆን በመንግስት መዋቅር ጭምር ይታይ ነበር። ይህም ስርዓቱን ጎዶሎ አድርጎት ነበር የሚሉት አቶ በላይ፣ ከሀገራዊ ለውጡ ወዲህ ይህ የታረመበት፤ እውነተኛ የፌዴራሊዝም ስርዓት ተግባራዊ የሆነበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

የፌዴራሊዝም ምሁሩ አቶ ሱልጣን በበኩላቸው፤ በተለይ በኢህአዴግ የአስተዳደር ዘመን ህገ መንግስቱ ለይስሙላ እንጂ ሀገር ይመራ የነበረው በዋናነት በፓርቲ ፕሮግራም እንደነበር ያነሳሉ፡፡ ህገ መንግስታዊ ማዕቀፎችና መርሆች ተጥሰው፣ ሀገሪቱ የፌዴረዳሊዝም ስርዓትን የምትከተል ቢሆንም ውሳኔዎች በማዕከላዊ ፓርቲ አደረጃጀት አማካኝነት ነበር የሚሰጡት፡፡

የፌዴራሊዝም ስርዓቱ ክልሎች ያላቸውን መሬት፣ ማዕድናትና የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብቶች በባለቤትነት የመጠቀም መብትን ያጎናፀፈ ቢሆንም የነበረው አስተዳደር ሀብቶች በሚገኙበት አካባቢ ያለውን ማህበረሰብ ትኩረት ባለመስጠቱ ብዝበዛዎች ነበሩ፡፡ ውሎ አድሮም በነበረው አስተዳደር ላይ ተቃውሞዎች እንዲነሱ በማድረግ በመጨረሻ የመንግስት ለውጥ እንዲመጣ አንድ ተጠቃሽ ምክንያት እንደሆነ የፌዴራሊዝም ምሁሩ ሱልጣን ያስረዳሉ።

ሀገራዊ ማንነት ግንባታ ላይ ብዙ አለመሰራቱ የስርዓቱ ሌላኛው ጉድለት ነው፡፡ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ምክትል ኃላፊ አቶ በላይ እንደገለፁት፣ ከለውጡ በፊት በነበሩ ዓመታት ከሀገራዊ ይልቅ የብሔር ማንነት ጎልቶ የወጣበት ሁኔታ ነበር፡፡ “የተለያየ ብሔር ሊኖረን፣ የተለያየ ቋንቋ ልንናገር እንችላለን፤ ስንሰባሰብ ደግሞ ኢትዮጵያዊ ማንነት ይኖረናል፡፡ በዚህ ረገድ የሚያሰባስብና የሚያጋምድ ትልቅ ሀገር እንድንፈጥር የሚያስችለን ትርክት ያስፈልጋል፡፡ በመሰረታዊነት ኢትዮጵያዊ ማንነት ጎልቶ መውጣት እንዳለበት” አቶ በላይ ያነሳሉ፡፡

ከሀገራዊ ለውጡ በፊት በኢህአዴግ (የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር) አባልና አጋር የነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ክልሎች ነበራቸው፡፡ በየራሳቸው ፓርቲ ተወያይተው በራሳቸው ክልል የሚወስኑበት፣ እንደሀገርም የሚነጋገሩበት ሁኔታ አልነበረም፡፡ አሁን ግን ሀገር እየመራ ያለው ፓርቲ ወጥ የሆነና ለሁሉም አባላት እኩል እድል የሚሰጥ በመሆኑ አንድ አጀንዳ ሲቀረፅ በሁሉም አካባቢ ሀገራዊ ይሆናል፡፡ ህብረ ብሔራዊነት እንደተጠበቀ ሆኖ እንደሀገር የሚወሰኑ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፣ ውይይት የሚደረግባቸው አግባብ ተፈጥሯል፡፡ ሀገራዊ ማንነትንና ክልላዊ (ብሔረሰባዊ ማንነትን) ሚዛናዊ ለማድረግ የፓርቲ አደረጃጀቱ እድል ሰጥቷል ይላሉ፤ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ምክትል ጽህፈት ቤት ኃላፊው አቶ በላይ፡፡

በፌዴራል እና ክልል መንግስታት መካከል ያለው ግንኙነት የሚመራበት የመንግስታት ግንኙነት አለመኖርም ሌላው የፌዴራሊዝም ስርዓቱ ክፍተት ነበር፡፡ የመንግስታት ግንኙነት አዋጅ ሲረቀቅ የኮሚቴ አባል በመሆን ከሰባት ዓመታት በላይ መስራታቸውንና ውድቅ ሲደረግ መቆየቱን የሚያነሱት አቶ በላይ፣ ስራዎች የሚሰሩት በፓርቲ መስመር ብቻ በመሆኑ ህጉ እንዲወጣ አይፈለግም ነበር፡፡ ሀገራዊ ለውጡ ከመጣ በኋላ ግን ፀድቆ ወደ ተግባር መግባቱን ያስረዳሉ፡፡

“የመንግስታት ግንኙነት የሚመራበት ህግ ሳይኖር አንድ የፌዴራል ስርዓት ጠንካራ ሊሆን አይችልም” የሚሉት አቶ በላይ፣ የመንግስታት ግንኙነት በክልልና ፌዴራል መንግስት መካከል ያሉ ጉዳዮች በውይይት፣ ንግግር፣ በድርድር፣ ሰጥቶ መቀበል ችግሮች የሚፈቱበት፣ ፖሊሲ የሚተነተንበት፣ እንደሀገርም ሀገራዊ አጀንዳዎች የጋራ የሚደረግበት ዕድል ይፈጥራል፡፡ ይህም ለፌዴራሊዝም ስርዓቱ መጠናከር የራሱ አስተዋፅኦ እንዳለው አብራርተዋል፡፡

### ቀጣይ ስራዎች

እንደ አቶ በላይ ገለጻ፣ አንድ ስርዓት በአንድ ጀምበር ሳይሆን በትውልድ ቅብብሎሽ ነው የሚገነባው፡፡ የኢትዮጵያ የፌዴራሊዝም ስርዓት በተተገበረባቸው ባለፉት ዓመታት ጠንካራ ሀገር ለመገንባት ተስፋዎች እና ሊሻገራቸው የሚገቡ ተግዳሮቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ፡ - በፌዴራሊዝም ስርዓቱ አንዱና ትልቁ ተግዳሮት ነጠላ ትርክት፣ ብሔራዊ ማንነትና ነጠላ ማንነት ወይም ሀገራዊ ማንነት እና ብሔረሰባዊ ማንነትን ሚዛናዊ አድርጎ አለመሄዱ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የተጀመሩ ስራዎች ቢኖሩም ብዙ መስራት ይጠይቃል፡፡

ሌላው የፌዴራሊዝም ስርዓቱ ጉድለት የዴሞክራሲ እጦት ነው፡፡ የዴሞክራሲና ፖለቲካ ባህላችን ደካማ ከመሆኑ የተነሳ በፌዴራሊዝም ስርዓቱ ትግበራ ላይ ጫና ሲፈጥር ቆይቷል፡፡ የፌዴራል ስርዓትና ዴሞክራሲ የሚነጣጠሉ ጉዳዮች አይደሉም፡፡ ከዚህ አኳያ በንግግር፣ ውይይትና ድርድር፣ በሰለጠነ መንገድ የውስጥ ችግርን መፍታት፣ የሀገር ጥቅምን ማስቀደም እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል፡፡

የፌዴራሊዝም ምሁሩ ቃሲም በበኩላቸው፣ የፌዴራሊዝም ስርዓቱ በተሟላ መልኩ እንዲተገበር መንግስት፣ የተፎካካሪ ፓርቲዎችና ማህበረሰቡ ለህገ መንግስቱ ታማኝ በመሆን የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡ ችግሮችን ህገ መንግስታዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ መፍታት ላይ መስራት ይገባል፡፡ መገናኛ ብዙሃን የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች መብቶች፣ ሀገራዊ ትርክቶች ላይ ግንዛቤ መፍጠር ይጠበቅባቸዋል። የመንግስት አካላትም ለህገ መንግስት ታማኝ በመሆን፣ ተፎካካሪ ፓርቲዎችና የፖለቲካ ጥያቄ ያላቸው አካላት ከጠብመንጃ ይልቅ ሰላማዊ መፍትሔን በመምረጥ ቢሰሩ ዘላቂነት ያለው ሰላምን ማረጋገጥ እንደሚቻል አስረድተዋል፡፡



# ማስታወቂያ

ዶ/ር ፀጋዬ ወልደጊዮርጊስ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ቦሌ 01/363/156-7488/00 በሴሪ ቁጥር 126686 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ/ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ**
**ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

በሂሩት ከበደ አጥናፍሰገድ ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር ቦሌ4/34/10/9/18416/00 የሴሪ ቁጥር 012430 የተሰጠበት ቀን 05/03/05 የቦታው ስፋት በሰነድ 94 ሜ.ካ የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በእኛ ተቋም የተሰጠ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ይሁንና በሂሩት ከበደ አጥናፍሰገድ ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር ቦሌ4/34/10/9/18416/00 የሴሪ ቁጥር 012430 የተሰጠበት ቀን 05/03/05 የቦታው ስፋት በሰነድ 94 ሜ.ካ የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ከእጃቸው የጠፋ ስለሆነ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ማህደሩን የምናደራጅ እና ሀላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር**
**ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

በሂሩት ከበደ አጥናፍሰገድ ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር ቦሌ10/52/3/6/33175/00 የሴሪ ቁጥር 057935 የተሰጠበት ቀን 26/10/07 የቦታው ስፋት በሰነድ 94 ሜ.ካ በሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በእኛ ተቋም የተሰጠ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ይሁንና በሂሩት ከበደ አጥናፍሰገድ ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር ቦሌ10/52/3/6/33175/00 የሴሪ ቁጥር 057935 የተሰጠበት ቀን 26/10/07 የቦታው ስፋት በሰነድ 94 ሜ.ካ የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ከእጃቸው የጠፋ ስለሆነ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ማህደሩን የምናደራጅ እና ሀላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር**
**ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የወ/ሮ አበባ ታረቀኝ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 12 ካርታ ቁጥር ቦሌ17/176/98-4460/00 ሴሪ ቁጥር 068227 የሆነ ኦርጅናል /ዋናው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በተለያየ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባለው 30 ቀናት ውስጥ በቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት የይዞታ አገልግሎትና ማስተካከል ዳሬክቶሬት ካልቀረበ በምትኩ ሌላ አዲስ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር**
**ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

በአልማዝ አልታዬ አለማየሁ አድራሻው በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር መለያ ቁጥር AA000090505057 ሴሪ ቁጥር R 0212463 የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ ታውጆ አገልግሎት እንዲሰጣቸው አመልክተዋል፡፡ በመሆኑም በጠየቁት መሰረት የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያሙች ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ካርታ ቁጥሮች እና በባለጉዳዮቹ ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ኦርጅናል ካርታም ሆነ ኮፒውን/ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 78 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ**
**ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

## ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በዋና ስራ አስፈጻሚ ጽ/ቤት ግዥ አስተዳደር ቡድን የ2018 በጀት ዓመት ሁለተኛ ዙር ጨረታ ከዚህ በታች በሎት የተጠቀሱትን ዕቃዎች በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

ሎት 1 ቋሚ የቢሮ እቃዎች

ሎት 2 የፅዳት አቃዎች

ጨረታውን ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች ከተ.ቁ 1-3 የተዘረዘሩትን በማሟላት መወዳደር ይችላሉ፡፡

1. ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸውና የዘመኑን ግብር የከፈሉበትን ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ እና በአቅራቢነት ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡ
2. የግብር ከፋይነት (tin number) ማቅረብ የሚችሉ
3. ተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑና ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ
4. ተጫራቾች የጨረታ ማስከቢሪያ ሎት አንድ 500,000.00 ብር ሎት ሁለት 10,000 ብር በCPO ብቻ ማስያዝ ይኖርባቸዋል
5. ተጫራቾች የጨረታውን ዝርዝር የያዘ ሰነድ የማይመለስ 250.00(ሁለት መቶ ሀምሳ ብር) በመክፈል ይህ የጨረታ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ10 (አስር) ተከታታይ የሥራ ቀናት ሆኖ የጨረታው ሰነድ ዘውትር በሥራ ሰዓት ሃይሌ ጋርመንት ላፍቶ አደባባይ በሚገኘው የከፍለ ከተማው ህንጻ ዘጠነኛ ፎቅ በመቅረብ መግዛት ይኖርባቸዋል ፡፡
6. ተጫራቾች የጨረታ መወዳደሪያውን ዋጋ በመሙላት እና ከተ.ቁ 1-4 የተጠቀሱትን ማስረጃዎች ኦርጅናልና ኮፒ በማሸግ ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ 10(አስር) የስራ ቀናት እስከ ቀኑ 11፡30 ሰዓት ድረስ ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል በ 10ኛው ቀን 11፡30 ሰዓት ሳጥኑ ይታሸጋል፡፡
7. ጨረታው በ11ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በግልጽ ይከፈታል
8. የጨረታው አሸናፊ ለመልካም አፈጻጸም (ለውል ማስረከቢያ) ያሸነፉበትን ዋጋ 10% ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
9. መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ተጫራቾች ለሚኖራቸው ጥያቄ በስልክ ቁጥር 011-8-34-27-15 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ።**

**በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ዋና ሥራ አስፈጻሚ ጽ/ቤት የመንግስት ግዢ ቡድን**

---

በተዋበች ወልዴ ሻንቆ ስም የቤቱ ልዩ መለያ ቁጥር AA0000801036983300321 በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በንፋስ ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 01 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ኮፒ (ካርታ) እና ማህደሩ ከመዝገብ ቤት ስለጠፋ በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 15 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ማህደር አደራጅተን ተለዋጭ ሰርተፊኬት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ሙሉወርቅ ይርጋ ኪዳኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 01 የሚገኘው በይዞታ ካርታ ቁጥር 01/93/21173/801372/01 በሴሪ ቁጥሩ 0219493 በስማቸው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ ወይንሸት ሰብስቤ ጌታጠሰኝ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉ/ክ/ከተማ ወረዳ 04 ነዋሪ የሆኑት የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000100501401 የሴሪ ቁጥር 0113589 በቀን 16/01/2017 ዓ/ም ወጪ የተደረገ ካርታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት/ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ጉለሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በዘሀራ ደድገባ ስም የተመዘገበ ይዞታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 የካርታ ቁጥር ኮ/ቀ/የማ/ን/መ/326/21466/00 የጠፋባቸው መሆኑን በቀን 19/3/2018 ዓ/ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ90 (ዘጠና) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ሳፋሪ አካዳሚ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 ካርታ ቁጥር ቦሌ ድ-444/98 በሴሪ ቁጥር 079509 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ /የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት /ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

## የየጨረታ ጥሪ (Bid Notice)

የቻይና ሲቪል ምህንድስና ግንባታ ኮርፖሬሽን (CCECC) ብቁ አማካሪ ድርጅቶችን ለሚኤሶ-ድሬዳዋ የፍጥነት መንገድ (ሎት 1 እና ሎት 2) አገልግሎት እንዲያቀርቡ ይጋብዛል።

1. ጨረታው ሁለት ፕሮግራሞችን ያካትታል፡-

የኤች አይ ቪ ኤድስና ሌሎች በግብረ-ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ HIV/AIDS and other STDs/ መከላከልና ቁጥጥር ፕሮግራም፤

2. የጾታ እኩልነት (Gender Mainstreaming) እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም (Sensitization program) ፕሮግራም።

ልምድ መስፈርት፡-

- ለSTD/HIV/AIDS:- አጠቃላይ 8 ዓመት ከመንገድ ግንባታ ዘርፍ ውስጥ ተመሳሳይ ልምድ፤
- ለጾታ እኩልነት (Gender Mainstreaming):- ከመንገድ ግንባታ ዘርፍ ጋር ተያያዥነት ያለው 3 ዓመት እና ከዛ በላይ ልምድ፤ ህጋዊ ድርጅቶችን ይመለከታል፡፡

ሙሉው የተግባ ርዝርዝር (ToR) በድሬዳዋ በሚገኘው የCCECC የምስራቅ ኢትዮጵያ ክልል ዋና መሥሪያ ቤት ይገኛል።

ፕሮፖዛሎች (ቴክኒካል እና ፋይናንሻል) ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ በአንድ (1) ሳምንት ውስጥ መቅረብ አለባቸው።

**Bike-Dire Dawa Expressway project**

---

**ጉዳዩ፡- የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ ይመለከታል።**

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ወረዳ 08 በ አዳነች በየነ ጎሮ ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ፣ የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000050800037 የተመዘገበ እና የሴሪ ቁጥር L 059132 የሆነ ካርታ እንደጠፋባቸው በቀን 24/03/2018 ዓ/ም አመልክተው ይህንኑ ይዞታ በጋዜጣ 90 ቀን ውስጥ በይዞታው መብት አለኝ የሚል እና ይህ ካርታ የጠፋ ስለሆነ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬትና ምዝገባ መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ማስታወቂያ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታው መጥፋቱን የሚያውቅ ካለ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባ መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ እንዲያሳውቅ እየገለጽን ይህ ባይሆን ለአመልካቹ አዲስ ካርታ ወጪ ተደርጎ የሚሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ/ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ጌታቸው ቦጋለ ፈለቀ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ካርታ ቁጥር ቦሌ ቦሌ/14/50/7/3/2787/53806/01 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ/ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

የአቶ ታደለ ወርቁ ደሳለው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የካ ክ/ከተማ ወረዳ 13 የቤቱ መለያ ኮድ /የጋራ መኖሪያ ቤት/ ቁጥር AA00005131077332503021 ሴሪ ቁጥር C 211867 በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት/ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካላቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት/ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ/ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

**ጉዳዩ፡- የደረሰኝ መጥፋት ማሳወቅ**

በአዲስ አበባ ክልል የአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 የቤት ቁጥር 1239ሀ ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0006004913 የሚታወቀው አሠለፍ ሚዲያና ኮሙኒኬሽንስ በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ------ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት የተሠራበት እና ያልተሠራበት የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ካሽ ፔይመንት ቮቸር ከቁጥር 251 - 450 እና ቲኦቲ ደረሠኝ ከ1 - 250 (የልተሠራባቸዉ) እና ቫት ደረሠኝ ከ1 - 50 እና ከ 901 - 1950፣ ቲኬት ከ1 - 10,000 (የተሠራባቸዉ) ስለጠፋብን በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራበት እና የጠፋ መሆኑ የሶስተኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ይሁንና ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው ለአራዳ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያ የሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም፡- አሠለፍ ሚዲያና ኮሙኒኬሽንስ**

---

መብራት ፋንታ ገብረኪዳን እና ሙሉ ፋንታ ገብረኪዳን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000060601054 ሴሪ ቁጥር R 049883 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

## የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ

በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 13 አስተዳደር እና ፋይናንስ ጽ/ቤት የ2018 በጀት አመት የ2ኛ ዙር ግዥ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል በመሆኑም ከታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የምታሟሉ ተጫራቾች እንድትወዳደሩ እያሳወቅን፡፡

| ተ.ቁ | የእቃው አይነት | የሎት አይነት | የጫረታ ማስከበሪያ ብር መጠን |
|---|---|---|---|
| 1 | የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች | ሎት 1 | 30,000 ብር |
| 2 | ፈርኒቸሮች | ሎት 2 | 20,000 ብር |
| 3 | የመስተንግዶ አቅርቦት | ሎት 3 | 8,000 ብር |
| 4 | የትራንስፖርት አገልግሎት | ሎት 4 | 5,000 ብር |
| 5 | የልብስ ስፌት አገልግሎት | ሎት 5 | 5,000 ብር |
| 6 | የህትመት አገልግሎት | ሎት 6 | 8,000 ብር |
| 7 | የመድረክ እቃዎች ኪራይ አገልግሎት | ሎት 7 | 8,000 ብር |

1. በጨረታ ለመወዳደር የሚፈልጉ ተጫራቾች በዘመኑ ህጋዊ የሆነ የታደሰ የንግድ ፍቃድ፣ ቲን ነምበር ያለው እና የቫት ተመዝጋቢ የሆነ እና መረጃ ማቅረብ አለበት፡፡
2. በጨረታው የሚወዳደሩ ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ በእየሎቱ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
3. ተጫራቾች በጨረታው ለመሳተፍ የሚያስችል በአቅራቢዎች ዝርዝር የተመዘገቡ ለመሆኑ ማስረጃ ከሰነዱ ጋር ማቅረብ የሚችል፡፡
4. ተጫራቾች ለሚወዳደሩበት እቃ ጫረታው ከመከፈቱ በፊት ናሙና ማቅረብ አለባቸው፡፡
5. ተጫራቾች ዋጋ ሲሞሉ ስርዝ ድልዝ ቢፈጠር ከፊት ለፊቱ ፊርማ ሊኖረው ይገባል አለበለዚያ የተሞላው ዋጋ ተቀባይነት የለውም፡፡
6. የጨረታ ሰነዱ አንዱ የጨረታ መመሪያ መሆኑን ተጫራቾች ሊረዱት የሚገባ ሲሆን በጨረታ ሰነዱ ላይ ያልተካተቱ ችግሮች ቢያጋጥሙን በግዥ መመሪያው መሰረት የሚዳኝ ይሆናል፡፡
7. ጨረታውን ለማወዳደር የእቃጥራት የዋጋ ዝቅተኝነት ወ.ዘ.ተ ግምት ውስጥ የምናስገባ ይሆናል፡፡
8. ጨረታውን ለማዛባት ወይም እንቅፋት ለመፍጠር የሚሞክሩ ተጫራቾች ከጨረታ ውጪ የሚሆኑ ሲሆን ወደፊትም በመንግስት ግዥ መመሪያ መሰረት በህግ እንዲከሰሱ ይደረጋል፡፡
9. ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ተጫራቾች ባቀረቡት የመወዳደሪያ ዋጋ ለውጥ ማሻሻያ ማድረግና ራሳቸውን ማግለል አይችሉም፡፡ እንዲሁም ከስፔስፊኬሽን ወይም ካቀረቡት ናሙና ውጭ ማቅረብ አይችሉም ፡፡
10. ጨረታው በሁለት ኢንቨሎፕ የሚቀርብ ሆኖ ኦርጂናል እና ኮፒ የጨረታ ሰነድ የሚል ጽሁፍ እንዲሁም ሙሉ የጫረታ ሰነዱ ኮፒ ተደርጎ በአቅራቢው ድርጅት ማህተም ተረጋግጦ ተመላሽ መሆን ይገባል፡፡
11. ጨረታው ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ተከታታይ የስራ ቀናት ክፍት ሆኖ የሚቆይ ይሆናል፡፡
12. ተጫራቾች መጫረቻ ሰነዶችን ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ እስከ 10ኛው ቀን ድረስ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ ጨረታው በ10ኛው ቀን 11፡00 ሰዓት የሚታሸግ ሲሆን ቀጣዩ ቀን የስራ ቀን ከሆነ ጠዋት 3፡30 ሰዓት ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ቢገኙም ባይገኙም የሚከፈትና የሚለይ ይሆናል፡፡
13. የመወዳደሪያ ሰነዱን ቦ/ክ/ከ/ወ/13/ አስተዳድር እና ፋይናንስ 4ኛ ፎቅ በመቅረብ አንድ ሎት ዋጋ የማይመለስ 300 (ሶስት መቶ) ብር በመክፈል መግዛት ይችላሉ፡፡
14. አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፉበትን ጠቅላላ ዋጋ 10% የውል ማስከበሪያ በማስያዝ ውል መያዝ አለባቸው፡፡ በተጨማሪም ውሉን ከተዋዋሉ በኃላ እቃውን በ10 ቀናት ውስጥ በአስተዳድሩ ግቢ ውስጥ ባለው ንብረት ክፍል አጠናቀው ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
15. ጽ/ቤቱ 20% መጨመር ወይም 20% መቀነስ መብቱ የተጠበቀነ ነው፡፡

**ማሳሰቢያ፡-** የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ፡-** ገርጂ ታክሲ ተራ ወረዳ 13 አስተዳድርና ፋይናንስ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 41 በአካል በመቅረብ ወይም በስልክ ቁጥር፡- 0118931655 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡

**በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 13 አስተዳደር እና ፋይናንስ ጽ/ቤት**

---

የጅማወርቅ ወርዶፋ ዴቲ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000061305947033000001 የሆነው ይዞታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራዝ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 የካርታ ቁጥር ቦሌ ሊዝ/ዕጣ/ጨ/020/95 የሆነው ይዞታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 07 ክልል ውስጥ በአቶ ፈሪድ መሀመድ ጋራድ ስም በልዩ መለያ ቁጥር AA000070707599 በሆነ የተመዘገበው ለድርጅት አገልግሎት የሚውል ይዞታ፤ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬቱ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጄ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

ጉዳዩ፡- የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ ይመለከታል፡፡

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ወረዳ 11 በ ትዕግስት ዓለሙ ወ/ዮሐንስ ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ፣ የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA00005110 5163 የተመዘገበ፣ የተሰጠበት ቀን 20/02/2010 ዓ/ም እና የሴሪ ቁጥር R 042821 የሆነ ካርታ እንደጠፋባቸው በቀን 18/03/2018 ዓ/ም አመልክተው ይህንኑ ይዞታ በጋዜጣ 90 ቀን ውስጥ በይዞታው መብት አለኝ የሚል እና ይህ ካርታ የጠፋ ስለሆነ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬትና ምዝገባ መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ማስታወቂያ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታው መጥፋቱን የሚያውቅ ካለ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባ መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ እንዲያሳውቅ እየገለጽን ይህ ባይሆን ለአመልካቹ አዲስ ካርታ ወጪ ተደርጎ የሚሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ/ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 07 ክልል ውስጥ በአቶ ፈሪድ መሀመድ ጋራድ ስም በልዩ መለያ ቁጥር AA000070702954 በሆነ የተመዘገበው ለድርጅት አገልግሎት የሚውል ይዞታ፤ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬቱ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጄ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 ቂሊንጦ ውስጥ በካርታ ቁጥር አቃ/ቃ/13/8/6/12681/00 በሴሪ ቁጥር 1638070 በአቶ ቸርነት ካሳ ረጋሳ የተመዘገበ ኮንደሚኒየም ዋና ካርታ ከእጃቸው የጠፋባቸው ስለሆነ ካርታውን የያዘ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ድረስ መጥተው ካላሳወቁ ማህደር በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው በዲ.አፍሪክ ስም በልደታ ክ/ከተማ በቀድሞ ወረዳ 03 ቀበሌ 51 በአዲሱ ወረዳ 09 የካርታ ቁጥር ል.51/79/8819/00 ሴሪ ቁጥር 032290፣ ጠቅላላ የቦታ ስፋት 3793 ካ.ሜ ሆኖ የተመዘገበ የይዞታ ካርታ ጠፋብኝ ብለው በቀን 19/03/2018 ዓ/ም በማመልከቻ የጠየቁ ስለሆነ፣ በመሆኑም በጠየቁት መሰረት የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ካርታ ቁጥሮች እና በባለጉዳይ ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (ኦርጅናል ካርታም ሆነ ኮፒውን) ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 72 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

አመልካች ዶ/ር ዘነበ ጀማነህ በቀን 19/03/2018 ዓ/ም ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት በቀድሞው ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 10 በለሚ ኩራ የካርታ ቁጥር ቦሌ10/101/9/10/598/00 በዶ/ር ዘነበ ጀማነህ የተመዘገበ ሲሆን የመኖሪያ ቤት ካርታ ስለጠፋብኝ ለፖሊስ ጣቢያ እና ለአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እንዲፃፍልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

በዚህም መሰረት በቀድሞው ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 10 በአሁኑ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ የሚገኝ ይዞታ ቤት ዶ/ር ዘነበ ጀማነህ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የካርታ ቁጥር ቦሌ10/101/9/10/598/00 ሴሪ ቁጥር 026765 ስፋት 150 ካ.ሜ የቤቱ አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነ ማረጋገጫ ካርታቸው የጠፋ ስለሆነ ቤቱን በዕዳ አስዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት ጥሪ የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ማህደሩን የምናደራጅ እና ሀላፊነቱን የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ በቀድሞ ወረዳ 19 ቀበሌ 60 በአዲሱ ወረዳ 11 ቤት ቁጥር--- በካርታ ቁጥር 16/446/806083/00 ለአቶ /ወ/ሮ/ወ/ሪት/እነ ታምራት ንጉሴ ታደሰ ተሰጥቷቸው የነበረው ካርታ የጠፋ ስለሆነ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 20 ቀን ድረስ ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ድረስ አቤቱታ እንዲቀርብ፡፡ ይዤዋለሁ የሚል ከሌላ ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# ተስፋ ያጫረው የስፖርቱ ስኬትና ምስጢሩ

**በሳህሉ ብርሃኑ**

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ በረጅም ርቀት ሩጫ ያስመዘገበችው ታሪክ የማይቀለበስ ቢሆንም፣ የሀገሪቱ ስፖርት በመሰረተ ልማት እጥረት ሳቢያ ሲፈተን ቆይቷል። ነገር ግን በቅርብ ዓመታት መንግስት ለስፖርት ዘርፍ በሰጠው ትኩረት ቀላል የማይባሉ ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡ ይህም የስፖርቱን ስኬት ወደላቀ ደረጃ ከፍ ሊያደርገው የሚችል ወሳኝ እርምጃ ነው፡፡ በዘርፉ ያሉትን ስር የሰደዱ ችግሮች ለመፍታት መሰረት የሚጥል ስለመሆኑ ብዙዎች ይስማማሉ፡፡

ለስፖርቱ ዘርፍ የሰጠው ትኩረት በተለያዩ ስራዎች የሚንፀባረቅ ነው። የአዲስ አበባ ስታዲየም ዕድሳትን ጨምሮ በተለያዩ ክልሎችና ከተሞች ዘመናዊ የስታዲየም ግንባታ ፕሮጀክቶች መጀመራቸው ወይም መጠናቀቃቸው አንደኛው ማሳያ ነው። በሌላም በኩል የወጣት ተሰጥኦዎችን ገና በለጋ ዕድሜያቸው ለይቶ በማውጣትና በማሰልጠን ላይ አድርጓል። በተለይ እንደ አዲስ አበባ ባሉ ከተሞች ደግሞ የስፖርት መሰረተ ልማቶችን ማስፋፋት፣ አካዳሚዎችን መክፈት እና በትምህርት ቤቶች የስፖርት ክህሎትን ማጎልበት ላይ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ይገኛል፡፡

የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ እጥረትን ለመቅረፍ የአዲስ አበባ ከተማ እያከናወነች ያለው ስራ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነው፡፡ ተተኪ ስፖርተኞችን በብዛት እና በጥራት ለማፍራት እየተሰሩ ያሉ ስራዎችም እንደዚሁም የአካል ብቃት እንቅስቃሴን ባህሉ ያደረገ ማህበረሰብ ለመፍጠር ድርሻው የጎላ ነው።

የማዕከላትና ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ አስተዳደር ልማት ዳይሬክተሩ አቶ ብርሃኑ ባዩ ከዚህ ቀደም ለዝግጅት ክፍላችን በጉዳዩ ላይ በሰጡት ማብራሪያ በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተገነቡ ያሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል እና የስፖርት ዓይነቶች ያካተቱ መሆናቸው ቀደም ሲል ከነበሩት የተለዩ ያደርጋቸዋል ብለዋል። ይህም ተተኪ ስፖርተኞችን ለማፍራት እንዲሁም ጤናው የተጠበቀ እና አምራች ዜጋ ለመፍጠር ትልቅ አስተዋጽኦ ይዞ መምጣቱን ተናግረዋል፡፡

የስፖርት መሰረተ ልማቱን ከማስፋፋት ጎን ለጎን ወጣትና አዳጊዎች ላይ በትኩረት እየተሰራ ይገኛል፡፡ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን፣ በባህል እና ስፖርት ሚኒስቴር የስፖርት ልማት ዘርፍ በኩል "ጉዞ 2029" የሚል ፕሮጀክት ተጀምሯል፡፡

የፕሮጀክቱ ዓላማ በአጭር ጊዜ ውስጥ በ2029 የአፍሪካ ዋንጫ የሚሳተፍ ቡድን ማድረስ፣ በረጅም ጊዜ ደግሞ አዳጊዎችን አብቅቶ ጠንካራና ወጥ አቋም ያለው ብሔራዊ ቡድን መገንባት ነው፡፡

የ"ጉዞ 2029" ፕሮጀክትን ለስኬት ለማብቃት ባለሙያዎች በመላው ሀገሪቱ አዳጊዎችን ፍለጋ ተሰማርተው ከክለቦች፣ ከክልሎችና ከአካዳሚዎች ከ 1 ሺህ 200 በላይ ተጫዋቾች የምልመላው አካል እንዲሆኑ በማድረግ ነበር ወደስራ የተገባው፡፡




ፎቶ ከገፀ ድር
ኢትዮጵያ ከ17 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድን ከ22 ዓመታት በኋላ ሞሮኮ በምታዘጋጀው የ 2026ቱ የአፍሪካ ዋንጫ ላይ ይሳተፋል

በሌላም በኩል 'አንድ ኳስ ለአንድ ሰልጣኝ' ፓይለት ፕሮጀክት በመላው ሀገሪቱ ያሉ የእግር ኳስ ችሎታ ያላቸው ከ15 እስከ 17 ዓመት ያሉ አዳጊዎች ተመልምለው የእግር ኳስ ስልጠና የሚያገኙበት ስለመሆኑም የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን መረጃ ያሳያል፡፡

ለሁለቱም ፆታዎች ተግባራዊ የተደረገው ፕሮጀክቱ ያለፉትን አራት ዓመታት በመርሃ ግብሩ የተካተቱ አዳጊዎችን ለማብቃት እየተሰራ ይገኛል። በዚህም ከ1 ሺህ 200 በላይ ሰልጣኞች መካተት ሲችሉ ወደ 54 አሰልጣኞች የተሳተፉበት ስለመሆኑ ተገልጿል፡፡ ሰልጣኞች የሚያስፈልጋቸው መኖሪያ፣ ምግብ እና ሌሎችም መሰረታዊ ፍላጎታቸው ተሟልቶ ትኩረታቸው እግር ኳሱ ላይ ብቻ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

በአበበ ቢቂላ ስታዲየም ሲከናወን የቆየውና ኢትዮጵያ ከ17 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድን ከ22 ዓመት በኋላ ለአፍሪካ ዋንጫ ማለፏን ያረጋገጠችበት ውድድር ደግሞ አዳጊዎች ላይ እየተሰራ ያለው ስራ ውጤት እያመጣ ስለመሆኑ ተስፋ ያጫረ ሆኗል፡፡ ኢትዮጵያ ኬንያን ማሸነፏን ተከትሎ ዩጋንዳ እና ታንዛኒያን ተከትላ ሞሮኮ በምታዘጋጀው የ2026ቱ ከ17 ዓመት በታች የአፍሪካ ዋንጫ ተሳታፊ መሆኗን አረጋግጣለች። የኢትዮጵያ ከ17 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድን የአፍሪካ ዋንጫ ተሳትፎ ሲያገኝ ከ22 ዓመት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው።

ብሔራዊ ቡድኑ ወደ አፍሪካ ዋንጫ ማለፉን ተከትሎ የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ላይ ባስተላለፉት መልዕክት በእግር ኳስ ስፖርት የተጀመረው ፕሮጀክት ፍሬ በማፍራት ላይ ስለመሆኑ ገልፀዋል፡፡

አያይዘውም ይህ ድል የእግር ኳስ ስፖርት ወዳድ ለሆነው ህዝብ የዘመናት ቁጭት በቅርቡ መልስ እንደሚያገኝ ያሳየ ነው ያሉት ከንቲባዋ "ቀይ ቀበሮዎቹ ያስመዘገቡት ውጤት ለዘርፉ የሰጠነው ትኩረት ውጤት እያፈራ መሆኑን ማሳያ ነው" ብለዋል።

የባህልና ስፖርት ሚኒስትር ወይዘሮ ሸዊት ሻንካ በበኩላቸው፣ ቡድኑ የመንግሥት እና የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ስራ ውጤት ነው ብለው፣ መንግስት በስፖርት ዘርፍ በርካታ የስፖርት መሰረተ ልማቶችን እየሰራ መሆኑን አውስተዋል፡፡ አክለውም፣ አዳጊና ህፃናትን ማዕከል ያደረገ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችም መሰራታቸውን፣ ብቁ፣ ተወዳዳሪና አሸናፊ ትውልድ ሲፈጠር የሀገር የኩራት ምንጭ መሆኑን ጠቁመው፣ ብሔራዊ ቡድኑ ያስመዘገበው ውጤት የዚሁ ማሳያ እንደሆነም ተናግረዋል።

የአፍሪካ ዋንጫ ተሳትፎውን ያሳካው ከ17 ዓመት በታች ቡድን ውስጥ ታዲያ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተመረጡ 17 አዳጊዎች በኢትዮጵያ የአዳጊዎች ብሔራዊ ቡደን አባላት ውስጥ ተሳትፎ ነበራቸው፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ በላይ ደጀን እንደገለፁት፣ ከተማ አስተዳደሩ እንደሀገር በቀጣይ ዓመታት በየስፖርት አይነቱ አሸናፊ ብሔራዊ ብድን ለመገንባት የተያዘውን ግብ ለማሳካታ ለአዳጊ ወጣቶች የስፖርት ስልጠና ልዩ ትኩረት በመስጠት እየተሰራ ነው፡፡

410 የአዳጊ ወጣቶች የስልጠና ፕሮጀክቶችን በ11ዱም ክፍለ ከተሞች በማቋቋም በ21 የስፖርት አይነቶች ከ22 ሺህ በላይ አዳጊዎች መደበኛ የስፖርት ስልጠና እየወሰዱ እንደሚገኙ አቶ በላይ አሳውቀዋል።

ከሀገራዊ ለውጡ ወዲህ ብቻ በመዲናዋ 1 ሺህ 530 የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን በመገንባት ተተኪ ስፖርተኞችን በብዛትና በጥራት ለማፍራት ምቹ መደላድል መፈጠሩን የቢሮ ኃላፊው ያስረዳሉ።

የ'አዲስ ተስፋችን እግር ኳስ ፕሮጀክት' አሰልጣኝ መሐመድ ናስር እንዳስረዱት የመዲናዋ ወጣቶች ደረጃቸውን በጠበቁ መጫወቻ ሜዳዎች በሚኖሩበት፣ በሚማሩበትና በሚሰሩበት አካባቢ በስፖርት እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ትልቅ ዕድል ፈጥሯል፡፡

የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በየአካባቢው በብዛትና በጥራት መኖር ለአዳጊ ፕሮጀክቶች የወጣቱን ጤንነት በመጠበቅ፣ አካል ለመገንባት፣ እና በሀገር አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆኑ ስፖርተኞችን ለማፍራት ምቹ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል ሲሉ ጨምረው ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት ለስፖርት ዘርፍ የሰጠው ትኩረት በሀገሪቱ ስፖርት ታሪክ ወሳኝ ምዕራፍ ሊሆን የሚችል ተስፋ ሰጪ ጅማሮ ነው። አሰልጣኙ እንደሚገልፁት የመንግስትን ጥረት ዘላቂና የበለጠ ፍሬያማ ለማድረግ ሊሰሩ ይገባቸዋል ያሏቸውን ጉዳዮች ያብራራሉ፡፡ የግል ባለሀብቶች ወደ ስፖርት ኢንቨስትመንት እንዲገቡ ማበረታታት እና ግልጽ የሆኑ የአጋርነት ስርዓቶችን መዘርጋት። እንደዚሁም የስፖርት ተቋማትን አመራር በስፖርት ዕውቀት እና በሙያዊ ብቃት ለተመረጡ ሰዎች ብቻ መተው ይገባል ይላሉ።

**"በአዲስ አበባ ከተማ 1 ሺህ 530 አዳዲስ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን በመገንባት ተተኪ ስፖርተኞችን በብዛትና በጥራት ለማፍራት ምቹ መደላድል ተፈጥሯል። 410 የአዳጊ ወጣቶች የስልጠና ፕሮጀክቶችን በ11ዱም ክፍለ ከተሞች በማቋቋም በ21 የስፖርት አይነቶች ከ22 ሺህ በላይ አዳጊዎች መደበኛ የስፖርት ስልጠና እየወሰዱ ይገኛሉ"**